# የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን

# መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 52/2013

ታህሳስ 2012 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# መግቢያ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌደሬሽን በአስተዳደሩ ውስጥ በተለያዩ እርከኖች በሚገኙ የከተማ፣ የክፍለ ከተማ፣ የወረዳ፣ የድርጅትና የክለቦችን የአትሌቲክስን ስፖርት ለማስፋፋት፣ ለማደራጀትና ለማጠናከር በከተማ አስተዳደሩ ስፖርት ኮሚሽን እንዲሁም በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ህጋዊ ስልጣን የተሰጠው አካል መሆኑ ይታወቃል፡፡

ሰለሆነም ፌዴሬሽኑ በአዲስ መልክ ሥራዎችን ለመስራት ብሎም የከተማውን የአትሌቲክስ ስፖርት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስና በከተማችን፣ በሀገር፣ በአህጉር እና በአለም አቀፍ ደረጃ የውድድር መድረኮች በአትሌቲክሱ መስክ ያላንን ተወዳዳሪነት ለማሣደግ ተልዕኮ እና ራዕዩን ሊያሳኩ የሚችሉ ልዩ ልዩ መመሪያዎችና አሠራሮች አዘጋጅቷል፡፡ ፌዴሬሽኑ የከተማ አስተዳደሩን ስፖርት ምክር ቤት፣ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን፣ የአህጉርና የዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን መመሪያዎች ባገናዘበና በማይጻረር መልኩ የአዲስ አበባን አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪ መመሪያ አሻሽሎ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ ይህን መተዳደሪያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

የስፖርቱ አመራር አካላት፣ አሰልጣኞች፣ ዳኞች፣ ሙያተኞች በየደረጃው የሚገኙ አባል ክለቦችና ክፍለ-ከተማዎች በስራቸው ታቅፈው የሚገኙ አትሌቶች በጠቅላላ ጉባኤው ጸድቆ የወጣውን መተዳደሪያ ደንብ የማክበርና ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት ስለላባቸው ተፈጻሚ እንድታደርጉ እናሳዉቃለን፡፡

በመሆኑም ለዚህ የዓላማ ስኬት ያግዘው ዘንድ የክለቦች፣ የፕሮጀክቶችና የልዩ ልዩ ቡድኖችን አደረጃጀት በመፈተሽ እንዲጠናከሩ፣ የውጤታማነትና የተፎካካሪነት ስሜታቸውን ከፍ በማድረግ የላቀ ብቃትና የጥራት ደረጃ ያላቸውን አትሌቶች ማፍራት እንዲችሉ ብሎም በሂደት ከድጐማ ወጥተው ራሳቸውን በፋይናንስ የሚችሉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ደመወዝ፣ ትጥቅ፣ ምግብ፣ ሕክምና ወዘተ... የመሳሰሉ በርካታ ወጪዎችን አውጥተው በሚያበቋቸው አትሌቶች ቀጥተኛ ተጠቃሚነታቸው እንዲረጋገጥ በማሰብ በአትሌቲክሱ ስፖርት ላይ የሚሠሩ የስፖርት ማህበራትንና ተቋማትን ወደ አትራፊነት (ወደ ቢዝነስ አስተሳሰብ) ሥርዓት በመቀየር ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ይህ የክለቦች፣ የፕሮጀክቶችና የልዩ ልዩ ቡድኖች ማቋቋሚያ መመሪያ ወጥቷል፡፡

ይህ ደንብ በውስጡ አራት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በክፍል አንድ ሥር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ በክፍል ሁለት ሥር ስለ ክለቦች፣ ፕሮጀክቶችና ልዩ ልዩ ቡድኖች አመሠራረት፣ መዋቅርና ምዝገባ፣ በክፍል ሶስት ሥር ስለአትሌቶች ቅጥር፣ ምዝገባና ዕድሳት፣ ተገቢነትና የዝውውር ሂደት በክፍል አራት ሥር የስፖርት ፌዴሬሽን፣ የክለቦች፣ የአትሌቶች እና የአሰልጣኞች መብትና ግዴታ/ኃላፊነት ተካተው ተዘጋጅተዋል፡፡

# ክፍል አንድ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ መመሪያ

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ባወጣው መመሪያና በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መመሪያ መሰረት የአዲስ አበባን የአትሌቲክስ ስፖርት በበላይነት የሚመራ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚል ስያሜ በህግ እንዲቋቋም አድርጓል፡፡

## አንቀጽ 1

## አውጭው አካል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ይህን መተደደሪያ መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 2

## ስያሜ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይገባል፡፡

## አንቀጽ 3

## ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ

1. **የከተማ አስተደዳደር ማለት**፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነው፡፡
2. **ስፖርት ኮሚሽን ማለት**፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ለማስፋፋት፣ ለማደራጀትና ለመምራት ህጋዊ ስልጣን ያለው ኮሚሽን ማለት ነው፡፡
3. **የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን**፡- ማለት የአትሌቲክስን ስፖርት በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ለማስፋፋትና ለመምራት በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡
4. **የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማለት**፡- በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የአትሌቲክስ ስፖርትን በበላይነት ለማስፋፋትና ለመምራት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳር ስፖርት ኮሚሽን ኃላፊነት የተሰጠው አካል ማለት ነው፡፡
5. **ጠቅላላ ጉባኤ**፡- የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን በበላይነት የሚመራ ከፍተኛው የስልጣን እርከን ነው፡፡
6. **መተዳደሪያ መመሪያ ማለት**፡- የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አባላትና አትሌቶች የሚመሩበትና የሚተዳደሩበት ገዥ መመሪያ ማለት ነው፡፡

7. **<u>የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ማለት</u>**፡- የአዲስ አባባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ የሚከታተል፣ የሚመራና አቅጣጫ የሚያስይዝ በጠቅላላ ጉባኤ የተመረጠና የተሰየመ አካል ነው፡፡
8. **<u>ፕሬዚዳንት ማለት</u>**፡- የፌዴሬሽኑን ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ጠ/ጉባኤውን በሰብሳቢነት የሚመራ የስፖርት ፌዴሬሽኑ የበላይ ኃላፊ ነው፡፡
9. **<u>ተ/ም/ፕሬዚዳንት ማለት</u>**፡- የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን በም/ሰብሳቢነት የሚመራ ኃላፊነት የተጣለበት አባል ማለት ነው፡፡
10. **<u>አቀቢ ንዋይ</u>** ፡- ማለት የፌዴሬሽኑን ፋይናንስና ንብረት በበላይነት የሚከታተልና የሚቆጣጠር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ማለት ነው፡፡
11. **<u>ዋና ጸሀፊ ማለት</u>**፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን በዋና ጸሐፊነት ተመድቦ እንዲሰራ የተወከለ ኦፊሰር /ባለሙያ/ ማለት ነው፡፡
12. **<u>ክለብ ማለት</u>**፡- የአትሌቲክስን ስፖርት እንቅስቃሴ ለማራመድ በድርጅት፣ በተቋም ወይም በግለሰብ ደረጃ የተቋቋመና በአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ስር ተመዝግቦ የሚገኝ ስፖርት ክለብ ማለት ነው፡፡
13. **<u>አባል ማለት</u>**፡- የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያ ተቀብሎ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባልነት፣ በንዑሳን ኮሚቴ አባልነት፣ በአሰልጣኝነት፣ በዳኝነት፣ በቡድን መሪነት፣ በወጌሻነት ፣ በአትሌትነት፣ በክለብና በክፍለ-ከተሞች አመራር ሰጭነት፣ በጽ/ቤት ሰራተኛነትና በስፖርት ፌዴሬሽኑ ዕውቅና ያላቸው በገንዘብና በማተርያል ድጋፍና ትብብር የሚያደርጉን ግለሰቦች/ባለሀብቶችና ድርጅቶች ይጨምራል፡፡
14. **<u>ክፍለ-ከተማ ማለት</u>** ፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የክ/ከተሞች ጽ/ቤቶች ማለት ነው፡፡
15. **<u>የክፍለ-ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማለት</u>**፡- የአትሌቲክስን ስፖርት በክፍለ ከተማው በሚገኙ ወረዳዎችና አግባብነት ባላቸው ክፍሎች ለማስፋፋትና ለማልማት በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡
16. **<u>አትሌት ማለት</u>**፡- በአትሌቲክስ ስፖርት ለመሰልጠንና ለመወዳደር ፍላጐትና ብቃት ያለው ታዳጊ፣ ወጣት እና አዋቂ ወንድ/ሴት ስፖርተኛ ማለት ነው፡፡
17 **<u>አሰልጣኝ ማለት፡-</u>** በአሰልጣኝነት ትምህርት፣ ስልጠና፣ ልምድ ብቁ ሆኖ እና ሕጋዊ ዕውቅና የተሰጠውና በውል ላይ ተመስርቶ በኮንትራት ወይም በጊዜያዊነት እንዲሁም በቋሚነት ተቀጥሮ አትሌቶችን የሚያሰለጥን ሁለገብ የሆነ ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ብቃታቸውን የሚያበለጽግ ባለሞያ ማለት ነው፡፡

18. **<u>ዳኛ ማለት</u>**፡- በዳኝነት ሰልጥኖ በቂ እውቀትና ልምድ ያለው በውድድር ወቅት ያለ አድሎ በታማኝነት በስነ-ምግባር የሚዳኝ ዳኛ ማለት ነው፡፡
19. **<u>ንዑሳን ኮሚቴ ማለት</u>**፡- በፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ልዩ ልዩ ስፖርታዊ ተግባራትን ለማከናወን የሚመረጡ ንዑሳን ኮሚቴዎች ናቸው፡፡
20. **<u>ውድድር ማለት</u>**፡- የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በግል ወይም በቡድን የሚያዘጋጃቸው ልዩ ልዩ የአትሌቲክስ ውድድሮች ናቸው፡፡
21. **<u>የጐዳና ሩጫ ማለት</u>**፡- ማንኛውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚካሄዱ የጐዳና ላይ ሩጫ፣ ፌስቲቫል በልዩ ልዩ መርህ ግብር የሚዘጋጅ ውድድር ነው፡፡
22. **<u>የጐዳና ላይ እግር ጉዞ ማለት፡-</u>** ማንኛውም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚካሄዱ የጐዳና ላይ እግር ጉዞ፣ ፌስቲቫል፣ ህብረተሰቡን ለፍቅር፣ ለአንድነት ለልዩ ልዩ በዓላት በተቋም፣ በኢቬንት ኦርጋናይዘር ወይም በልዩ ልዩ አዘጋጆች ከአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴረሽን ፍቃድ ሲያገኝ የሚካሄድ የእግር ጉዞ ልዩ ዝግጅትና ውድድር ነው፡፡
23. **<u>የግል ተወዳዳሪ ማለት፡-</u>** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መታወቂያ ካርድ ያላው/ት/ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው ውድድር ላይ በግል ተወዳዳሪነት ተመዝግቦ የሚወዳደር አትሌት ማለት ነው፡፡
24. **<u>አግባብነት ያላቸው ክፍሎች ማለት</u>**፡- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የታወቁ የስፖርት ማህበራት፣ ት/ቤቶች፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወ.ዘ.ተ. ናቸው፡፡
25. **<u>የዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማህበር (IAAF) ማለት፡-</u>** የአትሌቲክስ ስፖርትን በዓለም አቀፍ ደረጃ በበላይነት የሚመራ አካል ማለት ነው፡፡
26. **<u>የፌዴራል ስፖርት ኮሚሽን ማለት</u>**፡- ተጠሪነቱ ለባሕልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የሆነ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ስፖርት ኮሚሽን ማለት ነው፡፡
27. **<u>የአትሌቲክስ ስፖርት ማለት</u>**፡- የመም፣ የሜዳ ተግባር፣ የጐዳና ላይ ሩጫ፣ የርምጃ፣ የአገር አቋራጭና የተራራ ላይ ሩጫ ማለት ነው፡፡
28. **<u>የፕሮጀክት ቡድን ማለት፡-</u>** በሦስት የዕድሜ ክልል የሚከፋፈል (U-13 = ከ11-12 ዓመት)፣ (U-15 = ከ13-14 ዓመት)፣ (U-17 = ከ15-16 ዓመት) የታዳጊዎች ስልጠና ቡድን ማለት ነው፡፡
29. **<u>ልዩ ልዩ ቡድኖች ማለት</u>**፡- የክፍለከተማ ዋና እና ተስፋ ቡድን እንዲሁም የከተማው ምርጥ ቡድን የሚገልጽ ነው፡፡

30. **<u>ማናጀር ማለት፡-</u>** የአትሌቶች ወኪል በመሆን ከአይ.ኤ.ኤ.ኤፍ. እና ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፍቃድ (ዕውቅና) ተሰጥቶት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ ከሚገኙ አትሌቶች ጋር የሚሠራ ሕጋዊ ወኪል ማለት ነው፡፡

31. **<u>አለም አቀፍ ውድድር ማለት</u>፡-** ከአንድ አገር በላይ የሚሳተፉበት የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር ማለት ነው፡፡

32. **<u>አገር አቀፍ ውድድር ማለት</u>፡-** ከአንድ በላይ ክልሎች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ክለቦች እና ተቋማት የሚሳተፉበት የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር ማለት ነው፡፡

33. **<u>ከተማ አቀፍ ውድድር ማለት</u>፡-** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኙ ከአንድ ክለብ ወይም ተቋም ወይም ክ/ከተማ በላይ የሚሳተፉበት የአትሌቲክስ ስፖርት ውድድር ማለት ነው፡፡

34. **<u>ታዳጊ አትሌት ማለት</u>፡-** ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች ያለ (U-18፣ ከ15 እስከ 17 ዓመት) አትሌት ማለት ነው፡፡

35. **<u>ወጣት አትሌት ማለት፡-</u>** ዕድሜው ከ20 ዓመት በታች ያለ (U-20፣ ከ18 እስከ 19 ዓመት) አትሌት ማለት ነው፡፡

36. **<u>አዋቂ አትሌት ማለት</u>፡-** ዕድሜው 20 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ አትሌት ማለት ነው፡፡

# <u>አንቀጽ 4</u>

# <u>ዓላማ</u>

1. የዘር፣ የጾታ፣ የሃይማኖት፣ የቀለም ልዩነት ወይም ማናቸውም መድሎ ሳይኖር በአትሌቲክስ ስፖርት እንቅስቃሴ ጤናማ ዜጋን ለማፍራት በሚደረገው ሂደት ውስጥ የራሱን አስተዋጽ ለማድረግ፡፡
2. ስፖርተኞችን በየደረጃው በመልመልና ዘመናዊ ስልጠና በመስጠት የላቀ ችሎታና ብቃት ያላቸውን የአስተዳደሩና የሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች እንዲሳተፉ በማድረግ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ፣ የስፖርት ፌዴሬሽኑንና የሀገርን ስምና ዝና ማስጠበቅ፡፡
3. በስፖርቱ የወጡ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች ሀገር አቀፍ ደንቦችና መመሪያዎች በስፖርት ፌዴሬሽኑ አባላት በሙሉ እንዲከበሩ ማድረግ ፡፡
4. ከተለያዩ ድርጅቶችና አካላት ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር የአዲስ አበባ ከተማና የፌዴሬሽኑን ገጽታ ግንባታ ስራዎችን ማከናወን ናቸው፡፡

## አንቀጽ 5

## የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

1. በክፍለ ከተሞች በክለቦችና አግበብነት ባላቸው ክፍሎች በሚገኙ የአትሌቲክስ አመራር አካላት፣
2. በንኡሳን ኮሚቴ አባላት፣ በአሰልጣኞች፣ በቡድን መሪዎች፣ በወጌሻዎች ና በአትሌቶች
3. በፌደሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣ .
4. በስፖርተኞችና ማናጀሮች ላይ
5. በጽ/ቤት ሰራተኞች ለይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 6

## የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ዓርማ ማህተምና አድራሻ

1. የአዲሰ አባበ አስተዳደር  አትሌቲክስ ፌደሬሽን የራሱ ዓርማና ማህተም ይኖረዋል፡፡
2. የፌዴሬሽኑ  አርማና ፅሁፍ በክለቡ ማህተም ውስጥ ያርፋል፡፡
3. ፌዴሬሽኑ  የሚገኘው በአ.አ ከተማ በ በየካ ክ/ከተማ በጃንሜዳ ቅጥር ግቢ ውስጥ ይሆናል፡፡
4. የፌዴሬሽኑ ስልክ ቁጥር ቀጥታ መስመር 0118 67 76 36 ነው፡፡

## አባልነት፣ የአባላት መብትና ግዴዎች

## አንቀፅ 7

## አባልነት

1. የስፖርት ክለቡን የመተዳደሪያ መመሪያ ተቀብሎ በፌዴሬሽኑ ስር የተመዝገበ ክለብ፣ የክፍለ ከተማ ፌዴሬሽኖች  አባል ይሆናሉ፡፡
2. አባልነት የሚረጋገጠው በስፖርት ፌዴሬሽኑ ተመዝግቦ በሚመለከተው የስራ ሀላፊ ተፈርሞ የአባልነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሰጠው ነው፡፡

## አንቀጽ 8

## የአባልነት ዓይነቶች

1. የአባልነት ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

   ሀ/ የክብር አባል

   ለ/ መደበኛ አባል

2. የክብር አባልነት ስም የሚሰጠው ለስፖርት ፌዴሬሽኑ በዕውቀቱ፣ በገንዘቡ፣ በማቴርያልና በጉልበቱ ልዩ ውለታ የዋለና ከፍተኛ አግልግሎት ላበረከተ ነው፡
3. የክብር አባልነት ስም የሚሰጠው በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ ሲጸድቅ ነው፡፡

## አንቀጽ 9

## የአባላት መብት

1. የስፖርት ፌዴሬሽኑን እንቅስቃሴ በተመለከተ ገንቢና ጠቃሚ ማሻሻያ ሀሳቦች የማቅረብ፣
2. በሚዘጋጁ ደንብና መመሪያዎቸ ላይ ማሻሻያ ሀሳብ የመስጠት፣
3. ስፖርት ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ የመሳተፍ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 10

## የአባላት ግዴታዎች

1. ዓመታዊ መዋጮ የመክፈል፤
2. የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑን መተዳደሪያ ደንብ፣ የጠቅላላ ጉባኤንና ፣ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን ውሳኔዎችን የማክበርና የማስከበር፣
3. የስፖርት ፌዴሬሽኑን ዓርማና ስም የመጠበቅ፣
4. የራሱንም ሆነ የስፖርት ፌዴሬሽኑን ሞራልና ህልውና የሚነካ ድርጊት አለመፈጸም
5. የስፖርት ፌዴሬሽኑን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል አስጊ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የመጠቆምና የመተባበር ግዴታ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 11

## የክብር አባላት መብት

የክብር አባላት ከዚህ በታች የተጠቀሱት መብቶች ይኖራቸዋል፡፡

1. ስፖርት ክለቡ ወሳኝ ውድድር በሚያደርግበት ወቅት በክብር እንግድነት የመጋበዝ፣
2. በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ እንደአስፈላጊነቱ ሲጠሩ ተገኝተው ጠቃሚ ምክርና አስተያየት መስጠት፣
3. በራስ ተነሳሽነት ወርሀዊ ወይም ዓመታዊ የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 12

## የአባልነት መብት ስለማጣት

1. አንድ አባል የአባልነት መብት የሚያጣው

    ሀ/ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የጣለበትን እምነት አጉድሎ ከተገኘ፣

    ለ/ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያዎች ጥሶ ሲገኝ፣

ሐ/ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 10 ከተራ ቁጥር 1–5 የተጠቀሱትን የአባልነት ግዴታዎች ተግባራዊ ካላደረገ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ከአባልነቱ ሊወገድ ይችላል፡፡

# የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ተግባርና ኃላፊነት፣ ድርጅታዊ መዋቅር፣ የጠቅላላ ጉባኤ ጥንቅርና ኃላፊነት

## አንቀጽ 13

## የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ተግባርና ኃላፊነት

1. የአገሪቱን የስፖርት ደንብና መመሪያዎች፣ የአዲስ አበባ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽንና ሀገር አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የሚያወጧቸውን የስፖርት ደንብና መመሪያዎች በፌዴሬሽኑና በአባላቱ እንዲተገበሩና እንዲከበሩ ያደርጋል፤
2. በአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንቦች ላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ያከብራል፤
3. በአትሌቲክሱ ዘርፍ በየደረጃው ምርጥ አትሌቶችን በመምረጥ፣ በማደራጀት፣ ሙያተኞችና አሰልጣኞች በመመደብ በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ውድድሮች ላይ ይሳተፋል፤
4. ፌዴሬሽኑ በሂደት ራሱን እንዲችል የገቢ አቅም የሚያጎለብቱ ስልቶችን በመቀየስ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. የፋይናንስና፣ የማቴርያል ትብብር ከባለ ሀብቶችና ከድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ይጠይቃል፡፡
6. የስፖርት ፌዴሬሽኑ ራሱን የቻለ ዘመናዊ ጽ/ቤት ከማቴርያል ጋር እንዲኖረው ያደርጋል፣
7. ዳኞች፣ ሙያተኞች፣ አባል ክለቦችና ክ/ከተማዎች የቴክኒክ እገዛዎችና ትምህርትና ስልጠናዎች የሚያገኙበትን ሁኔታዎች ይፈጥራል፣
8. የስፖርት ፌዴሬሽኑን አቅም ባገናዘበ መልኩ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ይገዛል፣
9. ስፖርተኞችና አባላት በውድድርና በልምምድ እንዲሁም ለውድድር በሚጓዙበት ወቅት አደጋ ቢያጋጥማቸው፣ አቅምን ባገናዘበ መልኩ በሀገር ውስጥ ሕክምና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡
10. ታዳጊና ምርጥ ስፖርተኞችን በየደረጃው እንዲፈሩ በማድረግና ውጤት በማስመዝገብ የሀገርን ክብርና ዝና ያስጠብቃል፡፡
11. የልምምድና የውድድር ቦታዎችን ያዘጋጃል፡፡

12. ከሚመለከታቸው ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር የከተማ አስተዳደሩን ያስተዋውቃል፡፡
13. የመንግስት ፖሊሲዎች አገር አቀፋዊና አለም አቀፍ ደንቦችና ሕጎች በአባላት ዘንድ እንዲከበሩ ያደርጋል፡፡
14. ትምህርታዊ ሴሚናሮች፣ ውይይቶችና ኮርሶች በማዘጋጀት፣ የስፖርት ክለቡ አባላት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
15. ለውጤታማ ስፖርተኞችና አመራሮች ማበረታቻ ሽልማቶችን ያዘጋጃል፣
16. የስፖርት ፌዴሬሽኑን መተዳደሪያ መመሪያና የዲሲፕሊን መመሪያ በማያከብሩ የስፖርት ፌዴሬሽኑ አባላት/ ስፖርተኞች፤ አሰልጣኞች፤ የቡድን መሪዎች፣ ወጌሻዎች፣ የጽ/ቤት ሰራተኞች/ና ማናጀሮች ላይ ለአገር አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እያሳወቀ ደረጃውን የጠበቀ እርምጃ ይወስዳል፡፡
17. ከሌሎች አካላት ጋር የፈጸማቸውን የውል ስምምነቶች ያከብራል፣ የስፖርት ፌዴሬሽኑን ህልውና ያስጠብቃል፣ በህግ ለሌሎች አካላት የተደነገገውን መብት ያከብራል፣
18. ከስፖርታዊ ጨዋነት ውጭ የሆኑ ተግባራት በሌሎች ስፖርት ክለቦችና፣ አመራሮች ዳኞችና የአትሌቲክስ መሪዎች ላይ እንዳይፈጸም ያደርጋል፡፡
19. ይከሳል፣ ይከሰሳል ለሶስተኛ ወገን ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 14
## የፌዴሬሽኑ አደረጃጀት

ፌዴሬሽኑ የሚከተለው ድርጅታዊ መዋቅር ይኖረዋል፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ
3. አግባብነት ያላቸው ንኡሳን ኮሚቴዎች
4. ጽ/ቤትና ሰራተኞች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ 15
## የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ጥንቅር

1. የፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣
2. የክፍለ ከተማው ስፖርት ኮሚቴ ወይም ስፖርት ም/ቤት አንድ አንድ ተወካይ፣
3. የአንደኛ ዲቪዚዮን ክለቦች አንድ አንድ ተወካይ

4. የሁለተኛ ዲቪዚዮን ክለቦች ከ 1ኛ እስከ 5ኛ የወጡ አንድ አንድ ተወካይ
5. የአዲስ አበባ ከተማ ስፖርት ኮሚሽን አንድ ተወካይ
6. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አንድ ተወካይ፣
7. ድጋፍ ሰጭ የልዩ ልዩ ንኡሳን ኮሚቴ አባላት፣
8. ህጋዊ ዕውቅና ያላቸው የአ.አ አሰልጣኞች ፣ የዳኞች፣ የአንጋፋ አትሌቶች፣ የአትሌቶች ማህበር አንድ አንድ ተወካይ፤
9. የፌዴሬሽኑ የክብር አባላትና ከፍተኛ ስፖንሰር አድራጊዎች፤
10. በጠቅላላ ጉባኤ የተፈቀደላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች ተወካዮች፤
11. በጠቅላላ ጉባኤ የተሰየመ ኦዲተር አንድ ተወካይ፤

## አንቀጽ 16

## በድምጽ የሚሳተፉ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት

1. የፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት በሙሉ፣
2. የየክፍለ ከተማዎች አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አንድ አንድ ተወካዮች፣
3. የአንደኛ ዲቪዚዮን ክለቦች አንድ አንድ ተወካዮች፣
4. ሁለተኛ ዲቪዚዮን ክለቦች በዘመኑ የአ.አ ክለቦች ሻምፒዮና ውድድር ላይ የወንድና ሴት አጠቃላይ ውድድር ውጤት ከ 1ኛ እስከ 5ኛ የወጡ አንድ አንድ ተወካዮች፣
5. ህጋዊ ዕውቅና ያላቸው የአዲስ አበባ አሰልጣኞች ማህበር፣
6. ህጋዊ ዕውቅና ያላቸው የአዲስ አበባ የዳኞች ማህበር፣
7. ህጋዊ ዕውቅና ያላቸው የአዲስ አበባ አትሌቶች ማህበር፣
8. ህጋዊ ዕውቅና ያላቸው የአዲስ አበባ አንጋፋ አትሌቶች፣ ማህበር አንድ ተወካይ

## አንቀጽ 17

## ያለ ድምጽ የሚሳተፉ የጠቅላላ ጉባኤ አባላት

1. በምርጫ ወቅት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት፣
2. በዘመኑ በአ.አ.ክለቦች ሻምፒዮና ውድድር ከ 5ኛ ደረጃ በታች የወጡ የ2ኛ ዲቪዚዮን ክለቦች፣
3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን አንድ ተወካይ፣
4. የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አንድ ተወካይ፣

5. የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጽ/ቤት ኃላፊ፣
6. የድጋፍ ሰጭ የልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት፣
7. የፌዴሬሽኑ የክብር አባላትና ስፖንሰር አድራጊ ግለሰቦች፣
8. በጠቅላላ ጉባኤ የተፈቀደላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች፣
9. በጠቅላላ ጉባኤ የተሰየመ ኦዲተር አንድ አባል፤

## አንቀጽ 18
## የጠቅላላ ጉባኤ ተግባርና ኃላፊነት

ጠቅላላ ጉባኤው የፌዴሬሽኑ ከፍተኛ ስልጣን አካል ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡፡

1. በአዲስ አባባ ስፖርት ኮሚሽን፣ በሀገር አቀፍ፣ በአህጉርና በዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌደሬሽን የወጡና የሚወጡ የስፖርት ደንቦች፣ አዋጆችና መመሪያዎች በአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በየደረጃው በሚገኙ ስፖርት ቤተሰቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ መመሪያና አቅጣጫ ይሰጣል፡፡
2. በፌዴሬሽኑ ደንብና መመሪያዎች ላይ ማሻሻያ ሀሳብ ይሰጣል፡፡ያጸድቃል፡፡ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡
3. ያለፈውን ዓመት ቃለ ጉባኤና የስብሰባውን አጀንዳ ያፀድቃል፡፡
4. የስፖርት ፌዴሬሽኑን ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የኦዲትና ሂሳብ ሪፖርት አዳምጦ ያፀድቃል፡፡
5. የፌዴሬሽኑን ዓመታዊ ዕቅድና ማስፈጸሚያ ዓመት በጀት መርምሮ ያጸድቃል፡፡
6. የክብር አባላትን ብዛት ይወስናል፡፡ይመርጣል፡፡
7. አባላትን ይቀበላል፣ ከአባልነት ያግዳል፣ ያሰናብታል፡፡
8. ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የስልጣን ውክልና ይሰጣል፡፡
9. ከአባላት የሚቀርቡ የመልቀቂያ ጥያቄዎችን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
10. በሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
11. ምህረት ይሰጣል ቅጣት ያሻሽላል፡፡
12. የክብር አባላትን ይሰይማል፡፡
13. የቀጣዩን ዓመት ዕቅድና በጀት መርምሮ ያፀድቃል፡፡

# አንቀፅ 19
# መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ

1. መደበኛ ጠቀላላ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ በነሐሴ ወር ይካሄዳል፡፡
2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች በስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ ይዘጋጃል፡፡
3. አጀንዳዎችና ተያያዥነት ያላቸው ዶክመንቶች ከ15 ቀናት በፊት ለአባላት ይላካሉ፡፡
4. አበላት ሊካተትላቸው የሚገቡ አጀንዳዎች ካሉ ለፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ከ5 ቀናት በፊት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

# አንቀፅ 20
# አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ

1. አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ  አጀንዳዎችን አዘጋጅቶ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሊጠራ ይችላል፣
2. የጠቅላላ ጉባኤ ሁለት ሶስተኛው አባላት አስቸኳይ ጠ/ጉባኤ እንዲጠራ በፅሁፍ ሲጠይቁ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ጥያቄው በቀረበ አንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጉባኤው እንዲካሄድ ለአባላት ጥሪ ያስተላልፋል፡፡
3. የስብሰባው አጀንዳና ተያያዥነት ያላቸው ጠቃሚ ዶክመንቶች ስብሰባው ከመካሄዱ  ከ15 ቀን በፊት ለአባላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

# አንቀጽ 21
# የጠቅላላ ጉባኤ አመራርና ውሳኔዎችን ማሳለፍ

1. ጠቅላላ ጉባኤው በፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ይመራል፡፡ እሱ በሌለ ጊዜ በተ/ም/ፕሬዚዳንቱ ይመራል፡፡ ተ/ም/ፕሬዝዳንቱም ከሌለ በም/ፕሬዚዳንቱ ይመራል፡፡ ሦስቱም ካልተገኙ ከመካከላቸው በሚመረጥ አንድ አባል ስብሰባውን ይመራል፡፡
2. ፕሬዚዳንቱ ስብሰባውን በደንቡና በመመሪያው መሰረት እንዲከናወን የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡
3. የጠቅላላ ጉባኤው የስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ፌዴሬሽኑ በሚወክለው አካል ይከናወናል፡፡

# አንቀጽ 22
# የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች

1. ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መስጠት የሚችለው አጀንዳ በተያዘላቸው ጉዳዮች ብቻ ነው፣
2. ድምፅ የመስጠት መብት ካላቸው አባላት 50+1 ድጋፍ ካገኘ ውሳኔዎች ይወሰናሉ፡፡
3. የድምፅ ቁጥር እኩል ከመጣ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

4. የጠቅላላ ጉባኤ ተሳታፊዎች ድጋፍ የመስጠት፣ ድምጸ ታዕቅቦና ተቃውሞ መስጠት መብትና ግዴታቸው ነው፡፡
5. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች የጊዜ ገደብ ካልተቀመጠባቸው በስተቀር ወይም ተፈጻሚ የሚሆንበትን ጊዜ ስራ አስፈጻሚ እንዲወስን ውክልና ካልሰጠው በስተቀር ከተወሰነበት ዕለት ጀምሮ የጸና ሆኖ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
6. ደንብና መመሪያዎች፣ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤዎች አጀንዳ ማሻሻል፣ አባልን /አካልን ለመሰረዝ፣ የክብር ፕሬዚዳንት ወይም አባልነት መስጠትን፣ ማገድና ማፍረስን በተመለከተ ውሳኔዎች ሊተላለፍ የሚችለው ድምጽ የመስጠት መብት ካላቸው አባላት በ2/3ኛው ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው፡፡

## አንቀጽ 23

## የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዕጩ ስለማቅረብ

1. እያንንዱ የከፍለ ከተማ ስፖርት ኮሚቴ ወይም ስፖርት ምክር ቤት አንድ ዕጩ ለፕሬዝዳንትነት አንድ እጩ ለስራ አስፈጻሚ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዘመኑ የተመዘገቡ የአንደኛ ዲቪዘዮን ክለቦች አንድ አንድ ዕጩ ያቀርባሉ፡፡
3. በዘመኑ የ2ኛ ዲቪዚዮን የክለቦች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ውድድር በአጠቃላይ የወንድና ሴት ውጤት ከ1ኛ እስከ 5ኛ የወጡ ስፖርት ክለቦች አንድ አንድ ዕጩ ያቀርባሉ፡፡
4. የዕጩዎች አቀራረብ በጽሁፍ ማሕተም የኃላፊው ፊርማ ያረፈበት ሆኖ ለፌደሬሽኑ ከአንድ ወር በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡
5. ፌደሬሽኑ እጩዎችን ህጋዊነት ካረጋገጠ በኃላ ከምርጫው 15 ቀን በፊት ይፋ ያደርጋል ሆኖም አከራካሪ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ በሀገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ህግ መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 24

## የስራ አስፈጻሚ ኮሜቴ ምርጫ

1. አስመራጭ ኮሚቴው በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት በአንቀጽ 23 ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 የተዘረዘሩት ዕጩ አቀራቢዎች በጋራ ዕጩዎች ያቀርባሉ፡፡
2. ለፕሬዝዳንት ከቀረቡት ዕጩዎች መካከል እንድ በጠቅላላ ጉባኤ ይመረጣል ለስራ አስፈጻሚ ከቀረቡ ዕጩዎች መካከል ስምንት አባላትና ሁለት ተጠባባቂ ይመረጣል፡፡
3. የፕሬዝዳንት ሆነ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ ወይም በግልጽ እጅ በማውጣት ወይም በጹኍፍ ይሆናል፡፡

4. ተ/ም/ፕሬዝዳንት፣ም/ፕሬዝዳንትእና አቃቢ ነዋይ ከተመረጡ ስምንት ዕጩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መካከል በግልጽ ወይም በሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ በጠቅላላ ጉባኤ ይሰየማሉ፡፡
5. ለአቃቢ ንዋይነት ቦታ ከዕጩ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 8 አባላት መካከል ሙያዊ ትኩረት በመስጠት ከፍተኛ ድምጽ ያገኘው አቃቢ ንዋይ በመሆን ይሰየማል፡፡
6. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የምርጫ ሂደት በዲሞክራሲያዊ መንገድ በግልጽ ድምጽ አሰጣጥ መሰረት ይከናወናል፡፡
7. የፌደሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ የሚከናወነው በአራተኛው አመት በሰኔ ወር መጨረሻ ይሆናል፡፡
8. በሀገር አቀፍና በሌላ ስፖርት ማህበራት ላይ በስራ አስፈጻሚነት እያገለገሉ ሆነው ዕጩ ሆነው ሲቀርቡ ከነበሩበት ስፍራ ምን ያህል ዘመን በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴነት እንዳገለገሉ የሚገልጽ መልቀቂያ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
9. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን ማብቂያው በየአራት አመቱ ስለሆነ በጉባኤው አስመራጭ ኮሚቴዎች ከ3-5 አባላት ያሉት ያዋቅራል፡፡

## አንቀጽ 25

## የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መምረጫ መስፈርቶች

1. ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
2. ዕድሜው ከ21 ዓመት በላይ የሆነ፣
3. የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነ(የሆነች)
4. ፌደሬሽኑን ለማገልገል ሙሉ ፍቃደኛ የሆነ (የሆነች)
5. መልካም ስነ-ምግባር ያለውና በአርአያነቱ የሚጠቀስ ከጸረ- ስፖርት ድርጊት ና ሱሶች ነጻ የሆነ፤
6. በማንኛውም የስፖርት መስክ ተሰማርተው በአሰልጣኝነት፤በዳኝነትና በቡድን መሪነት ያሉ የስፖርት ባለሙያዎች በስራ አስፈጻሚነትና በንዑስ ኮሚቴነት ተመርጠው ማገልገል አይችሉም፡፡
7. ለስፖርት መስፋፋትና ዕድገት አስተዋትጽኦ ማድረግ የሚችል
8. በማንኛውም ስፖርት በዲሲፕሊን ያልታገደ፣
9. በህግ መብቱ ያልተገደበ/ች

# አንቀጽ 26

## የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጥንቅርና የስራ ዘመን

1. የፌዴሬሽኑ ስራ አሰፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ቁጥር ዘጠኝ ይሆናል፣

1.1 አንድ ፕሬዝዳንት

1.2 አንድ ተ/ም/ፕሬዚዳንት

1.3 አንድ ም/ፕሬዘዳንት

1.4 አንድ አቃቢ ንዋይ

1.5 አምስት  አባላት ይሆናሉ፡፡

1.6 የፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ኃላፊ ያለ ድምጽ አባል ይሆናል፡፡

1.7 በፌደሬሽኑ ውስጥ 30 ፐርሰንት ሴቶች በስራ አስፈጻሚነት ኮሚቴ ይካተታሉ፡፡

2. የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን 4 ዓመት ይሆናል
3. የስራ ዘመናቸውን የፈጸሙ ውጤታማ የፌዴሬሽኑ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ለቀጣዩ አራት ዓመት በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፣
4. የተጓደሉ አባለት ሲኖሩ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠባባቂዎች ባገኙት ድምጽ ቅደም ተከተል መሰረት ተክቶ ያሰራል፡፡ ለጠቅላላ ጉባኤውም አቅርቦ ያጸድቃል፡፡
5. በማሚያ ምርጫ የሚገባ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የስራ ዘመን የሌሎች ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን ይሆናል፡፡

# አንቀጽ 27

## የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለስፖርት ፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሀላፊነቶች ይኖሩታል

1. የፌዴሬሽኑን ስራ ይመራል፣ ያደራጃል ያስተባብራል፡፡
2. ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ያቋቁማል፣ የስራ መመሪያም ያዘጋጃል፡፡
3. በስፖርቱ የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
4. በስፖርቱ የማሻሻያ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ መረጃ ያደራጃል ያሰራጫል ወጤቱንም ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

5. ደረጃቸወን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከሚመለከታው አካሎች ጋር በመተባበር ይገነባል፣ ያስፋፋል፣ያስተዳድራል፡፡
6. ከተማ አቀፍ ውድድሮችን በሙሉ ስፖርታዊ ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፡፡
7. ለአሰልጣኞች፣ ለዳኞች፣ ለክለቦችና ለክፍለ ከተማዎች የፌዴሬሽኑ አባላት አቅም በፈቀደ መጠን ትምህርትና ስልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
8. የታዳጊ ወጣቶች አትሌቲክስ ፕሮጀክት እንዲስፋፋ፣ እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡
9. በየደረጃው ምርጥ ስፖርተኞችን ለማፍራት ዘመናዊ የስልጠና ስልት እንዲቀየስ ያደርጋል፡፡
10. ከአስተዳደሩ ስፖርት ኮሚሽን፣ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በመተባበር ለስፖርቱ የሚረዱ ኮርሶች፣ ሴሚናሮች፣ ወርክሾፖችና ስልጠናዎች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፡፡
11. በአገር አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ የአትሌቲክስ ስብሰባዎች ላይ ይገኛል፣ ውሳኔዎችንም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
12. ከቴክኒክ ኮሚቴ በሚቀርበለት መነሻ ሀሳብ መሰረት ለአዲስ አበባ አስተዳደር ምርጥ የአትሌቲክስ ቡድን፣ አሰልጣኞች፣ ወጌሻ ፣ የቴክኒክ አማካሪና ቡድን መሪ ይመድባል፡፡
13. የአትሌቲክስን ስፖርት በሚመለከት በሚቀርቡ ማናቸውም ክሶችና አቤቱታዎች እንዲሁም ይግባኞች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
14. አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የአትሌቲክስ ስፖርቱ እንዲስፋፋ እና ህብረተሰቡ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
15. የፌዴሬሽኑን ዓመታዊ የስራ እቅድና በጀት እንዲሁም መመሪያና ደንቦችን ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡
16. ከአቻ ፌዴሬሽኖች፣ ከሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ ክክለቦች፣ ከስፖርተኞችና ከሌሎች ስፖርት ቤተሰቦችና ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣ የአባላትን መብትና ጥቅም ያስጠብቃል፡፡
17. የክብር ፕሬዚዳንት ወይም የክብር አባላትን መርጦ ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፡፡
18. ለልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ደንቦችና መመሪያዎች ያዘጋጃል፣ በስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡
19. የጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡

20. የተለያዩ ዋንጫዎች፣ ሽልማቶችና ስጦታዎች ባግባቡ ተመዝግበው እንዲጠበቁ ያደርጋል፣
21. ቋሚና ጊዜያዊ የገቢ ምንጭ ፕሮጀክት እየቀረጸ የፌዴሬሽኑን የልማት ስራዎች ያከናውናል፣ ውድድሮችን በስፖንሰር ያካሄዳል፡፡
22. የፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያዎች፣ የፌዴሬሽኑን ስርዓትና የዲሲፕሊን መመሪያውን በማያከብሩ የክፍለ ከተማና የስፖርት ክለቦች፣ አመራር አካለትና፣ አሰልጣኞች ዳኞች የኮሚቴ አባላት ስፖርተኞችና የስፖርተኞች ማናጀሮች ላይ በመመሪያው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
23. በመጨረሻም ወቅታዊ ሪፖርት ለአዲስ አበባ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽንአስፈላጊ ለሆኑ ሌሎች አካላት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 28
## የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ

1. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት የስብሰባ ጊዜ በ15 ቀን አንድ ጊዜ ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተጨማሪ ስብሰባዎችን ማድረግ ይችላል፡፡
2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የራሱን የስብሰባ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡
3. ከአባላት መካከል ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤው እንደተሟላ ይቆጠራል፡፡
4. ከአባላት መካከል 3 አባላት ሰብሰባ እንዲደረግ ጥያቄ ካቀረቡ ፕሬዚዳንቱ ጥያቄው በቀረበ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን ሰብሰባ ይጠራል፡፡
5. ፕሬዚዳንቱ ጥያቄውን ተቀብሎ ስብሰባውን መጥራት ካልቻለ ጥያቂውን ካቀረቡት አበላት መካከል አንዱ ስብሰባውን መጥራት ይችላል፡፡ የመነጋገሪያ አጀንዳው ከሶስት ቀናት በፊት ለአባላት መድረስ ይኖርበታል፡፡
6. በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ወቅት ሌሎች ወገኖች በአስረጅነት ሊጋበዙ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 29
## ውሳኔ አወሳሰድ

1. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ውሳኔ በድምጽ ብልጫ ይከናወናል፡፡
2. ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡ ድምጽ ዕኩል ለዕኩል ከሆነ ፕሬዚዳንቱ የደገፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፡፡
3. በአብላጫ ድምጽ በተወሰኑ ውሳኔዎች ላይ ሌሎች አባላት ለውሳኔው ተገዥ ይሆናሉ፡፡
4. ውሳኔዎች በቃለ ጉባኤ ይያዛሉ፡፡ አባላት ልዩነታቸውን በቃለ ጉባኤ ማስያዝ ይችላሉ፡፡

5. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚወስነው ውሳኔ የጊዜ ገደብ ከላተቀመጠበት በስተቀር ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ ውሳኔው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 30

## የፌዴሬሽኑ ፕሬዚዳንት ተግባርና ሀላፊነት

ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡፡

1.በማንኛውም ስፍራ የስፖርት ፌዴሬሽኑን በመወከል ህጋዊ ተጠሪ ነው፡፡ ውል ይዋዋላል፣ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ውክልና የሰጣል፡፡

2.የጠቅላላ ጉባኤንና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን የስበሰባ አጀንዳዎች ከፌዴሬሽኑ ዋና ጸሀፊ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፡፡ሁለቱንም ስበሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

3. የጠቅላላ ጉባኤና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል

4.የፌዴሬሽኑ ስራዎች በፌዴሬሽኑ መመሪያዎች መሰረት መከናወናቸውን ይከታተላል፡፡ ያረጋግጣል፡፡

5.የፌዴሬሽኑን ገንዘብ ከአቃቢ ንዋዩና ከፌዴሬሽኑ ዋና ጸሀፊ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቀሳል፡፡

6.የኢመርጀንሲ ኮሚቴ ስብሰባን ይመራል፡፡

7.ፌዴሬሽኑን በመወከል ከማንኛውም አካል ጋር ግንኙነት ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 31

## የፌዴሬሽኑ ተ/ ም/ ፕሬዝዳንት ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለፕሬዚዳንቱ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነቶች ያከናውናል፡፡

1. ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ተክቶ በአንቀጽ 30 ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 የተዘረዘሩትን ተግባራት ያከናውናል፡፡
2. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡
3. በፕሬዚዳንቱና በስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ የሚሰጡትን መመሪያዎች /ተጨማሪ የስራ ድርሻዎች / ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 32

## የፌዴሬሽኑ ም/ ፕሬዝዳንት ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

1. የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ተ/ም ፕሬዝዳንት በማይኖርበት ጊዜ እርሱን ወክሎ ይሰራል፡፡
2. የሥራ አስፈጻሚ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡

## አንቀጽ 33

## የፌዴሬሽኑ አቃቤ ንዋይ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ስልጣንና ተግባራት ያከናውናል፡፡

1. የፌዴሬሽኑን የፋይናንስ እንቅስቃሴ በመመሪያ መሰረት መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡ወጭ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
2. የፌዴሬሽኑን ፋይናንስ ከፕሬዝዳንቱና ከዋና ጸሀፊው/ኦፊሰሩ/ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፡፡
3. የፌዴሬሽኑ ገቢና ወጭዎች በመመሪያና በስራ አስፈጻሚው ቃለ ጉባኤ መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፡፡
4. ለጠቅላላ ጉባኤው የፋናንሰንና ንብረት አስተዳደር ሪፖርት ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 34

## ኢመርጀንሲ ኮሚቴ

1. የስፖርት ፌዴሬሽኑ ኢመርጀንሲ ኮሚቴ አባላት ፕሬዚዳንቱ፣ ተ/ም/ፕሬዚዳንቱ ወይም ም/ፕሬዚዳንቱ አቃቢ ንዋዩና የፌዴሬሽኑ ዋና ጸሀፊ ይሆናሉ፡፡
2. የኢመርጀንሲ ኮሚቴ ስብሰባ የሚጠራው አስቸኳይና ፈጣን ጉዳይ ሲያጋጥም የኢመርጀንሲ ኮሚቴ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. በኢመርጀንሲ ኮሚቴ የተሰጠው ውሳኔ በሚቀጥለው ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡
4. የኢመርጀንሲ ኮሚቴ ውሳኔ የሚሰጠው በተቀመጠው ሕግና ደንብ ነው፡

## አንቀጽ 35

## የፌዴሬሽኑ ዋና ጸሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

ተጠሪነቱ ለፌዴሬሽኑ ፕሬዝዳንት ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ተግባርና ኃላፊነት ያከናውናል፡፡

1. የፌዴሬሽኑን ጽ/ቤት በመመሪያው መሰረት በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ያደራጃል፣ ይቆጣጠራል የዕለት ከዕለት ስራዎችን ያከናውናል፡፡፣

2. ከፕሬዚዳንቱ ጋር በመመካከር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴን የስብሳባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ስብሰባዎችን እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ በየስብሰባው አስተያዬቶችን ይሰጣል፡፡
3. የስራ አስፈጻሚ ከሚቴን ቃለ ጉባኤ ይይዛል፣ ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፤፤
4. የፌዴሬሽኑን የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡
5. የፌዴሬሽኑን የስራ እንቅስቃሴ በተመለከተ የመጻጻፍ ተግባራት ያከናውናል፡፡ የስፖርት ክለቡን ማህተምና ዓርማ ለስፖርት ክለቡ አገልግሎት ብቻ ያውላል፡፡
6. የፌዴሬሽኑን ሪከርዶችና ዶክመንቶች በአግባቡ ይይዛል፡፡
7. ከልዩ ልዩ ክለቦች፣ ከሀገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች፣ ከልዩ ልዩ ድርጅቶችና ከስፖርት ሚዲያዎች ጋር መልካም ግንኙነት ያደርጋል፣ ወቅታዊ ክንዋኔዎችን ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
8. የፌዴሬሽኑን ንብረቶች ደህንነታቸው እንዲጠበቅና በህግ አግባብ አገልገሎት ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል ግንኑነት ያደርጋል፣
9. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን ሪፖርት ተቀብሎ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያስፈጽማል፡፡
10. ከክለቦች፣ ከክፍለ ከተሞች ከአሰልጣኞች ከዳኞች፣ ከልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላትና ከአትሌቶች ጋር የሚቀርቡ አቤቱታዎች፣ ቅሬታዎችንና ይግባኞችን ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡ ውሳኔዎችንም ያሳውቃል፡
11. የተለያዩ የገቢ ምንጭ ማስገኛ ፕሮፖዛል ፕሮጀክት ያዘጋጃል፡፡ለተግባራዊነት ክትትል ያደርጋል፡፡
12. ለፌዴሬሽኑ የሚያስፈልጉ ማቴርያሎች እንዲሟሉ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡
13. የፌዴሬሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ በመመሪያው መሰረት ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
14. ከፕሬዝዳንቱና ከአቃቢ ንዋይ ጋር በመነጋገር እስከ ብር 1000.00/ አንድ ሺ/ ለአስቸኳይ ስራዎች ወጭ አድርጎ ተግባር ላይ ማዋል ይችላል፡፡ ገንዘቡም ወጪ ሆኖ በስራ ላይ ስለመዋሉ በወቅቱ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያሳውቃል፡፡
15. ደንብና መመሪያዎች ለክለቦችና ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲሰራጩ ያደርጋል፡፡
16. ፌዴሬሽኑ የሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ያስተባብራል፣ ይከታተላል ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

17. ለልማት ስራዎች ቅድሚያ በመስጠት የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡ በፌዴሬሽኑ ስር ለሚገኙ ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ስራዎችን ያከናውናል፡፡
18. በተጨማሪም ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተመሳሳይ ተግባራት ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 36
## ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች
## የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ንኡሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

1. የቴክኒክ ንኡስ ኮሚቴ
2. የስፖንሰርሺፕ የገቢ አሰባሳቢ ንኡስ ኮሚቴ
3. የጸጥታና ስፖርታዊ ጨዋነት ንኡስ ኮሚቴ
4. የህክምና ንኡስ ኮሚቴ
5. የኮሙኒኬሽንና የዶክመንቴሽን ንኡስ ኮሚቴ
6. የመስተንግዶና ፕሮቶኮል ንኡስ ኮሚቴ
7. የውድድርና ስነ ስርዓት ንኡስ ኮሚቴ

## አንቀጽ 37
## የኮሚቴዎች የጋራ መመሪያ

1. የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች ከፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተመርጠው ይመደባሉ፡፡
2. የኮሚቴዎች ተጠሪነት ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡
3. የኮሚቴ አባላት ቁጥር /3፣ 5፣ ወይም 7/ እንደ ስራው ስፋትና ጥበት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይወሰናል፡፡
4. ከአባላቱ ውስጥ ለእያንዳንዱ ኮሚቴ ም/ሰብሳቢና ጸሀፊ ይመረጣል፡፡
5. እያንዳንዱ ኮሚቴ የራሱን የስራ መመሪያ አዘጋጅቶ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡
6. ውሳኔዎች በመተዳደሪያ መመሪያ መሰረት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፡፡
7. የኮሚቴ አባላት የስራ ዘመን የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን ይሆናል፡፡ ድክመት የሚያሳዩ አባላት በውስጥ መመሪያቸው መሰረት በምተካቸው ሌላ አባል ሊተካ ይችላል፡፡
8. ከፌደሬሽኑ መመሪያዎች ውጭ ለሚከናወኑ ተግባራት ቋሚ ኮሚቴዎች በግልና በጋራ ተጠያቂዎች ይሆናሉ፡፡

9. ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወቅታዊ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለባቸው፡፡
10. በተጨማሪም ከስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

# አንቀጽ 38

# የልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

## 38.1. የቴክኒክ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የአትሌቶችን ፣ የአሰልጣኞችን የዳኞችን ተገቢነት ያረጋግጣል
2. የአትሌቶችን ዝውውር በደንቡ መሰረት መፈጸሙን አረጋግጦ ለአጽዳቂው አካል ያሳውቃል፡፡
3. የተለያዩ አካላት ለሚያዘጋጇቸው ውድድሮች ሙያዊ እገዛ ያደርጋል፡፡
4. በዝውውርና በተገቢነት ጉዳዮች በክለብና በአትሌቶች መካከል ያለመግባባት ሲፈጠር በደንቡና በመመሪያው መሠረት ስምምነት ላይ እንዲደርሱ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፡፡ መግባባት ካልቻሉና ህግ ተጥሶ በቴክኒክ ኮሚቴውም ሆነ በክለቦች ከተደረሰበትና አቤቱታ ከቀረበበት ጉዳዩን መርምሮ በደንቡ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. የከተማ አስተዳደሩን ወክለው የሚሰለፉ ምርጥ ተወዳዳሪዎችና አሰልጣኞች በመምሪጥ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያፀድቃል፣ ስራዉም ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡
6. የአ.አ ምርጥ ቡድኑ በተገቢው ሁኔታ ስልጠና ማግኘቱን ይከታተላል፣ የሚያስፈልገውን በጀትና የስፖርት ማቴሪያሎች አጥንቶ ለስራ አስፈፃሚ በማቅረብ በስራ ላይ ያውላል፡፡
7. ውድድሮችንና የፕሮጀክት ስልጠናዎችን ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡
8. አዳዲስ የማወዳደሪያ መሳሪያዎች እንዲሟሉ ያደርጋል፣ ለአዳዲስ መሳሪያዎች የትውውቅ ስልጠና ይሰጣል ይህንንም ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያፀድቃል፡፡
9. በየጊዜው ለሚሰጡ የዳኝነትና የአሰልጣኝነት ሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች የሚሰጡ ባለሙያዎችን ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመነጋገር ይመድባል፣ ስለ ስራዉ ሂደትም ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡
10. ተሻሽለው የወጡ የዳኝነትና የአሰልጣኝነት ህጐች ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያሳውቃል፤ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡
11. ወቅታዊና ዓመታዊ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡
12. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ተጨማሪ ተመሳሳይ ስራዎች ያከናውናል፡፡

## 38.2. የስፖንሰር ሺፕና የገቢ አሰባሳቢ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፌዴሬሽኑ የገንዘብ አቅም እንዲጎለብት የሚያግዙ ልዩ ልዩ የገቢ ምንጭ ስልቶችን እያጠና ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ሲፈቀድለት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

2. ውድድሮች በስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የሚከናወኑበትን ስልት ይቀይሳል፡፡ በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሲፈቀድ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
3. የስፖንሰርሺፕ ውሎችና ሰነዶችን ያዘጋጃል፣ በውሎች መሰረት ተግባሩን ያከናውናል፡፡
4. የኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴ በተመለከተ አሀዛዊ መረጃዎችን ገቢና ወጪዎችን እና የተገኙ የቁሳቁስ እርዳታዎችን በዶክመንት መዝግቦ ይይዛል፡፡
5. ወቅታዊና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ያቀርባል፡፡
6. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ተጨማሪ ስራዎች ያከናውናል፡፡

## 38.3. የፀጥታና የስፖርታዊ ጨዋነት ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የስፖርታዊ ጨዋነት መርሆዎች በስፖርት ቤተሰብ ዘንድ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡
2. ከውድድር አመራርና ሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ጋር በመተባበር ህብረተሰቡና የስፖርት አባላቶች ጨዋታ ህጎችን የሚገነዘቡበት ስልት እየቀየሰ ተግባራዊ ያደርግል፡፡
3. የስፖርታዊ ጨዋነት ተሸላሚ ሊሆኑ ለሚችሉ ክለቦች፣ ደጋፊዎችና ግለሰቦች የመምረጫ መመዘኛዎች ያዘጋጃል፡፡ ተሸላሚዎችንም መርጦ ያሸልማል፡፡
4. ከፀጥታ አስከባሪዎች ጋር ግንኙነት በማድረግ ውድድሮች በሚካሄዱባቸው ቦታዎች የፀጥታ ኃይሎች እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡ ተግባራቸውን መውጣታቸውን ይከታተላል፡፡
5. ሁከትን የሚጋብዝ ሁኔታ ሲከሰት ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በመተባበር በቁጥጥር ሥር እንዲውል ያደርጋል፡፡
6. የፀጥታ አጠባበቅ ሁኔታ በየጊዜው የሚሻሻልበትን ስፖርታዊ ጨዋነት የሚሰፍንበትን ስልት ይቀይሳል፡፡ ተግባራዊም እንዲሆን ያደርጋል፡፡
7. ስለኮሚቴው የሥራ እንቅስቃሴ መረጃዎችን በዶክመንት ይይዛል፡፡
8. በጎዳና ውድድር ሁኔታዎችን በማመቻቸት በቂ የትራፊክ ፖሊሶች እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡
9. ወቅታዊና ዓመታዊ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡
10. ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተጨማሪ ስራዎች ያከናውናል፡፡

## 38.4. የህክምና ንዑስ ኮሚቴ ተግባር ኃላፊነት

1. የስፖርት ሕክምናን በተመለከተ ኮርሶችን፣ ሴሚናሮችንና ወርክሾፖች ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡
2. በአ/አበባ ከተማ አቀፍ ለሚካሄዱ የአትለቲክስ ውድድሮች የሕክምና ባለሙያዎችን እንደአስፈላጊነቱ እንዲመደቡ ያደርጋል፡፡

3. ለስራዉ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች እንዲሟሉ ከሚመለከተው አባላት ጋር በመነጋገር አስፈቅዶ በስራ ላይ ያውላል፡፡
4. ስለ ስራው ሂደት ተገቢውን ክትትልና ግምገማ በማድረግ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
5. የቀይ መስቀል አምቡላንሶችን ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ጋር በመገናኘት ያስፈቅዳል፡፡ ለሥራም ያመቻቻል፡፡
6. የህክምና መገልገያዎች በዕርዳታ እንዲገኙ ተገቢውን ጥረት ያደርጋል፡፡
7. አትሌቶች የኃይል ሰጪ መድኃኒት እንዳይጠቀሙ በቅድሚያ ያስተምራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡
8. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተጨማሪ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 38.5. የኮሚኒኬሽን፣ ዶክመንቴሽን ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የፌዴሬሽኑን የሥራ እንቅስቃሴ፣ የውድድር ፕሮግራሞችን፣ ውጤቶችና ህብረተሰቡ ማወቅ የሚገባውን ስፖርት ነክ ዜናዎችና መግለጫዎች ከተለያዩ የስፖርት ሚዲያዎች ጋር በመገናኘት ፌዴሬሽኑን ኢሜጅ የመገንባት ተግባራት ከኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጋር በመተባባር ያከናውናል፡፡
2. ለፌዴሬሽኑ የሥራ እንቅስቃሴ አስፈላጊ የሆኑ መጽሔቶች፣ ፖስተሮችን፣ በራሪ ጽሁፎችንና ሌሎች የህትመት ሥራዎች እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደርጋል፡፡
3. ከፀጥታና ስፖርታዊ ጨዋነት ኮሚቴ ጋር በመተባበር ስፖርታዊ ጨዋነት በስፖርት ቤተሰብ ዘንድ እንዲሰርጽ በውድድር ቦታዎች ትምህርታዊ መግለጫ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡
4. የስፖርቱን እንቅስቃሴ በተመለከተ ከኤምባሲዎች፣ ከአምባሳደሮችና ከዕርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ጋር የውጭ ግንኙነት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡
5. መጽሔቶችና ፖስተሮች እንዲሁም ሌሎች የህትመት ሥራዎች በስፖንሰር አድራጊ ድርጅቶች ድጋፍና ትብብር እንደ አስፈላጊነቱ እንዲታተሙ ያደርጋል፡፡
6. ህጋዊ ከሆኑ አወዳዳሪ አባላት ጋር ተቢውን የሥራ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፡፡
7. ከጽ/ቤቱ ጋር በመሆን በታሪክ መዘክር ተቀርፀው መቀመጥ የሚገባቸውን የፌዴሬሽኑን እንቅስቃሴ በፊልም፤ በቪዲዮ ካሴት፤ በፎቶግራፍ፤ በአሃዝና በዶክመንት መዝግቦ ይይዛል፡፡ ለሚመለከታቸው ክፍሎችም እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

8. ፌዴሬሽኑን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሚቀርቡና በሚነሱ አሉታዊ መግለጫዎች ወቅታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ በአጠቃላይ በፌዴሬሽኑ ውስጣዊና ውጫዊ እንቅስቃሴዎችን ከኮሚሽኑ ጉዳዮች ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡
9. የፌዴሬሽኑ ሽልማቶች ባግባቡ እንዲያዙና እንዲቀመጡ ያደርጋል፡፡
10. ስለ ኮሚቴው የሥራ ሂደት ተገቢውን ሪፖርት አዘጋጅቶ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በወቅቱ ያቀርባል፡፡
11. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተጨማሪ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 38.6. የፕሮቶኮልና መስተንግዶ ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለስብሰባ፣ ለሴሚናርና ለወርክሾፕ እንዲሁም በግብዣ ወቅት ለሚጠሩ እንግዶች የመሰብሰቢያ አዳራሽ ያዘጋጃል፣ ለተሰብሳቢዎች የጥሪ ወረቀት ያዘጋጃል፡፡ አስፈላጊው መስተንግዶ እንዲሟላ ያደርጋል፡፡
2. ከጽ/ቤቱ ጋር በመሆን የውል ስምምነቶች በተገቢው መንገድ እንዲከናወኑ ያደርጋል፡፡
3. የሽብርቅ ሥራዎችንና በተጨማሪም ሌሎች የፕሮቶኮልና የመስተንግዶ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
4. የኮሚቴ/ውን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርቶች በማጠናከር ለሚመለከተው ክፍል ያቀርባል፡፡
5. ወቅታዊ ሪፖርት እያዘጋጀ ለሥራ አስፈፃሚ ያቀርባል፡፡
6. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

## 38.7. የውድድር አመራርና ሥነ ሥርዓት ንዑስ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ውድድር ዓመታዊ የውድድር መርሃ ግብር ከቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በማዘጋጀት ለፌዴሬሽኑ ያቀርባል ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
2. በአ/አበባ ከተማ አቀፍ ደረጃ ለሚከናወኑ ውድድሮች የውድድር ፕሮግራሞች ያዘጋጃል፡፡ ውድድሩ የሚካሄድበትን ቀን፣ ሰዓትና ውድድሩን ቦታ ይወስናል፡፡
3. አስፈላጊና አስገዳጅ የሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለተወዳዳሪ ክለቦች፣ ክ/ከተሞች ውድድሩን ለሚመሩ ዳኞችና ለሚመለከታቸው ክፍሎች አስቀድሞ በማሳወቅ የውድድሩን ፕሮግራም ቀን ሰዓትና ቦታ መቀየር ይችላል፡፡
4. በክ/ከተማ ደረጃና በሌሎች አካላት ለሚዘጋጁ ውድድሮች የትብብር ጥያቄ ሲቀርብ ደንብና ፕሮግራሞችን ያወጣል፡፡
5. የማወዳደሪያ ቦታዎችን ያመቻቻል የውድድር ፕሮግራሞችን ያሳውቃል፡፡
6. ከዳኞችና ከታዛቢዎች የሚቀርቡ ሪፖርቶችና አቤቱታዎችን ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

7. ከውድድር በተወገዱ አትሌቶች፣ ቡድኖች፣ በታዛቢ ሪፖርት ክስ የተመሰረተባቸው የቡድን መሪዎች፣ አሰልጣኞችና ወጌሾች ላይ በደንቡ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
8. በየውድድሩ ፍፃሜ ላይ ተገቢውን ኮሚኒኬ በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
9. ከቴክኒክ ንኡስ ኮሚቴና ከሌሎች ኮሚቴዎችጋር በመቀናጀት ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡
10. በውድድር ህጎች ውሳኔዎች ላይ መግለጫዎችን ይሰጣል፡፡
11. ለውድድር ህጎች የማሻሻያ ሃሳቦችን በማዘጋጀት ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡
12. በከተማ አስተዳደሩ ተመዝግበው የሚገኙ የአትሌቲክስ ዳኞችንና አሰልጣኞች የህይወት ታሪክ መረጃ በየደረጃው ለይቶ ይይዛል፡፡
13. በፌዴሬሽኑ ተመዝግበው በዳኝነት ሥራ ላይ ለሚገኙ ዳኞች ከቴክኒክ ኮሚቴ ጋር በመሆን በየጊዜው የሙያ ማሻሻያ ትምህርት የሚያገኙበት መንገድ ያመቻቻል፡፡
14. በከተማው አስተዳደሩና በክ/ከተማው ደረጃ ለሚደረጉ ውድድሮች የዳኞች ማህበር አንድ ተወካይ በሚገኝበት ተገቢ ዳኞች ይመድባል፡፡
15. ዳኞች በውድድር ወቅት የሚገለገሉባቸው የተለዩዩ ፎርሞች /ቅጻ ቅጾች/ አዘጋጅቶ በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡
16. የተለያዩ ክፍሎች በሚያዘጋጇቸው ውድድሮች ላይ የአትሌቲክስ ዳኞች እንዲመደቡ ያደርጋል ስለስራቸውም አስፈላጊው ክትትል ያደርጋል፡፡
17. በውድድር ቦታዎች በመገኘት የዳኝነት ስራዎችን ይከታተላል፡፡
18. በአጥፊ ዳኞች ላይ የመጀመሪያ ቅጣት ውሳኔ በመስጠትና በተለያዩ ጊዜ በሚዘገዩ ያለበቂ ምክንያት በሚቀሩና በውድድር ቦታ ችግር በሚፈጥሩት ለይ ችግሩን ተመለክቶ በደንቡ መሰረት ውሳኔ ይሰጣል፡፡
19. ያከናወናቸውን ተግባራት /ሥራዎች/ በቃለ ጉባኤ በመያዝ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡
20. የክለቦች፣ የክፍለ ከተሞችን፣ የታዳጊዎችንና የወጣቶችን ከተማ አቀፍ ውድድሮች ማስፈፀሚያ ዝርዝር የውድድር ደንብና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፡፡ እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡ ከውድድሩ በፊትም ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፡፡
21. ለውድድር የሚያስፈልጉ የሽልማት ዓይነቶች ብዛት፣ መጠንና ሌሎች ለስራ አስፈላጊ የሆኑ ማቴሪያሎች /ቁሳቁሶች/ እንዲሟሉ ሀሳብ ያቀርባል ይከታተላል፡፡

22.በውድድር ሂደቶች በሚከሰቱ ልዩ ልዩ ችግሮች ላይ ከክለቦች፣ ከክፍለ ከተሞች፣ ከቡድን መሪዎች፣ ከአሰልጣኞች፣ ከዳኞች ከኮሚቴ አባላትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማመቻቸት ይወያያል፡፡

23. የውድድር ፕሮግራሞችን ውጤቶችን፣ ቻርቶችን፣ አህዛዊ መግለጫዎችንና አጠቃላይ የኮሚቴውን የዶክሜንቴሽን ስራ ከኮሚኒኬሽንና ዶክሜንቴሽንና መስተንግዶ ኮሚቴ ጋር በመሆን መግለጫ ይሰጣል፡፡

24.በተጨማሪም ከስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠውን ተጨማሪ ስራ ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 39

## የበጀት ዘመን

የፌዴሬሽኑ የበጀት ዘመን ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቀን የአንድ ዓመት ጊዜ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 40

## የፌዴሬሽኑ የገቢ ምንጭ

## የፌዴሬሽኑ የገቢ ምንጭ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከስፖንሰርሺፕና ከማስታወቂያ ገቢ
2. ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን ከሚገኝ ድጎማ
3. ከአባል ክለቦች ዓመታዊ መመዝገቢያ ክፍያ
4. ከታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ የሚገኝ ገቢ
5. ከአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን ከሚገኝ ድጎማ
6. ከመወዳደሪያ የደረት ቁጥር ሽያጭ
7. የድጋፍ ደብዳቤ ከሚጠይቁ አካላት
8. ከጎዳና ሩጫ፣ እግር ጉዞ ከሚያደርጉ ድርጅቶችና ተቋማት
9. ከዕርዳታና ከስጦታ ከሚገኝ ገቢ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 41

## የፌዴረሽኑ የፋይናንስ እንቅስቃሴ

1. በአንቀጽ 46 ከተራ ቁጥር 1 እስከ 9 ለተዘረዘሩት ገቢዎች ፌዴሬሽኑ አንድ የባንክ አካውንት ይኖረዋል፡፡
2. የፌዴሬሽኑ ገቢዎች በፌዴሬሽኑ የፋይናንስ መመሪያና በስራ አስፈጻሚ ኮመቴ ውሳኔ መሰረት ይከናወናሉ፡፡

3. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ገቢዎች በተከፈተው የባንክ አካውንት ገቢ ሳይሆን ወጭ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ተግባር ነው፡፡
4. በጀት ላልተያዘላቸው ድንገተኛ ጉዳዮች ለመጠባባበቂ ከተያዘው እስከ ብር 1000.00 /አንድ ሺ ብር/ ድረስ ወጭ አድርጎ በስራ ላይ ማዋል ይቻላል፡፡ ወጭው በጠቅላለ ጉባኤ ስብሰባ ወቅት ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል፡፡
5. ለልዩ ልዩ ውድድሮች ማከናወኛ መነሻ በጀት በቴክኒክ ኮሚቴው ተዘጋጅቶ ይቀርባል፡፡ በጽ/ቤት ኃላፊው ታይቶ በስራ አስፈጻሚው ኮሚቴ ሲጸድቅ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 42

## ስለ ሂሳብ ምርመራ

1. የፌዴሬሽኑ ሂሳብ በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ በውስጥና በፌዴሬሽኑ በተመረጠው ኦዲተር ኦዲት ይደርጋል፡፡
2. የምርመራ ውጤቱም በኦዲት አድራጊው አካል ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ይቀርባል፡፡

## አንቀጽ 43

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

በዚህ መመሪያ ያልተጠቀሱ ጉዳዮች በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ደንብና መመሪያዎች ተፈጻሚነት_ይኖራቸዋል፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የክለቦችና የፕሮጀክቶች ማቋቋሚያ መመሪያ 53/2013 ዓ/ም

# አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የክለቦች፣ የፕሮጀክቶች እና የልዩ ልዩ ቡድኖች ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 53/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

# አንቀጽ 2

# አውጪው አካል

**የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ወጣቶችና ስፖርት ኮሚሽን** በ2003 ዓ.ም የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበት ሁኔታ ለመወሰን ባወጣው መመሪያና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በ2010 ዓ.ም ባወጣው የውስጥ አሠራር ደንብ መሠረት ይህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክለቦች፣ ፕሮጀክቶችና የልዩ ልዩ ቡድኖች ማቋቋሚያ መመሪያ ወጥቷል፡፡

# አንቀጽ 3
# የመመሪያው ዓላማና አስፈላጊነት

የከተማችን እና የአገራችን የአትሌቲክስ ስፖርት እንዲጠናከርና ተተኪ አትሌቶችን ለማፍራት እንዲቻል ታዳጊ፣ ወጣትና አዋቂ አትሌቶችን በመያዝ እና ወቅታዊና ሳይንሳዊ ስልጠና በመስጠት ተቋማቸውን፣ ክለባቸውንና ከተማቸውን የሚያስጠሩ ምርጥ አትሌቶች በተቀናጀና በተደራጀ አካሄድ በየደረጃው ለማፍራትና ለማስተዳደር ይረዳ ዘንድ ወቅቱ የሚጠይቀውን ምቹ የአሠራር ሁኔታ ለመፍጠር ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ማስታወሻ ፡- በዚህ ሰነድ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ ለሴትም ጭምር ያገለግላል፡፡

# ስለክለቦች፣ ፕሮጀክቶችና ልዩ ልዩ ቡድኖች አመሠራረት፣ መዋቅርና ምዝገባ

# አንቀጽ 4

# የአትሌቲክስ ስፖርት ክለብ እና ልዩ ልዩ ቡድን ስለመመስረት

1. የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች እና ልዩ ልዩ ቡድኖች በመኖሪያ አካባቢና ከተሞች፣ በድርጅቶች፣ በፋብሪካዎች እና በትምህርት ተቋማት እንዲሁም በማሰልጠኛ ማዕከላት ስፖርቱን ለድጋፍ ወይም ለንግድ (ለትርፋማነት) በሚጠቀሙ ባለሐብቶች ወይም ድርጅቶች ወይም ተቋማት ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡
2. የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማስፋፋትና ለማልማት የተለያዩ የቡድን አደረጃጀቶችን መፍጠር አስፈላጊ ሲሆን የክለቦችና የልዩ ልዩ ቡድኖች አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

   2.1 የክለቦች አደረጃጀት

      2.1.1 1ኛ ዲቪዚዮን ክለብ

      2.1.2 2ኛ ዲቪዚዮን ክለብ

      2.1.3 የአማተር ቡድን

   2.2 የፕሮጀክቶችና ልዩ ልዩ ቡድኖች አደረጃጀት

      2.2.1 የክፍለ ከተማው ዋና ቡድን

      2.2.2 የክፍለ ከተማው ተስፋ ቡድን

      2.2.3 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሮጀክት ቡድን

      2.2.4 የስፖርት ኮሚሽን ፕሮጀክት ቡድን

      2.2.5 የከተማው ምርጥ ቡድን

# አንቀጽ 5
# የስፖርት ክለብን ስለመመስረት

1. ማንኛውም በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚቋቋም ወይም የሚመሰረት ክለብ ተጠሪነቱ ለአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሆኖ የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ኮሚሽን ያወጣውን የክለቦች አመዘጋገብ ደንብና ከዚህ በታች የተጠቀሱትን መመዘኛ መስፈርቶች አሟልቶ ሲቀርብ ተመዝግቦ ፍቃድ ያገኛል፡፡

ሀ. የመቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ፤

ለ.ቀደም ሲል ሌሎች ክለቦች ያልተጠሩበት መጠሪያ ስም፣ አርማና በቀለሙ ተመሳሳይነት ያለው የመወዳደሪያ ማሊያ፤

ሐ. የክለብ ስራ አስኪያጅ እና ቋሚ የጽ/ቤት አድራሻ ያለው፡- (ያለበት ቦታ ስም፣ የቤት ቁጥር፣ የስልክ ቁጥርና ኢሜል የመሳሰሉት መረጃዎች ያሉት)፤

መ. የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ቢቻል በባለቤትነት ወይም በኪራይ ወይም በትውስት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሠ. መሠረታዊ የስልጠና ቁሳቁስ ያሟላ፤

ረ. በፌዴሬሽኑ የተረጋገጠ ህጋዊ የሆነ የአሠልጣኝነት ማስረጃ ያላቸው ቢያንስ ሁለት ባለሙያዎች ያሉትና ከክለቡ ጋር ውል የፈፀሙበትን የስምምነት /የቅጥር/ ማስረጃ የሚያቀርብ፤

ሰ. ሕጋዊ በሆነ መልኩ የተመዘገቡና መዋጮ /ድጋፍ/ ሊያደርጉ የሚችሉ ደጋፊ አባላት ያሉት፤

ሸ. በስሙ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስረጃ ማቅረብ የቻለ፤

ቀ. የሚይዛቸው አትሌቶች በሁለቱም ፆታ ቢያንስ 25 /ሃያ-አምስት/ ሆነው <u>በመምና በሜዳ ተግባራት ተወዳዳሪ አትሌቶችን ያቀፈ</u> እና የአትሌቶቹን የውል ስምምነት ፌዴሬሽኑ ባዘጋጀው ቅጽ /ፎርማት/ መሠረት አዘጋጅቶ የሚያቀርብ፤

በ. የአገር አቀፉንና የከተማ አስተዳደሩን አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም የሚያስተላልፏቸውን ውሳኔዎች የሚቀበል ስለመሆኑ በጽሑፍ ማረጋገጥ የሚችል፤

ተ. ክለቡ የሚይዛቸው አትሌቶች ስርጭት ቢያንስ በሂደት በታዳጊ፣ በወጣትና በአዋቂ ዕድሜ ቡድን ያዋቀረ ወይም ለማዋቀር የተዘጋጀ፤

## <u>አንቀጽ 6</u>

## <u>የስፖርት ክለቦች መዋቅር</u>

የሀገሪቱ የስፖርት ፖሊሲ እንዳስቀመጠው ስፖርቱ ሕዝባዊ መሠረት እንዲኖረው የአትሌቲክስ ስፖርት ክለቦች መዋቅር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ያሟሉ ሊሆን ይገባል፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም የሥራ አመራር ቦርድ
3. ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች
4. የክለብ ፅ/ቤት ኃላፊ፣ የቴክኒክ ባለሞያ (ዳይሬክተር)፣ አሠልጣኞች፣ አትሌቶች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## <u>አንቀጽ 7</u>

## <u>ስለ ክለቦች የምዝገባ ሂደት</u>

1. ክለቦች <u>በአንቀጽ 4 ቁጥር 1</u> ስር የተጠቀሱትን የመቋቋሚያ መስፈርቶች አሟልተው ሲገኙ በሚከተለው አኳኋን ክለባቸውን በማቋቋም ይመዘገባሉ፡፡

2. የመቋቋሚያ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ ክለቦች ለፌዴሬሽኑ የምዝገባ ጥያቄ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ድረስ በፅሑፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ጥያቄው ሲቀርብ ፌዴሬሽኑ ክለቡ በመስፈርቱ መሠረት የሚጠበቅበትን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ይመዘግባል፤
4. ፌዴሬሽኑም ክለቡ መመዝገቡን የሚገልጽና ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ መሳተፍ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ለክለቡና ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በመላክ ያሳውቃል፡፡
5. የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጀው የውድድር ሥርዓት ክለቡ <u>ለሦስት ዓመት ከቆየ በኋላ</u> ያለውን የብቃት ደረጃ በማሳደግ በዓመቱ መጨረሻ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የመወዳደር ጥያቄ በከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በኩል ለአገር አቀፍ ፌዴሬሽኑ ማቅረብ ይችላል፡፡
6. የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በበጀት ዓመቱ ውስጥ የክለቡን ዓመታዊ ክፍያ፣ የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት፣ የተወዳዳሪ አትሌቶችን ተሳትፎ፣ ስፖርቱን ለማሳደግ የያዛቸውን ዕቅዶች፣ የውድድር ላይ ብቃትና ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ዕውቅና እንዲሰጥ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ይልካል፡፡
7. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የቀረቡለትን መመዘኛዎች ከመረመረ በኋላ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መልስ በመስጠት ለክለቡ የውድድር እውቅና ይሰጣል፡፡

## <u>አንቀጽ 8</u>

## <u>የክለቦች ተግባርና ኃላፊነት</u>

በአንቀጽ 4 ቁጥር 1 ሥር የተቀመጠላቸውን መመዘኛ መስፈርቶች በማሟላት የሚመሠረቱ ክለቦች የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉባቸው፡-

1. በፌዴሬሽኑ የክለቦች መቋቋሚያ መመሪያ መሠረት የመቋቋም ግዴታ፤
2. በፌዴሬሽኑ ዕውቅና የተሰጣቸው በቂና ከአትሌቶች ብዛት ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ አሠልጣኞችን የመቅጠር ኃላፊነት፤
3. ለቀጠራቸው አትሌቶች አስፈላጊውን ዘመናዊና ሳይንሳዊ ስልጠና እንዲሁም የትራንስፖርት፣ የምግብና ንጹሕ የመጠጥ ውሃ፣ የደመወዝ፣ የትጥቅና የመሳሰሉትን የግብአት አቅርቦቶች የማሟላት ግዴታ፤

4. የአትሌቶችን ስልጠና የመደገፍና የመከታተል፣ ውጤታማነታቸውንም የማረጋገጥ ኃላፊነት፤
5. የውል ጊዜያቸውን የጨረሱና ከክለቡ ጋር መቀጠል ለማይፈልጉ አትሌቶች በወቅቱ መልቀቂያ የመስጠት ግዴታ፤
6. የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽንም ሆነ ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጇቸው ውድድሮች ላይ አትሌቶችን የማሳተፍ ኃላፊነት፤
7. ከክለቡ ጋር ስምምነት የፈጸሙበትን አንድ የውል ቅጂ/ኮፒ/ ለአትሌቶች በወቅቱ የመስጠት ተግባርና ኃላፊነቶች አለባቸው፡፡

# አንቀጽ 9

# የክለቦች ደረጃ መስጫ መስፈርቶች

ከታች በተዘረዘሩት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ ጤናማ የፉክክር መድረክ በመፍጠር የጥራት ደረጃቸውን በሂደት ለማሳደግ ታሳቢ ያደረገ ለክለቦች ደረጃ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የከተማው ክለቦች በሦስት ደረጃዎች ተከፍለው ተቀራራቢ የመዋቅር ደረጃ ላይ የሚገኙት በተመሣሣይ የውድድር ሥርዓት የሚወዳደሩበትን ምቹ ሁኔታና ሥርዓት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከታች በተዘረዘሩት መመዘኛ መስፈርቶች መሠረት ክለቦች ተመዝነው በሦስት ደረጃ ማለትም በ1ኛ ዲቪዚዮን፣ በ2ኛ ዲቪዚዮንና በአማተር ቡድን የሚመደቡ ሲሆን በየደረጃው የተገለጹትን መስፈርቶች ባሟሉት ልክ በሚመጥኑበት ደረጃ ተመድበው የሚመዘገቡና የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡

1. **የ1ኛ ዲቪዚዮን ክለብ ደረጃ መመዘኛ መስፈርቶች፡-**
   ሀ. የክለቦችን መቋቋሚያ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ያሟላ፤
   ለ. ቢቻል መሠረታዊ ቁሳቁሶችን ያሟላ ማለት የአትሌቶች መኖሪያ ካምፕ ያለው ወይም ቢያንስ በራሱ መንገድ ለአትሌቶች መኖሪያ ልዩ ድጋፍ ማድረግ የሚችል፤
   ሐ. ለአትሌቶች በቂ ደመወዝ ከመክፈል በተጨማሪ የምግብና ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ያለው፤
   መ. መሠረታዊ የሆነ የማዘውተሪያ ሥፍራ ያለው ወይም በኪራይና በትውስት የሚጠቀም፤
   ሠ. መሠረታዊ የሆኑ የአትሌቲክስ ስፖርት የልምምድ ቁሳቁሶችን ያሟላ፤
   ረ. በሦስቱም የውድድር ዓይነቶች (ተግባሮች) አትሌቶችን የያዘ፤

ሰ. 50 /ሃምሳ/ እና ከዚያ በላይ አትሌቶችን የያዘና አሰልጣኝ ለአትሌት ምጥጥን ቢያንስ አንድ አሰልጣኝ ለ15 አትሌቶች የመደበ፤

ሸ. በብሔራዊ ፌዴሬሽኑና በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ የአሰልጣኝነት ሙያ ስልጠና በመውሰድ ዕውቅና ያላቸው አሰልጣኞች ያሉት፤

ቀ. መሠረታዊ የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎችና ሠራተኞች ያሉት፤

2. ከላይ በተዘረዘሩት መመዘኛ መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያሟሉ በ1ኛ ዲቪዚዮን ክለብ ደረጃ ተመድበው የሚመዘገቡና የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡

3. የአንደኛ ዲቪዚዮን ክለቦች በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ክለቦች ጋር የሚወዳደሩ ሲሆን ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በማሳወቅ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ ሚኒማ ያሟሉ አትሌቶችን በመያዝ በቀጥታ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

4. **የ2ኛ ዲቪዚዮን ክለብ ደረጃ መመዘኛ መስፈርቶች፡-**

ሀ. የክለቦችን መቋቋሚያ መስፈርት ሙሉ በሙሉ ያሟላ፤

ለ. ከደመወዝ በተጨማሪ የምግብና ንጹሕ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ያለው፤

ሐ. መሠረታዊ የሆኑ የአትሌቲክስ የልምምድ ቁሳቁሶችን ያሟላ፤

መ. የሚይዛቸው አትሌቶች በሁለቱም ፆታ ቢያንስ 30 /ሠላሳ/ ሆነው በመምና በሜዳ ተግባራት ተወዳዳሪ አትሌቶችን ያቀፈ፤

ሠ. 30 /ሠላሳ/ እና ከዚያ በላይ አትሌቶችን ይዞ አሰልጣኝ ለአትሌት ምጥጥን ቢያንስ አንድ አሰልጣኝ ለ15 አትሌቶች የመደበ፤

ረ. ሕጋዊ የሆነ የአሰልጣኝነት ሙያ ስልጠና ወስደው ማስረጃ ያላቸው አሰልጣኞችን የያዘ፤

ሸ. ቢቻል የወጌሻ ባለሙያ ያለው፤

5. ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛ መስፈርቶች የሚያሟሉ ክለቦች በ2ኛ ዲቪዚዮን ክለብ ደረጃ ተመድበው የሚመዘገቡና የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡

6. የ2ኛ ዲቪዚዮን ክለቦች በከተማ አቀፍ ውድድር በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ክለቦች ጋር የሚወዳድሩ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱም ፈቃድ ሲያገኙ ብቻ የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ ሚኒማ ያሟሉ አትሌቶችን በመያዝ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

7. ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው መደበኛ የውድድር ዓይነቶች ማለትም በማራቶን፣በግማሽ ማረቶን፣ በክለቦች ሻምፒዮና በአገር አቋራጭ እና በማራቶን ሪሌ በዓመቱ መጨረሻ

ድምር ውጤት መሠረት በ1ኛ ዲቪዚዮን ሲወዳደሩ ከነበሩበት ደረጃ በውጤት መጨረሻ ላይ የሚገኝ ክለብ በቴክኒክ ኮሚቴዉ ዉሳኔ መሠረት ወደታችኛው ዲቪዚዮን የሚወርድ ሲሆን ከ2ኛ ዲቪዚዮን ውጤታማ የሆነና የአደረጃጀት ብቃቱ አስተማማኝ ሁኔታ ላይ የሚገኝ አንድ ክለብ በምትኩ ወደ ላይ የሚወጣ ይሆናል፡፡

8. ከ2ኛ ዲቪዚዮን በውጤቱ መሠረት ወደ 1ኛ ዲቪዚዮን የገባው ክለብ ከፌዴሬሽኑ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) የማበረታቻ ገንዘብ ድጐማ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም ግን ድጐማው የሚሰጠው በቀጣዩ የውድድር ዘመን አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቶና ተመዝግቦ ወደ ውድድር መግባቱ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡

9. **የአማተር ቡድን ደረጃ መመዘኛ መስፈርቶች፡-**
   - ሀ. የራሱ የሆነ የመመስረቻ እና የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ እና የአሠራር መመሪያ ያለው፤
   - ለ. ከከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በደረጃው የመቋቋምና የመደራጀት ፍቃድ አግኝቶ የተቋቋመ፤
   - ሐ. ሕጋዊ የሆነ የአሰልጣኝነት ሙያ ስልጠና ወስደው ማስረጃ ያላቸው አሰልጣኞች ያሉት፤
   - መ. በሁለቱም ፆታ ቢያንስ 15 /አስራ አምስት/ አትሌቶችን የያዘ፤
   - ሠ. የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም፣ አርማ እና የባንክ አካውንት ያለው፤ መሆኑ ሲረጋገጥ በዚህ ደረጃ ተደራጅቶ መቋቋምና ተመዝግቦ መወዳደር ይችላል፡፡

10. የአማተር ቡድን በተመሳሳይ የብቃት ደረጃ ላይ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር የሚወዳድር ሲሆን ክፍለ-ከተሞችና ወረዳዎች በሚያዘጋጁት ውድድር ላይ ግን በቀጥታ የሚሳተፍ ይሆናል፡፡ እንደአስፈላጊነቱም ብቃታቸው እየተረጋገጠ የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው ልዩ ልዩ ውድድሮች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 10
## የከተማ እና የክ/ከተማ ቡድን ስለመመስረት

1. የአትሌቲክስ ስፖርት ቡድኖችና ፕሮጀክቶች በመኖሪያ አካባቢና ክ/ከተሞች፣ በድርጅቶች፣ በፋብሪካዎች እና በትምህርት ተቋማት ስፖርቱን ለድጋፍ ወይም ለንግድ (ለትርፋማነት) በሚጠቀሙ ባለሐብቶች ወይም ድርጅቶች ወይም ተቋማት ሊመሠረቱ ይችላሉ፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስር በመቋቋም ተመዝግበው የሚወዳደሩ ቡድኖች በአምስት ዋና ዋና መንገድ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡
3. እያንዳንዱ ክ/ከተማ አንድ ዋና እና አንድ ተስፋ ቡድን በባለቤትነት የማደራጀትና የመደገፍ ኃላፊነት አለበት፡፡
4. ከክፍለ-ከተማው አስተዳደር በጀት ተመድቦለት በሁሉም ክፍለከተሞች አንድ ዋና ቡድን እና አንድ ተስፋ ቡድን የሚቋቋም ይሆናል፡፡ ከስሩ የሚቋቋመው የተስፋ ቡድን በየዓመቱ ለዋናው ቡድን ከ5 ያላነሱ ተተኪዎችን የሚያቀርብ መሆን ይሆናል፡፡
5. በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ድጋፍ የተቋቋመው የአትሌቲክስ ፕሮጀክት ቡድን ባለበት ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ይህ ቡድን በየዓመቱ ተተኪዎችን ለክልሉ ምርጥ ቡድን የማብቃት ኃላፊነትና ተልዕኮ አለበት፡፡
6. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ከሚደግፈው የፕሮጀክት ቡድን በተጨማሪ የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስፖንሰር በማፈላለግ እና 30/ሰላሳ/ ሰልጣኞችን በመጨመር የሰልጣኞችን ብዛት በድምሩ 60 ማድረስና የተጨማሪ 30 ሰልጣኞችን ወጪ የሚሸፍን ይሆናል፡፡
7. ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ የተማከለውን የብሔራዊ ቡድን ስልጠና ወደ ክልል ያወረደው ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም እንደሌሎች ክልሎች ሁሉ የራሱን ዓመታዊ ምርጥ ቡድን ማደራጀት ይጠበቅበታል፤ ይህ ቡድን በዓመት 10 ወር /ከመስከረም እስከ ሰኔ ወር መጨረሻ ድረስ የሚቆይና በየዓመቱ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን/ እያንዳንዱ አትሌት በብቃት መለኪያ ተመዝኖና ተመርጦ በመሰባሰብ ተከታታይነትና ወጥነት ባለው ስልጠና የሚያዝና ከተማ አስተዳደሩን /ፌዴሬሽኑን/ ወክሎ በአገር አቀፍ ውድድሮች ላይ ይሳተፋል፡፡ ለዚህም እያንዳንዱ አትሌት ከፌዴሬሽኑ ጋር የአንድ ዓመት ውል የሚገባ ሲሆን ይህ ቡድን ከፌዴሬሽኑ በልዩ ሁኔታ የፋይናንስና የማቴሪያል (የበጀት) ድጋፍ ይደረግለታል፡፡
8. ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪም የክልሉን ምርጥ ቡድን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድየተሻለ የበጀት አቅም ያለው የአንደኛ ዲቪዚዮን ክለብ እንደጊዜያዊ አማራጭ ለመጠቀም ይረዳ ዘንድ ቢያንስ 5 /አምስት/ አትሌቶችን በመያዝና በማብቃት (የትራንስፖርት፣ የምግብና የስልጠና ድጋፍ በመስጠት) ለከተማ አስተዳደሩ ምርጥ ቡድን አስተዋጽዖ ማድረግ የሚችልበት መንገድና ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡
9. በየክፍለከተማው የተቋቋሙ የአትሌቲክስ ፕሮጄክት ቡድኖች የተደራጁት በአዲስ አበባ ከተማ ስፖርት ኮሚሽን ባለቤትነት ሲሆን ለነዚህ የፕሮጄክት ቡድኖች ፌዴሬሽኑ

ሙያዊ ድጋፍ የመስጠትና የመከታተል ሚና ይኖረዋል፡፡ የፌዴሬሽኑ ሚና ይህ ብቻ ከሚሆን ይልቅ በከተማው ስፖርት ኮሚሽን ተይዞ የሚመራው የአትሌቲክስ ስፖርት ፕሮጀክት ከነበጀቱ ወደ ፌዴሬሽኑ ወርዶ የ10ሩም ክ/ከተሞች ፕሮጀክት በፌዴሬሽኑ ቁጥጥር ስር የሚውልበት ሁኔታ የሚመቻች ይሆናል፡፡

10. ልዩ ልዩ የክፍለከተማ ቡድኖችና የፕሮጀክት ስልጠና ጣቢያዎች በተመሳሳይ ደረጃ ተዋቅረው ከሚገኙ ቡድኖች ጋር የሚወዳድሩ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ በየደረጃው ባሉ የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እንዲሁም የብሔራዊ ፌዴሬሽኑ አደረጃጀቶች በሚያዘጋጁት ውድድሮች ላይ የተቀመጠውን ሚኒማ ካሟሉ የሚሳተፉ ይሆናል፡፡
11. ከላይ ስለተዘረዘሩት ልዩ ልዩ ቡድኖች የአደረጃጀትና የአሠራር ሂደት የስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ በጋራ ከፀደቀ በኋላ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል፡፡
12. ማንኛውም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚቋቋም የአትሌቲክስ ስፖርት ቡድን፡- ከዚህ የሚከተሉትን መመዘኛዎች ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡

ሀ. የመቋቋሚያና መተዳደሪያ ደንብ፤

ለ. ቀደም ሲል ሌሎች ፕሮጀክቶች ወይም ሌሎች ቡድኖች ያልተጠሩበት መጠሪያ ስም፣ አርማና በቀለሙ ተመሳሳይነት ያለው የመወዳደሪያ ማሊያ ያለው፤

ሐ. የስራ አስኪያጅ ወይም ቡድን አስተባባሪ እና ቋሚ የጽ/ቤት አድራሻ ያለው፡- (ያለበት ቦታ ስም፣ የቤት ቁጥር፣ የስልክ ቁጥር የመሳሰሉት መረጃዎች ያሉት)፤

መ. ቢቻል የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ በባለቤትነት ወይም በኪራይ ወይም በትውስት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሠ. መሠረታዊ የስልጠና ቁሳቁስ ያሟላ፤

ረ. ፌዴሬሽኑ የተረጋገጠ ህጋዊ የሆነ የአሠልጣኝነት ማስረጃ ያላቸው ቢያንስ ሁለት ባለሙያዎች ያለው፤

ሰ. በስሙ የባንክ ሂሳብ በመክፈት ማስረጃ ማቅረብ የቻለ፤

ሸ. ህጋዊ በሆነ መልኩ የተመዘገቡና መዋጮ /ድጋፍ/ ሊያደርጉ የሚችሉ ደጋፊ አባላት ያሉት፤

ቀ. የሚይዛቸው አትሌቶች በሁለቱም ፆታ ቢያንስ 25 /ሃያ አምስት/ ሆነው <u>በመምና በሜዳ ተግባራት ተወዳዳሪ አትሌቶችን ያቀፈ፤</u>

በ. የከተማ አስተዳደሩን ፌዴሬሽን መተዳደሪያ ደንቦችና የሚያስተላልፏቸውን ውሳኔዎች የሚቀበል ስለመሆኑ በጽሑፍ ማረጋገጥ የሚችል፤

ተ. ቡድኑ የሚይዛቸው አትሌቶች ስርጭት ቢያንስ በሂደት በታዳጊ፣ በወጣትና በአዋቂ የዕድሜ እርከን ቡድን ያዋቀረ ወይም ለማዋቀር የተዘጋጀ፤

## አንቀጽ 11

## የክ/ከተሞች ዋና እና ተስፋ-ቡድን መዋቅር

የአትሌቲክስ ስፖርት ቡድኖች መዋቅር ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች ያሟላ ሊሆን ይገባል ፡፡

1. ጠቅላላ ጉባኤ
2. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም የሥራ አመራር ቦርድ
3. ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችና ንዑሳን ኮሚቴዎች
4. የፕሮጀክቱ(የቡድኑ) ጽ/ቤት ኃላፊ፣ ቴክኒክ ኮሚቴ/ባለሞያ/፣ አሠልጣኞች፣ አትሌቶች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## አንቀጽ 12

## ስለ ልዩ ልዩ ቡድኖች የምዝገባ ሂደት

1. ቡድኖች በአንቀጽ 11 ቁጥር 12 የቅድሚያ መቋቋሚያ መስፈርቶችን አሟልተው ሲገኙ በሚከተለው አኳኋን ክለባቸውን በማቋቋም ይመዘገባሉ፡፡
2. የመቋቋሚያ መመዘኛዎችን የሚያሟሉ የክፍለከተማ ቡድኖች በአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የምዝገባ ጥያቄ ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም 30 ድረስ በፅሁፍ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. የከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም በቀረበለት ጥያቄ መሠረት ቡድኑ በመስፈርቱ መሠረት የሚጠበቅበትን ማሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ ይመዘግባል፤
4. የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽን ቡድኑ መመዝገቡን የሚገልጽና ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ መሳተፍ የሚችል መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡
5. ከተማ አስተዳደሩ በሚያዘጋጀው የውድድር ሥርዓት ቡድኑ ለሦስት ዓመት ከቆየ በኋላ ያለውን የብቃት ደረጃ በማሳደግ በዓመቱ መጨረሻ በአንደኛ ዲቪዚዮን ክለብ ደረጃ ተመዝግቦ ለመወዳደር በክ/ከተማው ስፖርት ፌዴሬሽን በኩል ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
6. የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽን በበጀት ዓመቱ ውስጥ የቡድኑን ዓመታዊ ክፍያ፣ የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት፣ የተወዳዳሪ አትሌቶች ተሳትፎ፣ ስፖርቱን ለማሳደግ የያዛቸው

ዕቅዶች፣ የውድድር ብቃትና ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟላ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ በአንደኛ ዲቪዚዮን ክለብነት ተመዝግቦ እንዲወዳደር ዕውቅና ይሰጣል፡፡

7. በአንደኛ ዲቪዚዮን ክለብነት ተመዝግቦ በከተማ አቀፍ ውድድር እየተወዳደረ የሚገኝ የክፍለከተማ ቡድን ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ የመሳተፍ መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የከተማ አስተዳደሩ ስፖርት ፌዴሬሽን በወቅቱ የሚያወጣውን መመሪያ ተፈጻሚ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ 13

## የዋና እና የተስፋ-ቡድን ኃላፊነትና ግዴታ

በአንቀጽ 12 ቁጥር 13 ሥር የተቀመጠላቸውን መመዘኛ መስፈርት በማሟላት የሚመሠረቱ የአትሌቲክስ ስፖርት ቡድኖች የሚከተሉት ኃላፊነቶችና ግዴታዎች አለባቸው፡-

1. በከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የስፖርት ቡድኖች መቋቋሚያ መመሪያ መሠረት የመቋቋም፤
2. በፌዴሬሽኑ ዕውቅና የተሰጣቸው በቂና ተመጣጣኝ አሠልጣኞችን የመቅጠር፤
3. አስፈላጊውን የስልጠና፣ የትራንስፖርት፣ የላብ መተኪያ(የምግብና የውሃ)፣ የደመወዝ፣ የትጥቅና የመሳሰሉትን የግብአት አቅርቦቶች የማሟላት፤
4. የአትሌቶችን ስልጠና የመደገፍና የመከታተል፣ ውጤታማነታቸውንም የማረጋገጥ፤
5. የውል ጊዜያቸውን የጨረሱና ከቡድኑ ጋር መቀጠል ለማይፈልጉ አትሌቶች በወቅቱ መልቀቂያ የመስጠት፤
6. የክፍለከተማው እና የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ አትሌቶችን የማሳተፍ፤
7. ከቡድኑ ጋር ስምምነት የፈጸሙበትን አንድ የውል ኮፒ ለአትሌቶች በወቅቱ የመስጠት ኃላፊነትና ግዴታዎች አለባቸው፡፡

## ስለ አትሌቶች ቅጥር፣ምዝገባና ዕድሳት፣ ተገቢነትና የዝውውር ሂደት

## አንቀጽ 14

## የአትሌት ቅጥር፣ ምዝገባና ዕድሳት ሂደት

1. ማንኛውም ክለብ የራሱ የብቃት መመዘኛ መስፈርት በማውጣት የፈለገውን አትሌት መመልመልና መቅጠር ይችላል፡፡

2. በአትሌቱ እና በክለቡ መካከል የሚደረገው የጋራ ውል ስምምነት ከ ---- እስከ ------ በሚል ጊዜው ተጠቅሶ በውል ስምምነት ፊርማ ይፈፀማል፤ ይህ የስምምነት ውል ሕጋዊ ሆኖ በሥራ ላይ የሚውለው በአ/አበባ ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሲፀድቅ ብቻ ይሆናል፤
3. በአትሌቱና በክለቡ መካከል የሚደረገው የጋራ የውል ስምምነት ዘመን በውሉ ላይ የሚገለጽ ሆኖ አትሌቱ በግልጽ በሚገባው ቋንቋ ተተርጉሞለት በመፈራረም ይፈጸማል፡፡
4. አንድ አትሌት ከአንድ ክለብ ጋር ስምምነት ካደረገ በኋላ የውል ስምምነቱ በሦስት ኮፒ ተሰርቶ በአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሲጸድቅ አንደኛው ኮፒ ለፌዴሬሽኑ፣ ሁለተኛው ኮፒ ለአትሌቱ፣ ሦስተኛው ኮፒ ለክለቡ ከተሰጠ በኋላ ውሉ በስራ ላይ ይውላል፡፡
5. ውሉ የሚፈጸመው እድሜያቸው ከ18 አመት በታች ካሉ አትሌቶች ጋር ከሆነ የውል ስምምነቱ ሊፈጸም የሚችለው ከወላጅ አባት ወይም እናት ወይም ህጋዊ ውክልና ከተሰጠው አካል ጋር መሆን ይኖርበታል፡፡
6. በአትሌቱና በክለቡ መካከል የተደረገውን ውል ሁለቱም አካሎች በጋራ ተስማምተው ማፍረስ ይችላሉ፡፡ ይህንንም ጉዳይ የሁለቱንም ተዋዋዮች ፊርማና የክለቡን ማህተም በማድረግ ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አቅርበው ሲፈቀድላቸው ለውል ማፍረሻ እያንዳንዳቸው ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በመክፈል ውላቸውን ማፍረስ ይችላሉ፡፡
7. ሁለቱም ተዋዋዮች በጋራ የተስማሙበትን ውል በአንደኛው ወገን ፍላጎት /ጥያቄ/ ብቻ ማፍረስ አይቻልም፡፡ ሆኖም ውሉ እንዲፈርስ የሚያስገድድ ሁኔታ ከተፈጠረ ውል አፍራሽ ውል ለፈረሰበት ወገን ቀደም ሲል የተደረገው ስምምነት እንደተጠበቀ ሆኖ ውል አፍራሹ ውል ለፈረሰበት ወገን ብር ከ10,000.00 (አሥር ሺህ) እስከ 20,000.00 (ሃያ ሺህ ብር) ካሣ በመክፈል ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡ በተጨማሪ ጉዳዩን ለሚያስፈጽመው ፌዴሬሽን የአገልግሎት ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ከፍሎ ውሉን ሊያቋርጥ ይችላል፡፡
8. ሁለቱ ተዋዋዮች ውላቸውን ጨርሰው እንደገና ለማደስ ከፈለጉ ከላይ በተ.ቁ. 2 ላይ በተገለጸው መሠረት የሁለቱን ተዋዋዮች የስምምነት ውል በክለቡ ማህተም አስደግፎ ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በማቅረብ ውሉን ማሳደስ ይቻላሉ፡፡

9. አንድ አትሌት ከክለቡ ጋር በገባው ውል መሠረት ማግኘት የሚገባውን ደመወዝና ጥቅማጥቅም ካጣና ሁኔታውን ለፌዴሬሽኑ ካሳወቀ፣ ፌዴሬሽኑ ሁኔታውን ካጣራ በኋላ በደንቡ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
10. አንድ አትሌት በአንድ የውድድር ዓመት ለሁለት ክለቦች ፈርሞ ተገቢነት ተሰጥቶት ሲወዳደር ቢገኝ አትሌቱ ብር 5,000.00 (አምስት ሺህ ብር) የሚቀጣ ሲሆን ተገቢነቱ ቀድሞ ለፈረመበት ክለብ ይሆናል፡፡ ተገቢነት በሌለው ክለብ ተመዝግቦ በውድድሩ ያስመዘገበው ውጤትም በሙሉ ይሰረዛል፤ ተገቢነቱን ሳያረጋግጥ መዝግቦ ያወዳደረ ክለብም ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ይቀጣል፡፡
11. አንድ አትሌት ከነበረበት ክለብ ጋር በዘመኑ የገባውን ውል ፈጽሞ በዛው በነበረበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ሌላ ክለብ ለመመዝገብ ከፈለገ ከነበረበት ክለብ የሚሰጠው የመልቀቂያ ደብዳቤ በማቅረብ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ከሌላ ክልል/ከተማ አስተዳደር የመጣ ከሆነ ከክልሉ/ከከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መልቀቂያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
12. አንድ አትሌት ከክለቡ ጋር የተስማማው በመደበኛ የሥራ ቅጥር ውል ከሆነ ውሉ የሚፀናው በመስሪያ ቤቱ ደንብና ሥነ-ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡
13. አንድ አትሌት ከክለቡ ጋር የተስማማው ያለምንም የደመወዝ ክፍያ ከሆነ ውሉ ሊፀና የሚችለው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል፡፡
14. አንድ አትሌት ከክለቡ ጋር የሚያደርገው ስምምነት በደመወዝ ክፍያ ከሆነ ውሉ ሊፀና የሚችለው ሁለቱ ወገኖች በሚያደርጉት የጊዜ ስምምነት ይሆናል፡፡
15. ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በጋራ ያደረጉት የውል ዘመን ስምምነት ከተጠናቀቀ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውሉ ይፈርሳል፡፡
16. የአትሌቶችን የዝውውር ሂደት የሚፈቅደውና የሚያጸድቀው የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ብቻ ነው፡፡
17. አንድ አትሌት ከክለቡ/ከቡድኑ/ ጋር የሚኖረው የውል ስምምነት ከአንድ እስከ አራት ዓመት ሊደርስ ይችላል፤ ሆኖም በክለቡ እና በአትሌቱ ስምምነት መሠረት ውሉን በየዓመቱ ማደስ ይቻላል፡፡

18. አንድ የአትሌቲክስ ክለብ በውድድር ዘመኑ የተወሰነውን የምዝገባና የዕድሳት ክፍያ ለአንደኛ ዲቪዚዮን ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/፣ ለሁለተኛ ዲቪዚዮን ብር 2,000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ በመክፈል ለመጀመሪያ ጊዜ ከሐምሌ 01 ቀን የመጀመሪያው ሰኞ ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን ባሉት የሥራ ቀናት ውስጥ ተመዝግቦ በወቅቱ ቴሴራ ማሳደስ ይኖርበታል፤ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይመዘገብ ቢቀር እስከ ጥቅምት 30 ቀን ድረስ ብቻ ባሉት የሥራ ቀናት ከመደበኛው ክፍያ በተጨማሪ የቅጣት ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በመክፈል ክለቡን በማስመዝገብ ቴሴራና ውል ማሳደስ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ሳይመዘገብ ቢቀር ክለቡ እንደፈረሰ ተቆጥሮ በስሩ የነበሩ አትሌቶችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደፈለጉበት ክለቦች ገብተው ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡
19. አንድ የአትሌቲክስ ክለብ በውድድር ዘመኑ የተወሰነውን የምዝገባና የዕድሳት ክፍያ ከፍሎ ወደ ውድድር ከገባ በኋላ ለሁለተኛ ዙር የአትሌት ምዝገባና የቴሴራ ዕድሳት ፌዴሬሽኑ የክለቦችን አትሌቲክስ ሻምፒዮና ካጠናቀቀ በኋላ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ከአትሌቶች ጋር ውል ተዋውሎ ማስመዝገብና ቴሴራ ማሳደስ ይችላል፡፡
20. ከላይ በተራ ቁጥር 18 እና 19 ላይ ከተጠቀሰው የጊዜ ገድብ ውጪ ቴሴራ የሚያሳድስ ክለብ በአንድ ቴሴራ ብር 50.00 /ሃምሳ ብር/ እየከፈለ ማሳደስ ይችላል፡፡ ቴሴራ የሚታደስበት ፕሮግራም በተመለከተ በፌዴሬሽኑ የጽ/ቤት ኃላፊ የሚወሰን ሲሆን በሳምንት አንድ ቀን በሚመደበው ሰዓት መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡
21. ከላይ በተራ ቁጥር 19 እና 20 ላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ አንድ ክለብ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውጪ የሆነና ከሌላ ክልል/ከተማ አስተዳደር ወደ አዲስ አበባ የሚመጣን አትሌት መቅጠር ቢፈልግ አትሌቱ ከመጣበት ክለብ ወይም ክልል የተሰጠ ግልጽ መልቀቂያ በመያዝና የመመዝገቢያ ብር 50.00 /ሃምሳ ብር/ በመክፈል ማስመዝገብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 15
## የአትሌት ተገቢነትና የዝውውር ሂደት

1. አንድ አትሌት በአንድ የውድድር ዘመን ተገቢነት የሚያገኘው በፍቃደኝነት ቀድሞ ለፈረመበት ክለብ ወይም ቡድን ብቻ ነው፡፡

2. አንድ አትሌት በአንድ የውድድር ዘመን ለሁለት ክለቦች ተመዝግቦና ፈርሞ (ተዋውሎ) የተገኘ አትሌት በዲሲፒሊን ደንቡ መሠረት ይቀጣል፡፡ (በውድድሩ ያስመዘገበው ውጤት ይሰረዛል፤ እንደጥፋቱ ክብደትና ቅለት ከ3 ውድድር እስከ 2 ዓመት ከማንኛውም ውድድር ይታገዳል፤ በተጨማሪም እስከ 3,000 ብር የሚደርስ ገንዘብ ይቀጣል፤) ሆኖም በተገቢነት ጥያቄ ላይ የተነሳ አቤቱታ ተገቢነት የሚኖረው በዘመኑ በቅድሚያ ለፈረመበት ክለብ ይሆናል፡፡
3. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚከናወን የአትሌቶችን ዝውውር ሂደት የሚፈቅደውና የሚያፀድቀው የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ነው፡፡
4. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኝ አንድ ክለብ የሌላውን ክለብ ወይም ፕሮጀክት አትሌት የውል ዘመኑ ከማለቁ በፊት በዝውውር ለመውሰድ ከፈለገ፡-
   ሀ. ከአንደኛ ዲቪዚዮን ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ለሚደረግ ዝውውር ብር 20,000.00 /ሃያ ሺህ ብር/፤
   ለ. ከሁለተኛ ዲቪዚዮን ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ ብር/፤
   ሐ. ሁለተኛ ዲቪዚዮን ወደ ሁለተኛ ዲቪዚዮን ለሚደረግ ዝውውር ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/፤
   መ. ከፕሮጀክቶች ወደ ክለቦች የሚደረግ ከሆነ ወደ አንደኛ ዲቪዚዮን ለሚደረግ ዝውውር ብር 3,000.00 /ሦስት ሺህ ብር/ እንዲሁም ወደ ሁለተኛ ዲቪዚዮን ለሚደረግ ዝውውር ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/፤
5. በተራ ቁጥር 6 ከሀ - መ የተጠቀሰው ክፍያ ተግባራዊ የሚሆነው፡-
   ሀ. ክለቡ የአትሌቱን የዝውውር ድርድር የሚያደርገው አትሌቱ ከነበረበት ክለብ እና ከአትሌቱ ጋር በስምምነት ሆኖ የስምምነቱ ሰነድ ለፌዴሬሽኑ ሲቀርብ፤
   ለ. አትሌቱ በዝውውር ከሄደበት ክለብ ከሚገኘው ክፍያ ውስጥ ቀድሞ ለነበረበት ፕሮጀክት ወይም ክለብ የባለቤትነት 80%፣ ውሉን ለሚያፀድቀው የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአገልግሎት ክፍያ 20% ሲከፍል ውሉ ይፀድቃል፡፡
6. የአትሌቶችን ተገቢነትና ዝውውር ጉዳይ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በይግባኝ የማየትና በጉዳዩ ውሳኔ የመስጠት ሙሉ ስልጣን አለው፡፡

## የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ፣ የክለቦች፣ የአትሌቶች ፣ የአሰልጣኞች ፣የቡድን መሪ እና የወጌሻዎች መብትና ግዴታ/ኃላፊነት/

## <u>አንቀጽ 16</u>

# የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ መብትና ግዴታ

## 16.1 የፌዴሬሽኑ መብት

1. የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ የአትሌቲክስ ውድድሮች ላይ ለመሳተፍ በስሩ ካደራጃቸው ክለቦችና ክ/ከተሞች አትሌቶችን በመመልመል የመጠቀም ሙሉ መብት አለው፡፡ ክለቦችም የተጠየቁትን አትሌት የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡
2. ክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች እና ክለቦች አብረው በሚወዳደሩበት ውድድር ወቅት ከክለቦች ወይም ከክ/ከተሞች አትሌቶች ውስጥ በደረጃ ከ1ኛ-5ኛ ካሉት ውስጥ ከተማ አስተዳደሩ አንዱን አትሌት መርጦ መውሰድ ይችላል፤ ነገር ግን ውድድሩ ክለቦችን የማያሳትፍ ከሆነና የክልሎች/የከተማ አስተዳደሮች ውድድር ብቻ ከሆነ በደረጃ ከ1ኛ-3ኛ ያሉትን አትሌቶች በመወሰድ ከተማ አስተዳደሩ ማወዳደር ይችላል፡፡
3. የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ክለቦችና ልዩ ልዩ ቡድኖች በደንቡ መሠረት ተግባራቸውን ለመወጣት ካልቻሉ ፍቃዳቸውን የመሰረዝ ስልጣን አለው፡፡

## 16.2. የፌዴሬሽኑ ግዴታ

162.1. የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሥሩ ተመዝግበው ፍቃድ በማግኘት ወደ ውድድር የገቡትን ክለቦች የስራ እንቅስቃሴ በየጊዜው ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

162.2. ክለቦች ከአትሌቶቻቸውና ከአሰልጣኞቻቸው ጋር የሚገቡትን ውል ያጸድቃል፣ ተፈጻሚነቱንም ይከታተላል፤

162.3. አትሌቶችም ሆኑ አሰልጣኞች ከክለቦቻቸው ጋር ለሚኖራቸው ማንኛውም ቅሬታ ለፌዴሬሽኑ አቤቱታ ቢያቀርቡ ፌዴሬሽኑ አቤቱታውን ተመልክቶ በፌዴሬሽኑ ደንብና መመሪያ መሠረት ውሳኔ ይሰጣል፤

16.2.4. አንድ ክለብ ከውስጠ-ደንቡ ውጪ በአትሌቶቹ የተለየ ጥቅም ለማግኘት ሲል ችግር ቢፈጥርና አቤቱታ ቢቀርብበት ጉዳዩን በማጣራት በአጥፊው ክለብ ላይ በዲሲፒሊን ደንቡ መሠረት ከቀላል ቅጣት እስከ ማገድ ርምጃ ይወሰድበታል፡፡

# አንቀጽ 17
# የስፖርት ክለብ መብት

1. የአትሌቶችን የውል ሰምምነትና ቴሴራዎች በፌዴሬሽኑ እንደጸደቀ ወዲያውኑ የማግኘት፤

2. አቤቱታዎችን ለፌዴሬሽኑ የማቅረብ፣ ወቅታዊ ምላሽና ውሳኔዎች የማግኘት፤
3. የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች የመሳተፍ፣ሽልማቶችን የማግኘት፤
4. የፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያዎች እንዲሁም የውድድር ፕሮግራሞች የማግኘት፣ በደንብና መመሪያዎች ላይ ማሻሻያ ሀሳብ የመስጠት፤
5. ከስፖርት ክለቡ አባላትና አትሌቶች ወርሃዊ ደመወዝ ላይ የሥራ ግብር ቀንሶ ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ የማድረግ፣
6. በዲሲፕሊን ጉድለት፣ በአቋም መዋዠቅ በስፖርት ክለቡ አባላት ላይ ደረጃ በደረጃ የሚወሰድውን ርምጃ ለፌዴሬሽኑ የማሳወቅ፣
7. በአሰልጣኞችና በአትሌቶች መካከል አለመግባበቶች ሲፈጠር በሰላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኝ የማድረግ፡፡
8. ህጋዊ መስመሩን ተከትሎ በደንቡና በመመሪያው መሰረት በአትሌቱ፣ በአሰልጣኞች፣ በማናጀሮችና በሌሎች አባላት ላይ አቤቱታ የማቅረብ፣
9. የፌዴሬሽኑን መመሪያዎች፣ ልዩ ልዩ ደብዳቤዎች እንዲሁም የውድድር ፕሮግራሞች በወቅቱ የማግኘት፣
10. መመሪያዎች ላይ የማሻሻያ ሐሳብ የመስጠት፤
11. ህጋዊ አካሄዱንና መስመሩን ተከትሎ በመመሪያው መሠረት በአትሌቶች፣ በአሰልጣኞች፣ በአመራሮችና በሌሎች አባላት ላይ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 18
## የስፖርት ክለብ ግዴታ

1. የአትሌቶችንና አስለጣኞችን መብት የመጠበቅ፣
2. በፌዴሬሽኑ የጸደቀውን የአትሌቶችና የባላሙያዎች ውል አንድ አንድ ኮፒ የመስጠት
3. የአትሌቶችን የዝውውር ክፍያ ለፌዴሬሽኑ የማሳወቅ፣ የክፍፍል ግዴታዎችን የማሟላት፣
4. ከፌዴሬሽኑ የሚላኩ ህጋዊ ደብዳቤዎችን የመቀበል፣
5. ስለ ፌዴሬሽኑ አደረጀጃጀትና አስራር ኢንፎርሜሽን ሲጠየቅ የመስጠት
6. የታገደ አባል ወይም አትሌትን አሳትፎ አለመገኘት፣
7. የክለቡን መመዝገቢያ ና ሌሎች ክፍያዎች በወቅቱ የማጠናቀቅ
8. ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚመረጡ አትሌቶችን የመስጠት
9. የአ/አበባ እና የሀገር አቀፉን ፌዴሬሽን ደንብና መመሪያዎች ለአሰልጣኞች፣ ለቡድን መሪ፣ ወጌሻና አትሌቶች የማሳወቅ፣

10. ለስፖርቱ የወጡትን ደንብና መመሪያዎች የማክበርና የማስከበር፣
11. ለክለቡ የአትሌቲክስ ቡድን አባላት የልምምድና የውድድር ስፖርት ትጥቆች የማሟላት፣
12. በገባው ውል መሠረት ለቡድኑ አባላት ወርሃዊ ደመወዝ የመክፈል፣
13. በልምምድና በውድድር ወቅት ለቡድኑ አባላት ምግብና ትራንስፖርት የማቅረብ፣
14. ለቡድኑ አባላት የ24 ሰዓት ኢንሹራንስ የመግባት፣
15. የውል አንድ ኮፒ ለሚመለከተው የመስጠት፣
16. በቡድኑ አባላት በየደረጃው የዲስፕሊን ርምጃ ሲወሰድ ፌዴሬሽኑን የማሳወቅ፣
17. ከፌዴሬሽኑ የሚላኩ የዲሲፕሊን እርምጃዎችንና ውሳኔዎችን ተቀብሎ የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡
18. ማንኛውም በአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስር የተመዘገበ ክለብ የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያዘጋጀውን መታወቂያ (ቲሴራ) የፌዴሬሽኑ ቴክኒክ ኮሚቴ በወቅቱ በሚወስነው የዋጋ ተመን መሠረት በመግዛት በሥራ ላይ ያውላል፡፡
19. አንድ የአትሌቲክስ ክለብ በውድድር ዘመኑ የተወሰነውን የምዝገባና የዕድሳት ክፍያ ለአንደኛ ዲቪዚዮን ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/፣ ለሁለተኛ ዲቪዚዮን ብር 2,000.00 /ሁለት ሺህ ብር/ በመክፈል ከሐምሌ 01 ቀን የመጀመሪያው ሰኞ ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን ባሉት የሥራ ቀናት ውስጥ ተመዝግቦ በወቅቱ ቴሴራ ማሳደስ ይኖርበታል፤ ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሳይመዘገብ ቢቀር እስከ ጥቅምት 30 ቀን ድረስ ብቻ ባሉት የሥራ ቀናት ከመደበኛው ክፍያ በተጨማሪ የቅጣት ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በመክፈል ቴሴራና ውል ማሳደስ ይችላል፡፡ ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ሳይመዘገብ ቢቀር ክለቡ እንደፈረሰ ተቆጥሮ በስሩ የነበሩ አትሌቶችም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ወደፈለጉበት ክለቦች ገብተው ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡
20. በውድድር ዘመኑ የተቋቋመ አዲስ ፍቃድ ጠያቂ ክለብ ሲፈቀድለት የመግቢያ ክፍያ ብር 500.00 /አምስት መቶ/ እና ለዓመታዊ ውድድር ምዝገባና ዕድሳት ብር 2,000 መክፈል አለበት፡፡
21. አንድ የሁለተኛ ዲቪዚዮን ክለብ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በዘመኑ ውድድር አልወዳደርም ብሎ ካመለከተና ምክንያቱም ተቀባይነት ካገኘ ለቀጣዩ ዓመት በነበረበት ደረጃ ተመዝግቦ መወዳደር ይችላል፡፡ ሆኖም በወቅቱ በነበረው የውድድር ውጤት መሠረት ወደ 1ኛ ዲቪዚዮን የወጣ ክለብ ከሆነ አቤቱታውና ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

22.ማንኛውም ተወዳዳሪ ክለብ በውድድር ጊዜ በዘመኑ የታደሠ መታወቂያ /ቴሴራ/ ይዞ ለውድድር መቅረብ አለበት፡፡ ቴሴራ ይዞ ያልቀረበ ክለብ በውድድሩ እንዲሳተፍ አይፈቀድለትም፡፡

23.አንድ ክለብ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ላይ የመሳተፍ ግዴታ ያለበት ሲሆን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለመወዳደር ባይችል ጉዳዩን በቅድሚያ ለፌዴሬሽኑ በጽሑፍ በማቅረብ ውሳኔ ያገኛል፡፡ በወቅቱ ካላሳወቀ በስነምግባር ደንቡ በመሠረት ተገቢው የዲሲፒሊን እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

24.ማንኛውም ሕጋዊ የአትሌቲክስ ክለብ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው መደበኛ ውድድሮች ላይ የመሳተፍ ግዴታ አለበት፡፡ ይህ ሳይሆን ሲቀር እንደውድድሩ ክብደትና ቅለት በዲሲፒሊን ደንቡ መሠረት ከብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ እስከ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ የሚደርስ ቅጣት ይወሰንበታል፡፡

25.አንድ ክለብ ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው ዓመታዊ መደበኛ ውድድሮች ላይ በአንዱ ላይ ሳይሳተፍ ቢቀር በቀጣዩ ውድድር ለመሳተፍ በቅድሚያ በቂ ምክንያት ለፌዴሬሽኑ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ ባይሆን ለውድድሩ የወጣውን ወጪ ማካካሻ ብር 5,000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ይቀጣል፡፡

26.ማንኛውም ክለብ ከአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር በገባው ስምምነት መሠረት የአትሌቶችንና የአሰልጣኞችን መብት የመጠበቅ፣ ግዴታዎችንም የማሟላት ኃላፊነት አለበት፡፡

27.በፌዴሬሽኑ የጸደቀውን የአትሌቶችና የባለሞያዎች የውል ስምምነት አንድ ቅጅ ለአትሌቱ ወይም ለባለሞያው በወቅቱ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

28.ማንኛውም ክለብ ለአትሌቶች ዝውውር የሚከፍለውን ክፍያ ለፌዴሬሽኑ በግልጽ የማሳወቅና የክፍፍል ግዴታዎችንም በአግባቡ የመፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

29.የውል ዘመናቸውን ያጠናቀቁ አትሌቶችና ባለሞያዎች የመልቀቂያ ወረቀት እንዲሠጣቸው ሲጠይቁ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በ10 ቀናት ውስጥ የመልቀቂያ ወረቀት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

30. ከፌዴሬሽኑ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በጊዜ ገደቡ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት፤

31.ፊርማና ማኅተም ያረፈባቸውን የፌዴሬሽኑን ሕጋዊ ደብዳቤዎች የመቀበል ግዴታ፤

32.ስለክለቡ አደረጃጀትና የውስጥ አሠራር ልዩ ልዩ መረጃዎች በፌዴሬሽኑ አካላት ሲጠየቅ ወዲያው የመስጠትና አስፈላጊውን ትብብር የማድረግ ግዴታ፤

33. በፌዴሬሽኑ የታገደ የክለቡ አትሌት /አባል/ በየትኛውም የአትሌቲክስ ውድድር ወይም እንቅስቃሴ እንዳይሳተፍ የመከላከል፣ የማገድ፣ ለፌዴሬሽኑ የማሳወቅ ኃላፊነት፤

34. ለፌዴሬሽኑና ለስፖርት ኮሚሽኑ የሚፈጸሙ የክለቡን መመዝገቢያና ሌሎች ክፍያዎችን በወቅቱ የማጠናቀቅ ግዴታ፤

35. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ውድድሮች ከተማ አስተዳደሩን ወክለው እንዲወዳደሩ የሚመረጡ አትሌቶችን ሲጠየቅ ማንኛውም ክለብ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውጤት ቅድሚያ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ይህም በትይዩ በውድድር ከ1ኛ-5ኛ ደረጃ የወጡ አትሌቶችን ክለቡ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህ ባይሆን ግን በፌዴሬሽኑ የዲሲፒሊን ደንብ መሠረት በክለቡ ላይ እንደውድድሩ ክብደት፡-

    1. የመጀመሪያ ጥፋት ከሆነ ብር 10,000.00 ይቀጣል፡፡
    2. ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከሆነ ብር 15,000.00 ይቀጣል፡፡
    3. ጥፋቱ ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ የክለቡ ፍቃድ ይሰረዛል፡፡

36. ማንኛውም ክለብ በሴት አትሌቶች ላይ ለሚያደርስ ጥቃት /ትንኮሳ/ በሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

37. በየትኛውም ደረጃ ለስፖርቱ ደኅንነትና ዕድገት ሲባል የወጡ ደንብና መመሪያዎችን የማክበርና የማስከበር፤

38. የአ/አበባን እና የአገር አቀፉን ፌዴሬሽን ደንብና መመሪያዎች ለአሰልጣኞች፣ ለቡድን መሪ፣ ወጌሻና አትሌቶች የማሳወቅ ኃላፊነት፤

39. ለክለቡ የአትሌቲክስ ቡድን አባላት የልምምድና የውድድር ስፖርት ትጥቆችን በወቅቱ የማሟላት፤

40. በገባው ውል መሠረት ለቡድኑ አባላት ወርሃዊ ደመወዝ በወቅቱ የመክፈል፤

41. በልምምድና በውድድር ወቅት ለቡድኑ አባላት ምግብና ትራንስፖርት የማቅረብ፤

42. ለቡድኑ አባላት የ24 ሰዓት ኢንሹራንስ የመግባት፤

43. በዲሲፕሊን ጉድለትና በአቋም መዋዠቅ ምክንያት በስፖርት ክለቡ አባላት ላይ የዲስፕሊን ርምጃ ሲወስድ ደረጃ በደረጃ የሚወስደውን ርምጃ ለፌዴሬሽኑ የማሳወቅ ኃላፊነት፤

44. ከፌዴሬሽኑ የሚላኩ የዲሲፕሊን እርምጃዎችንና ውሳኔዎችን ተቀብሎ የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ፤

45. ለውጤታማ ስፖርተኞች፣ አሰልጣኞችና አመራሮች ማበረታቻ ሽልማቶችን ማዘጋጀት፤

46.በአሰልጣኞችና በአትሌቶች መካከል አለመግባባቶች ሲፈጠሩ በሠላማዊ መንገድ መፍትሔ እንዲያገኝ የማድረግ ኃላፊነት፤

47.ስፖርተኞችና አባላት በውድድርና በልምምድ እንዲሁም ለውድድር በሚጓዙበት ወቅት አደጋ ቢያጋጥማቸው አቅምን ባገናዘበ መልኩ በአገር ውስጥ ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግ

## አንቀጽ 19

## የአትሌቶች፣ የአሰልጣኞች፣ የቡድን መሪና የወጌሻ መብትና ግዴታ

1. በሙያ ማሻሻያ ስልጠና የመሳተፍ፣ የምስክር ወረቀት የማግኜት
2. የድጋፍ ደብዳቤ ሲጠይቅ በህጉ መሰረት የማግኘት
3. በክለቡ መመሪያ መሠረት የመለማመጃ የስፖርት ትጥቅ የማግኘት፣
4. ከክለቡ ጋር የተዋዋለበትን ወርሃዊ ደመወዝ የማግኘት፣
5. በልምምድና በውድድር ወቅት ምግብና ትራንስፖርት የማግኘት፣
6. ከአ/አበባ ውጭ ሲንቀሳቀስ የሚገባውን እንክብካቤ የማግኘት፣
7. የክለቡ ከፍተኛ አመራር አካላት በሚወስኑት መሠረት ማበረታቻ ሽልማት የማግኘት፣
8. ከስፖርት ክለቡ ጋር የተዋዋለበትን ውል አንድ ኮፒ የማግኘት
9. በልምምድና በውድድር ጊዜ ድንገተኛ ጉዳት ቢያጋጥመው ህክምና የማግኘት፣ የ24 ሰዓት የመድን ዋስትና የማግኘት፣
10. የውል ጊዜውን ሲጨርስ የመልቀቂያ ወረቀት የማግኘት መብት አለው፡፡
11. የውድድር ውጤት የመጠየቅና የማግኘት፤
12. ከፌዴሬሽኑ ሕጋዊ የድጋፍ ደብዳቤ እና ልዩ ልዩ መረጃዎችን የመጠየቅና የማግኘት፤
13. ማንኛውም አትሌት (የክለብም ሆነ የግል) የውድድር ውጤት እንዲጻፍለት ፌዴሬሽኑን በጠየቀ ጊዜ፡-

    ሀ. ለሚጠይቀው የውድድር ውጤትና የድጋፍ ደብዳቤ የአገልግሎት ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) መክፈል አለበት፡፡

    ለ. የክለብ ተወዳዳሪ ከሆነ በቅድሚያ ከተመዘገበበት ክለብ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይገባዋል፡፡

    ሐ. ጥያቄ የቀረበበት የውድድር ውጤት ከሦስት ዓመት በፊት የተካሄደ ውድድር ከሆነ ጥያቄው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

14.አንድ አትሌት በከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተመዝግቦ የአትሌት መታወቂያ (ቲሴራ) ከወጣለት በፌዴሬሽኑ ከተመረጠ ከተማ አስተዳደሩን ወክሎ የመወዳደር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 20
## የአትሌቶች ግዴታ

1. የአዲስ አበባና የሀገር አቀፍ ፌዴሬሽን ደንብና መመሪያ የማክበር፣ ውሳኔዎችን የመቀበል፣
2. የልምምድና የውድድር ሰዓቶችን እንዲሁም የአሰልጣኞችን የሥራ መመሪያ የማክበር፣
3. በአሰልጣኞች የሚሰጠውን ስልጠና በብቃት የመወጣት፣
4. በወድድር ጊዜ የውድድር ደንቦችን በማክበር መሳተፍ፣
5. የስፖርት ሥነ ምግባር በሚፈቅደው መሠረት የክለቡንና የአ.አ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ገጽታ የማክበርና የማስከበር፣
6. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለውድድር ሲፈለግ የመሳተፍ፣
7. የስፖርት ክለቡን መተዳደሪያ ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያዎችን አክብሮ በውድድሮች መሳተፍ፣
8. ለስፖርት ክለቡ ውጤት ማማር አቅሙ የፈቀደውን ሁሉ የማድረግ፣
9. በክለቡም ሆነ በፌዴሬሽኑ የሚሰጠውን ውሳኔ የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ፡፡

## አንቀጽ 21
## የአሰልጣኞች ግዴታ

1. በአንድ የውድድር ዘመን አንድ ክለብ ብቻ የማሰልጠን፣
2. በውሉ መሠረት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት፣
3. የስልጠና ቀኑን ሰዓቱንና ፕሮግራሙን በማክበር ስልጠናውን የማከናወን፣
4. በማንኛውም መልኩ የአትሌቶች አርአያ ሆኖ መቅረብ፣
5. የሥራ ዕቅድና ማስፈጸሚያ በጀት አዘጋጅቶ ለስፖርት ክለቡ የማቅረብ፣
6. በብቃት ማነስና የዲሲፕሊን ጉድለት በሚያሳዩ አትሌቶች ላይ ደረጃ በደረጃ ማስጠንቀቂያዎች እንዲሰጣቸው የማደረግ፡፡
7. ለስፖርት ክለቡ ውጤት ማማር ሙሉ ኃይሉን፣ ጊዜውንና ዕውቀቱን የመስጠት፡፡
8. ከበላይ አካላት የሚተላለፉ መመሪያዎች በአትሌቶችና በክለቡ አባላት ዘንድ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግ፡፡

9. ስፖርታዊ ጨዋነት በስፖርት ክለቡ የማስፈን፡፡
10. የአዲስ አበባን ምርጥ ቡድን እንዲያሰለጥን ሲጠየቅ ፈቃደኛ ሆኖ የመገኘት
11. ከማናጀሮች ለአትሌቶች የሚቀርበውን ጥያቄ ተመልክቶ የክለቡን ጥቅም በማስቀደም ፈቃድ የመፍቀድ፣ የመከልከል፣
12. ከማንኛውም የሙስና ተግባር ራስን የመጠበቅ፣ በሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃት ከማደረስ የመቆጠብ ፣
13. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 22

## የወጌሻዎች ግዴታ

1. በአንድ የውድድር ዘመን አንድ ክለብ ብቻ የመስራት፣
2. በውሉ መሠረት የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ የመወጣት፣
3. የስልጠና ቀኑን ሰዓቱንና ፕሮግራሙን በማክበር ስልጠናውን የማከናወን፣
4. በማንኛውም መልኩ የአትሌቶች አርአያ ሆኖ መቅረብ፣
5. ለስፖርት ክለቡ ውጤት ማማር ሙሉ ኃይሉን፣ ጊዜውንና ዕውቀቱን የመስጠት፡፡
6. ከበላይ አካላት የሚተላለፉ መመሪያዎች በአትሌቶችና በክለቡ አባላት ዘንድ ተግባራዊ እንዲሆን የማድረግ፡፡
7. ስፖርታዊ ጨዋነት በስፖርት ክለቡ የማስፈን፡፡
8. የአዲስ አበባን ምርጥ ቡድን በወገሻነት ሲመደብ ፈቃደኛ ሆኖ የመገኘት
9. ስፖርታዊ ጨዋነት በስፖርት ክለቡ የማስፈን፡፡
10. ከማንኛውም የሙስና ተግባር ራስን የመጠበቅ፣ በሴቶች ላይ ጾታዊ ጥቃት ከማደረስ የመቆጠብ ፣
11. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 23

## የስም ለውጥ ስለማድረግ

23.1. አንድ ክለብ/ቡድን በራሱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት የክለቡን/የቡድኑን መጠሪያ ስም መለወጥ ይችላል፡፡ ይህንንም ውሳኔ ለከተማ አስተዳደሩ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሳውቆ ካፀደቀ በኋላ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን የሌላ በስራ ላይ ያለ ክለብ/ቡድን ወይም ተቋቁሞ የፈረሰ የአትሌቲክስ ስፖርት ክለብ/ቡድን ስም ወይም ተመሳስሎ ሶስተኛ ወገን ሊያደናግር የሚችል ስም መጠቀም አይቻልም፡፡

23.2. የቀድሞው ስም ተለውጦ በአዲስ የሚሰጠው ስም ከብሔር፣ ከእምነትና ከፖለቲካ የፀዳ ስፖርታዊ መጠሪያ ስያሜ መሰጠቱን ፌዴሬሽኑ በምዝገባ ወቅት ማረጋገጥ አለበት፡፡

23.3. አንድ የአትሌቲክስ ክለብ በራሱ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት የስም ለውጥ ማድረግ ይችላል፡፡

23.4. የስም ለውጥ የተደረገበት ምክንያት በፌዴሬሽኑ ተቀባይነት ካገኘ ብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በመክፈል የስም ለውጡ የሚፀድቅለት ይሆናል፡፡

23.5. በአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ውስጥ ሁለት ክለቦች በተመሳሳይ ስምና አርማ ሊመዘገቡ አይችሉም፡፡ ተመዝግበው ቢገኙ በቅድሚያ ለተመዘገበው ክለብ እውቅና ይሠጠዋል፡፡

## አንቀጽ 24

## ስለ ውህደት

24.1. በፌዴሬሽኑ ስር የሚገኙ ሁለት ክለቦች/ቡድኖች በራሳቸው ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ሊዋሀዱ ይችላሉ፡፡ መጠሪያቸውም ሁለቱም በተስማሙበት የሚወሰን ሲሆን ይህንንም ውሳኔ ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አቅርበው በማፀደቅ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም የስም ለውጡ የሚፀድቀው ለፌዴሬሽኑ የአገልግሎት ብር 1,500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ ሲከፍሉ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 25

## ስለመፍረስ

25.1. አንድ ክለብ/ቡድን በራሱ ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት ሊፈርስ ይችላል፡፡ መፍረሱንም ለከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያሳውቃል፡፡ በብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ተመዝግቦና

ተወዳድሮ የሚያውቅ ከሆነ የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክንያቱን በማጣራት በ30 ቀናት ውስጥ ለብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ሁኔታውን ያሳውቃል፡፡

25.2. በተለያዩ ምክንያቶች የፈረሰ ማንኛውም ክለብ በውስጡ ለነበሩ አትሌቶች መልቀቂያ የመስጠት ግዴታ አለበት፤ ሆኖም ይህ ተግባራዊ ሳይሆን ቢቀር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አትሌቱ መልቀቂያውን ከአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ማግኘት ይችላል፡፡

# አንቀጽ 26

# ስለ ቅጣት

26.1. ማንኛውም ክለብ/ቡድን በከተማ አስተዳደር እና በአገር አቀፍ ፌዴሬሽኖች የወጡ ደንቦችን፣ መመሪያዎችንና ውሳኔዎችን ጥሶ በተገኘ ጊዜ የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ባወጣው የሥነ-ምግባር ደንብ /መመሪያ/ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤

26.2. የከተማ አስተዳደሩ ፌዴሬሽን የማስተካከያ እርምጃ ባልወሰደ ጊዜ ብሔራዊ ፌዴሬሽኑ ጉዳዩን አጣርቶ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

26.3. ይህንን መመሪያ የጣሰ ወይም የዚህን መመሪያ አፈፃፀም ያሰናከለ ማንኛውም ክለብ/ቡድን ወይም የክ/ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አግባብ ባለው የአትሌቲክስ ስፖርት ሕግ መሠረት ይቀጣል፤ ፌዴሬሽኑም የሥነ-ሥርዓት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የውድድር ሥነ-ስራት መመሪያ 54/2013 ዓ/ም

# አንቀፅ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ውስጥ የሚካሄዱ ማንኛውም ውድድርና ስልጠና ማለትም የጐዳና ላይ ሩጫ፣ የመምና የሜዳ ተግባር ውድድሮች፣ አገር አቋራጭ ሩጫ፣ የተራራ ሩጫ፣ የእግር ጉዞ የአትሌቲክስ ፌስቲቫሎች የወዳጅነትና የፍቅር ሩጫ፣ ዝግጅቶች ወዘተ... ፍቃድ መስጠት ያጠቃለለ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

# አንቀፅ 2

## ውድድሩን የሚመራ አካል

ውድድሮች የሚመሩት የአ/አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሥሩ በሚያቋቁማቸው የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ነው::

# አንቀፅ 3

## ውድድር የሚመራበት ደንብ

1. ውድድሩ የሚካሄደው በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን (IAAF) እና በየውድድሩ የሚያዘጋጅ የውድድር ደንብና መመሪያ ይሆናል፡፡
2. ከላይ በደንብ 1 የተጠቀሱ የውድድር ዓይነቶች ከስፖንሰር አድራጊዎች ወይም በገንዘብና በማቴሪያል ከሚደግፉ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር በሚደረግ የውል ስምምነት መሠረት የመምራት ሀላፊነት እንዲሁም ፍቃድ ለሚጠይቁ ድርጅቶች ተቋሞች አስፈላጊውን መስፈርት ሲያሟሉ መርምሮ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ የፈቃድ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡ ይህንን በማያከብሩ ላይ አስፈላጊው እርምጃ ይወስዳል፡፡በአንቀጽ1 የተጠቀሱትን የውድድር ዓይነቶች ፍቃድ የመስጠት ሥልጣኑ የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ብቻ ነው፡፡

# አንቀፅ 4

## ለውድድር መሟላት የሚገባቸው መሥፈርቶች

1. አንድ ውድድር ለማካሄድ የሚጠይቅ አካል የውድድሩን ዓላማ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለማሣደግ የሚረዳ መሆን ሲገባው ተገቢ ባልሆነ መልኩ የዘር የጾታ፣ የሃይማኖትና የፖለቲካን ሁኔታ መሠረት ያደረገ ከሆነ ፈቃድ የማያሰጥ ይሆናል፡፡

2. ፈቃድ ጠያቂው አካል የሚያካሂዳቸው ውድድሮች አትሌቶችን የማይጐዳ ተገቢውን ህግና ደንብ የተከተለና ለሌሎች የከተማው አስተዳደር አትሌቲክስ ውድድር ፕሮግራም የማያውክ መሆን አለበት፡፡
3. የሚካሄደው ውድድር ተሣታፊ አትሌቶችን የማይጐዳ እና ለአሸናፊዎች ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ (የማቴሪያል) ሽልማት ያለው መሆን አለበት፣
4. ፍቃድ ጠያቂው አካል ህጋዊ የንግድ ፈቃድ የዘመኑን ግብር የከፈለና ቲን ነምበር ያለው ውድድር ለማካሄድ ከሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ ያለው፡፡

## አንቀፅ 5

## ፈቃድ የሚሠጣቸው ልዩ ልዩ ክፍሎች

1. መንግሥታዊ ተቋም
2. እርዳታና ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት
3. አገራዊ ተልዕኮ ያላቸው ተቋማት
4. ልዩ ልዩ የግልና ህዝባዊ ማህበራት
5. የቢዝነስና የንግድ ተቋማት
6. በከተማ አስተዳደሩ ፈቃድ ተሰጥቷቸው የተቋቋሙ ክለቦች
7. የክፍለ ከተማው አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እና የመሣሠሉትን …

## አንቀፅ 6

## የክፍያ ሁኔታ

1. ከላይ በአንቀጽ 1 የተመለከቱትን ውድድሮች በሚከናወኑበት ጊዜ በሚያሳትፉት የህዝብ ብዛት የገቢያቸውን መጠን በፐርሰንት ክፍያ ይፈፅማሉ

   ሀ. ከ2000 — 5000 25% ተወዳዳሪ ካሣተፉ

   ለ. ከ5001 — 10,000 20% ተወዳዳሪ ካሣተፉ

   ሐ. ከ10,001 — 30,000 15% ተወዳዳሪ ካሣተፉ

   መ. ከ30,001 በላይ የሚያሣትፉ 10 ፐርሰንት ተወዳዳሪዎችን ካሣተፉ ይህ በእንደዚህ እንዳለ ቅናሽ የሚደረግላቸው ለማህበራት 3% እና ለክፍለ ከተሞች 9% ቅናሽ ይደረግላቸዋል፡፡ አወዳዳሪ አካላት ከስፖንሰር የሚያገኙት ገቢ ፌዴሬሽኑ አይጠየቅም

2. ማንኛውም በአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሥር ተመዝግቦ በመወዳደር ላይ የሚገኝ የአትሌቲክስ ክለብ ከፌዴሬሽኑ ፈቃድ ሳያገኝ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና

ከሌሎች አወዳዳሪ ክፍሎች ጋር የቀጥታ ግንኙነት ማድረግ አይቻልም፡፡ ይህን ተላልፎ የተገኘ በፌዴሬሽኑ የዲሲፕሊን መመሪያ መሠረት የሚቀጣ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 7

## የጎዳና ላይ ሩጫ ልኬት

1. በአ/አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር ለሚደረጉ ለማንኛውም የጎዳና ሩጫና ልዩ ልዩ ውድድሮች ፌስቲቫሎች ልኬት መለካት ያለበት የፌዴሬሽኑን የፈቃድ ይሁንታ ከተገኘ በኋላ መሆን አለበት፡፡ ከዚያ በፊት ማንኛውም የልኬት ስራ መሥራት ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡
2. ፈቃድ ጠያቂው ክፍል ከፌዴሬሽኑ ፈቃድ ካገኘ በኋላ የፈቃድ ወረቀቱን ይዞ የልኬት ባለሙያዎች ጋር በመነጋገር የልኬት ካርታ ከፍቃዱ ጋር ማያያዝ አለበት፡፡ ፌዴሬሽኑ በባለሙያ መለካቱን ማረጋገጥና ለፌዴሬሽኑ የሚከፈለውን ክፍያ ገቢ መሆኑን ጭምር ማረጋገጥ አለበት

## አንቀፅ 8

## የባለሙያ ልኬት ክፍያ

1. ፌዴሬሽኑ በሚያከናውናቸው ውድድሮች ከሆነ ለዋናው ለኪ ብር 1500 (አንድ ሺ አምስት መቶ ብር) እና ለ3 ረዳት ባለሙያዎች ለእያንዳንዳቸው 500 ብር (አምስት መቶ ብር) ይከፈላል፡፡
2. ፌዴሬሽኑ ከሚያዘጋጃቸው ውድድሮች ውጪ ከሆነ ለዋና ለኪ 5000.00 (አምስት ሺ) ብር እንዲከፈለው ተደርጎ ለኪው ባለሙያ ለፌዴሬሽኑ 1000.00 (አንድ ሺ ብር) ይከፍላል፡፡

## አንቀፅ 9

## ውድድሮች የሚካሄዱበት ጊዜና ቦታ

1. ዓመታዊ መደበኛ ውድድሮች የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአ/አ/ከ/አስ/ስፖርት ኮሚሽንና ሌሎች በከተማ ውስጥ የሚካሄዱ ውድድሮችን የውድድር ካላንደር መሠረት ያደረገ ፕሮግራም እየተዘጋጀ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

# አንቀፅ 10

## የውድድር ተሣትፎ

1. በየውድድሩ ተሣታፊ የሚሆኑት በአ/አበባ ከ/አስ/ሥር ተመዝግበው ፌዴሬሽኑ ያወጣውን ህግና ደንብ የሚከተሉ /የሚያከብሩ/ ክለቦች የክፍለ ከተማ ክለቦች፣ ፕሮጀክቶች እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ክፍሎች ናቸው፡፡
2. ማንኛውም የክለብ ተወዳዳሪ በውድድር ጊዜ በዘመኑ የታደሰ መታወቂያ /ቴሴራ/ ይዞ መቅረብ አለበት ይዞ ያልቀረበ የክለብ ተወዳዳሪ በውድድሩ እንዲሣተፍ ፈፅሞ አይፈቀድለትም
3. በግልና በአንጋፋ ደረጃ የሚወዳደሩ አትሌቶች ማንነታቸውንና አድራሻቸውን የሚገልፅ የሚኖርበትን ወረዳ የነዋሪነት መታወቂያ ይዞ መቅረብ አለበት፡፡ በምዝገባና በውድድር ጊዜ ይዘው ካልቀረቡ በውድድሩ እንዲሳተፉ አይፈቀድላቸውም፡፡
4. ማንኛውም የአ/አ/ከ/አስ/የክፍለ ከተማ ነዋሪ ለመመዝገብ ሆነ ለመወዳደር የሚችለው የወረዳውን መታወቂያ ይዞ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች የወረዳው አስተዳደር በሚዘጋጀው ጊዜያዊ የመታወቂያ ወረቀት ይዘው ሊወዳደሩ ይችላሉ፡፡ ወይም የት/ቤት መታወቂያ በዘመኑ የታደሰ
5. የማንኛውም ተወዳዳሪ /ቲሴራ/ መታወቂያ ሥርዝ ድልዝ ካለው መረጃው ተቀባይነት የለውም ከውድድሩም ይሠረዛል፡፡
6. አንድ አትሌት ለሁለት ክለቦች ተመዝግቦና ፈርሞ የተገኘ እንደሆነ ውጤቱ ይሰረዛል፡፡ አትሌቱም እንደ ጥፋቱ ቅለትና ክብደት በፌዴሬሽኑ የዲሲፕሊን መመሪያ መሠረት ይቀጣል፡፡
7. በክ/ከተማና በት/ቤት ደረጃ በሚካሄደው ውድድር በተገቢነት ጉዳይ ክርክር ቢነሣ በሚቀርበው ህጋዊ የወረዳ የት/ቤት የመታወቂያ ካርድና ሌሎች አግባብነት ባላቸው መረጃዎች መሠረት ተገቢነቱ ይወሰናል፡፡
8. የሐሰት መረጃ ሠጥቶ ያወዳደረ አካል /ተወዳዳሪ/ ቡድን ክ/ከተማ በሚደረገው ማጣራት ውጤቱ ይሠረዛል፡፡
9. ማንኛውም አንጋፋ አትሌት (ቬተራን) የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጀው ውድድር ላይ ለመሳተፍ የአዲስ አበባ አንጋፋ አትሌቶች ማህበር አባል በመሆን በማህበሩ ስም ተመዝግቦ መወዳደር አለበት፡፡

10. ማንኛውም በአንጋፋ አትሌቶች ማህበር አባልነት ተመዝግቦ በመወዳደር ላይ የሚገኝ አትሌት የከተማ አስተዳደሩ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጃቸው በማንኛውም ውድድሮች ላይ በአትሌቲክስ ዳኝነት ተመድቦ መስራት አይችልም፡፡

## አንቀፅ 11

## የመወዳደሪያ የደረትና የጀርባ ቁጥር

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ በውድድር ወቅት ፌዴሬሽኑ ያቀረበው የመወዳደሪያ ቁጥር ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ለጥፎ የመወዳደር ግዴታ አለበት፡፡
2. የግል ተወዳዳሪዎች ሁሉ ለእያንዳንዱ ጥንድ ቁጥር ብር 50 ፌዴሬሽኑ በሚያስቀምጠው የገንዘብ መጠን በመግዛት በደረትና ጀርባ ላይ በመለጠፍ መወዳደር አለባቸው፡፡ ፌዴሬሽኑ ካዘጋጀው ቁጥር ውጪ ሌላ ቁጥር ለጥፎ መወዳደር አይቻልም፡፡ ሆኖም ተገቢ ያልሆነ ቁጥር ለጥፎ ከተገኘ ማጣራት ተደርጐ ውጤቱ ይሠረዛል፡፡

## አንቀፅ 12

## ክስና አቤቱታ

1. የተወዳዳሪ ተገቢነት ክስ የሚመሠረተው ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት በ30 ደቂቃ
2. የቴክኒክ ክስ የሚመሠረተው ውጤቱ በተገለፀበት በ30 ደቂቃ ውስጥ መሆን አለበት
3. ክስ የሚመሠረተው በተወዳዳሪ አትሌት ወይም በአሰልጣኝ በቃል ሆኖ በዚህ መልስ ካልረካ ለክስ እና አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ክሱን በፅሑፍና ማስረጃ አስደግፎ ከ500 ብር (ከአምስት መቶ ብር) ጋር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 13

## በምዝገባ መዘግየት

1. በየትኛውም የውድድር ዓይነት ለውድድር የምዝገባ ጊዜ በፌዴሬሽኑ ህግና ደንብ በየውድድሩ ይገለፃል ሆኖም የመመዝገቢያ ጊዜ ዘግይቶ የተወዳዳሪ ስም ዝርዝር የሚያቀርብ ሁሉ ከቅጣት ብር 300 /ሦስት መቶ ብር/ ጋር ዝርዝር ማቅረብ ይችላል፡፡ ሆኖም የቅጣት የመጨረሻ ጊዜ ውድድሩ ከመጀመሩ በፊት ባለው አራት ቀናት በፊት ባለው የሥራ ቀን ነው፡፡

# አንቀፅ 14

## የተመዝጋቢ ብዛትና የቡድን አሰላለፍ

1. በውድድር ወቅት አንድ ክለብ፣ ክ/ከተማ ወይም ት/ቤት ቀደም ብሎ በሚላከው የውድድር ደንብ ላይ የተጠቀሱትን ተወዳዳሪዎች በጐዳና፣ በአገር አቋራጭ ውድድሮች ላይ ሊያስመዘግብ ይችላል፡፡
2. ተወዳዳሪ አካሎች ፌዴሬሽኑ የሰጣቸውን የሚመለስ የመወዳደሪያ ቁጥር በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መመለስ አለባቸው በማይመልሱ አካሎች ላይ 300 ብር (ሦስት መቶ ብር) ቅጣት እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የመወዳደሪያ ቁጥር የጣለ በአንድ የመወዳደሪያ ቁጥር ብር 50 (ሃምሣ ብር) እንዲከፍል ይደረጋል፡፡
3. ውድድር ያለበት ማንኛውም ተወዳዳሪ ውድድሩ ከመጀመሩ 1 ሰዓት በፊት ቀድሞ መገኘት አለበት፡፡ በውድድር ቦታ ለውድድር ጥሪ ተደርጐለት ያልቀረበ ተወዳዳሪ በፈቃዱ እንዳልተገኘ ተቆጥሮ ከተጠራበት ውድድር ይሰረዛል፡፡
4. የውድድሩ ተሣታፊዎች አትሌቶች ብዛት በየውድድሩ ተግባር በሚላኩ የውድድር ደንቦች ይገለፃል፡፡

# አንቀፅ 15

## የመዝጊያና የመክፈቻ ሥነ-ስርዓት

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ በመክፈቻና በመዝጊያ ሥነ-ሥርዓት ላይ የቡድን አርማና የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በመያዝ በተስተካከለ ስፖርታዊ አለባበስ በሰልፍ በመሆን በክብር እንግዳ ፊት ለፊት ማለፍ አለባቸው፡፡

# አንቀፅ 16

## የሽልማት ሥነ-ሥርዓት

1. ማንኛውም ተወዳዳሪ በየውድድሩ የሚያሸንፉ አትሌቶች ለሽልማት ሲቀርቡ የወከሉትን ክፍል ትጥቅ (ስፖርታዊ አለባበስ) ለብሰው መቅረብ አለባቸው፡፡
2. በሁሉም የውድድር አይነቶች ከ1ኛ - 3ኛ ለሚወጡ ተወዳዳሪ አትሌቶች ሁሉ የሜዳሊያ ወይም የምስክር ወረቀት ሽልማት ይሰጣል በተጨማሪ እንደ ውድድሩ ዓይነት የገንዘብና የልዩ ልዩ ሽልማቶች ይሰጣሉ፡፡ በተጨማሪ የተሻለ ነጥብ ለሚያስመዘግቡ የዋንጫ ሽልማት ይሰጣል

3. ሁለት ክለቦች ወይም ክ/ከተሞች ወይም ት/ቤቶች በድምር እኩል ነጥብ ካስመዘገቡ የሚለይበት ባመጡት የወርቅ ብዛት በዚህም እኩል ከሆኑ የብር ሜዳሊያ ብዛት በዚህም እኩል ከሆኑ በነሐስ ሜዳሊያ ብዛት ይለያሉ፡፡ አሁንም እኩል ከሆኑ በዕጣ እንዲለዩ ይደረጋል፡፡
4. ተሸላሚ አትሌቶች በሽልማት አሰጣጥ ፕሮግራም ላይ በመገኘት ሽልማታቸውን መውሰድ ይኖርባቸዋል ነገር ግን ተሻላሚው አትሌት በወቅቱ በመቅረብ ሽልማቱን ካልወሰደ በሌላ ጊዜ ሽልማቱን ማግኘት አይችልም፡፡
5. በአትሌቲክስ ስፖርት ዕድገትና መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ለሚያበረክቱ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ለቴክኒክ ኮሚቴ፣ ለአሰልጣኞች፣ በዳኝነት ረዥም ዓመት ላገለገሉ ግለሰቦች በአትሌቲክስ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ሽልማት ተዘጋጅቶ ይሰጣል፡፡
6. አንድ አትሌት በ3 የውድድር ዓይነቶች በ1ኛነት ካሸነፈ ለእያንዳንዱ ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ ይሸለማል፡፡ በቀጣዩ የቴክኒክ ኮሚቴ በሚወስነው ውሳኔ መሰረት ለኮከብ አትሌቶች የገንዘብ ሽልማት ይሰጣል፡፡
7. አንድ አትሌት በወቅቱ በደንቡ ላይ በሚገለፀው መሠረት ኮከብ አትሌት ወይም ሪከርድ በማሻሻሉ ሽልማት ይሰጠዋል፡፡

## አንቀፅ 17

## የውድድር መርሀ ግብር

1. በየዓመቱ የሚካሄዱ ውድድሮች በዓመታዊ ካሌንደር ተዘጋጅቶ ለሚመለከታቸው ክለቦችና ክ/ከተሞች በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ይላክላቸዋል፡፡

# የአዲስ አበባ ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የዲስፒሊን መመሪያ 55/2013 ዓ/ም

## አንቀጽ 1

## አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የዲሲፕሊን መመሪያ ቁጥር 55/2013 ተብሎ ሊጠቃለል ይችላል

## አንቀጽ 2

## አውጪው አካል

የአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ይህንን የዲሲፕሊን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 3

## አስፈላጊነትና ዓላማ

በአትሌቲክስ ስፖርት ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ አባላት ለስነ-ስርዓት ተገዥ እንዲሆኑ ለመረዳት ብሎም በከተማ አቀፍና አገር አቀፍ ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል ለማድረግና ከአሁን በፊት በተግባር ባለመዋሉ በማንኛውም የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ የሚያጓትት ጥፋቶችና ችግሮችን ለመቀነስ ይህን መመሪያ ማውጣት አስፈልጓል፡፡

## አንቀጽ 4

## የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ የዲሲፕሊን መመሪያ አ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጀው ውድድሮችና እንቅስቃሴዎች ላይ በማንኛውም ጊዜና ቦታ በሚከሰቱ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
2. የዲሲፕሊን መመሪያው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት አባላትና አካላት ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡
   - ሀ. በፌዴሬሽኑ አባላትና አባል ክለቦች፤
   - ለ. በክፍለ ከተማው አትሌቲክስ ኮሚቴዎች ፤
   - ሐ. በአትሌቲክስ ስፖርት አመራር ላይ ለተሰማሩ አባላት፤
   - መ. በተመዘገቡ አትሌቶች፤
   - ሠ. ውድድር በሚመሩ አመራርና ዳኞች አባላት፤
   - ረ. ውድድሮችና ከውድድር ጋር ተያያዥነት ያላቸው ተግባራት ለማከናወን በፌዴሬሽኑ በተመደቡ አባላት፡
   - ሰ. ከአትሌቲክስ ስፖርት ጋር ግንኙነት ባላቸው አባላት፤

## አንቀጽ 5

## የአትሌቶች፣ የአሰልጣኞችና የወጌሻ መብትና ግዴታ

### 1. የአትሌቶች መብት

1.1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ አትሌት ለ/አ/አ ቡድን ሲመረጥ ከተማውን ወክሎ የመወዳደር

1.2. ከፌዴሬሽኑ የሚሰጠው አገልግሎት የድጋፍ ደብዳቤ ቅጅ የማግኘት፤

1.3. ለአትሌቶች የተፈቀደውና የተመደበውን ጥቅማጥቅም የማግኘት፤

1.4. በውድድርና ልምምድ ወቅት ምግብና ትራንስፖርት አገልግሎት የማግኘት፤

1.5. በውድድርና ልምምድ ወቅት የስፖርት ትጥቅና መሳሪያ የማግኘት፤

1.6. ድድርና ልምምድ ወቅት ጉዳት ቢደርስ የመታከም፤

1.7. ስለ ቡድኑ ጥንካሬና ድክመት በነፃነት ሀሳቡን የመግለፅ፤

1.8. ለተመዘገቡት አንድ ክለብ /ቡድን/ መወዳደር፣

1.9. ፌዴሬሽኑ ያስቀመጠውን መስፈርት ሲያሟሉ ሽልማት የማግኘት፤

1.10. ለአ/አ ምርጥ ቡድን ሲመረጥ ከክለባቸው ከመ/ቤታቸው ፍቃድ የማግኘትና በልምምድ ጊዜ የክለቡን ትጥቅ መጠቀም፤

1.11. በፌዴሬሽኑ በደሎችና ችግሮች የደረሰበት ከሆነ የፌዴሬሽኑን ህግና ደንብ ተከትሎ አቤቱታ የማቅረብና ምላሽ የማግኘት፤

## 2. የአትሌቶች ግዴታ

2.1. የግል ንፅህና የልምምድና የውድድር መጠቀሚያ መሳሪያዎች ፤የስፖርት ማዘውተርያ ስፍራዎች በንፅህና በጥንቃቄና በእንክብካቤ የመያዝ፤

2.2. በሀገር ውስጥ ሆነ በክለቡ የሚያርፉባቸው ስፍራ ቦታዎች አካባቢውን በንፅህና የመያዝ በአግባብ የመጠቀምና በመጨረሻም በትክክል የማስረከብ የደረስም ጥፋት ሲኖር ተጠያቂ የመሆን፤

2.3. በልምምድ ሆነ በውድድር ቦታ ከአትሌቶች ጋር የመግባባትና የመከባበር ፤

2.4. በማንኛውም ያታ ላይ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ስነ አምሮአዊ አካላዊ ይሁን ወሲባዊ ትንኮሳ አለማድረግ፤

2.5. ለጋራ ዓላማ ሲባል ከአሰልጣኞች ጋር ተግባብቶ ተከባብሮ የመስራት

2.6. ፌዴሬሽኑ የሚያወጣውን ደንብና መመሪያ የመቀበልና ተግባራዊ የማድረግ፤

2.7. ለአ.አ ከተማ ምርጥ ቡድን የተመረጠ አትሌት ፌዴሬሽኑ በመደበለት አሰልጣኝ በመሰልጠን መወዳደር ፤

2.8. የሀገር ውስጥና አለም አቀፍ ውድደር ለመወዳደር ፍቃድ የመጠየቅ፤

2.9. በውድድር ወቅት የዳኛውን ወሳኔ በፀጋ የመቀበል ተቃውሞ ካለ ህጉ በሚያዘው መሰረት ቅሬታውንና ተቋውሞን በፅሁፍ የማቅረብ፤

2.10. አትሌቱ በግሉና በቡድን ለሚፈፅማቸው ህገ ወጥ ድርጊቶች በፌዴሬሽኑ ህገ ደንብ መሰረት ተጠያቂ የመሆን፤

2.11. ከአጉል ሱሶችና አበረታች መድሐኒቶች ነፃ የመሆን፤

2.12. በውድድር ወቅት ሆን ብሎ ቢጫና ቀይ ካርድ አለማየት፤

2.13. በልምምድ ስፍራ በመመገቢያና ማረፍያ ስፍራ ማንኛውንም ድምፅ ያለው እና ድምፅ አልባ መሳሪያ ይዞ አለመገኘት፤

2.14. ለስፖርት ቤተሰብ ተመልካቹና ተወዳዳሪ ቡድን ክብር ካለመስጠት ቁጣ ከሚያስነሱ ድርጊቶች የመቆጠብ ፤

2.15. ለስፖርት ህግና ለስፖርታዊ ጨዋነት ተገዢ መሆን፤

2.16. ለተመዘገበት ለስፖርት ክለቡ የመወዳደር ግዴታ አለበት

2.17. አትሌቶች ውድድር የሚሳተፉት ፌዴሬሽኑ ባዘጋጀው የመወዳደሪያ የደረትና የጀርባ ቁጥር ብቻ ነው፡፡

## 3. የአሰልጣኞች መብት

3.1. በሰለጠኑበት የአሰልጣኝነት ሙያ የማሰልጠን፤

3.2. ለአሰልጣኞች በሚወጣው ስልጠና መስፈርት መሰረት ኮርሶችን የማግኘት የመወዳደርና የማሰልጠን፤

3.3. ፌዴሬሽኑ ወይም የስልጠና ኮርሱን ባዘጋጀው አካል ተሳታፊ ከሆነ በኃላ የምስክር ወረቀት የማግኘት፤

3.4. በተመደቡበት አሰልጣኝነት ክለብ /ተቋም/ ውሉን ለማቋረጥ ሲፈለግ ከአንድ ወር በፊት የጽሁፍ ጥያቄ ማቅረብ ስምምነት ላይ መድረስ ፤በውሉ መሰረት ስንብት ማግኘት፤

3.5. በውድድር ወቅት የስፖርት ትጥቆችና የማሰልጠኛ መሳርያዎች የማግኘት ፤

3.6. የስልጠናው ሂደት አስመልክቶ በሚቀርብለት ክስና አቤቱታ ምላሻ የመስጠት፣

3.7. ከከተማ ውጪና ክልል ከተሞች ሲንቀሳቀስ አስፈላጊውን ወጪ በመረጠው አካል የመሸፈን፣

3.8. ለስልጠናና ለውድድር በሚጎዝበት ወቅት ድንገተኛ አደጋ ቢያጋጥመው የህክምና አገልግሎት የማግኘት፣

## 4. የአሰልጣኞች ግዴታ

3.9. በአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም ሆነ በክለቡ ህጋዊ የአሰልጣኝነት ማስረጃየማቅረብ፣

3.10. በአንድ የውድድር ዘመን ለአንድ ክለብ ብቻ ተመዝግቦ የማሰልጠን ግዴታ አለበት

3.11. ይህው የተመዘገበው አሰልጣኝ የውል ዘመኑ ሳያበቃ ከሌላ ክለብ ጋር ውል መግባት አይችልም፣

3.12. አንድ አሰልጣኝ ከተመዘገበበት ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፈቃድ ሳያገኝ ወደ ሌላ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ሄዶ ማሰልጠን የሚችለው ከከተማው ፌዴሬሽን ሲፈቀድለት ብቻ ነው ፣

3.13. አንድ በከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የተመዘገበ አሰልጣኝን ፌዴሬሽኑ የሙያ ድጋፍ እንዲያደርግ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፣

3.14. አንድ አሰልጣኝ በሚቀርብበት አቤቱታ ወይም ክስ በወቅቱ ምላሽ የመስጠት፣

3.15. በአሰልጣኝነት የተመዘገበ በዳኝነት ላይ ተመድቦ ማገልገል አይችልም፡፡

3.16. የአትሌቱን የውድድር የውጤትና የስልጠና መረጃዎችን የመስጠት፣

3.17. በስነ ምግብር በአርአያነት ሰልጠና መስጠት የሙያውን ክብር ከሚነኩ ድርጊቶች የመታቀብ ከብክነት ከሙስና የፀዳ መሆን፣

3.18. እራሳቸውን ለለውጥ ዝግጁ የማድረግ፣

3.19. ከከተማው የተመረጡ አትሌቶችን የውድድርና የስልጠና መረጃ የመያዝ፣

3.20. የፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎችን እንዲሁም ውሳኔዎች ህጎች የማክበርና የመፈፀም የማስፈፀም፣

3.21. በዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት የወጡትን የዲሲፕሊን መርሆች የማክበር የማስከበርና ተግባራዊ ማድረግ፣

3.22. ከፌዴሬሽኑ አመራሮችና ባለ ድርሻ አካላት ጋር ተግባብቶ የመስራት፣

3.23. በያንዳንዱ ውድድር ስልጠና ላይ የተከሰቱ ደካማና ጠንካራ ጎኖች የጽሁፍ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፣

## 5. <u>የወጌሻ መብት</u>

5.1 ከፌዴሬሽኑ ጋር የተደረገ የውል ስምምነት ቅጂ የማግኘት

5.2 ወጌሻው ከአትሌቶች ጋር ሲንቀሳቀስ የህክምና አገልግሎት ማግኘት፤

5.3 ከክለቡ ወይም ከፌዴሬሽኑ  የገባበትን ግዴታ የማያሟላ ሆኖ ከተገኘ አቤቱታውን ለፌዴሬሽኑ ውሳኔ እንዲሰጠው የማቅረብ፤

5.4ከነበረበት ክለብ ስምምነት የመልቀቅ

5.5 በገባው ውል መሰረት ወርሃዊ ደመወዝ ሌሎችን ጥቅማ ጥቅሞችን የማግኘት፤

5.6 በዚህ የዲስፕሊን መመሪያ የተሰጡትን ሌሎች መብቶችን የማግኘት መብት አለው፤

## 6. <u>የወጌሻ ግዴታ</u>

5.7ከፌዴሬሽኑ ወይም ከክለቡ ጋር በገባው ውል መሰረት የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በተገቢው መንገድ የማከናወን፤

5.8 የክለቡን የፌዴሬሽኑን ደንብና የዲሲፕሊን መመሪያ የማክበር በመመሪያው መሰረት የተሰጡትን ግዴታዎች የመፈፀም፤

5.9 ለከተማው ፌዴሬሽን አገልግሎት እንዲሰጥ ሲመረጥ አክብሮ መገኘት፤

5.10 ስፖርታዊ ጨዋነት መርሆችንና ስነ ምግባሮችን ተግባራዊ በማድረግ ለአትሌቶች አርአያ የመሆን፤

5.11 . በአትሌቶች ከቡድን መሪዎች ከአሰልጣኞችና ከአመራር አካላት ጋር ተግባብቶ የመስራት፤

# <u>አንቀጽ 6</u>

# <u>የክለቦች መብትና ግዴታ</u>

## 1. <u>የክለቦች መብት</u>

በፌዴሬሽኑ መተዳደሪያ ደንብ የተጠቀሱ መብቶች እንደተጠበቀ ሆኖ

1.1 የአትሌቶች አሰልጣኞችና ወጌሻዎች የውል ስምምነትና ቴሳራዎች በፌዴሬሽኑ እንዲፀደቀ ወዲያውኑ የማግኘት፤

1.2 የክለቡን የዲሲፕሊን መመሪያና ግዴታዎች በሚያሟሉ አትሌቶች፤አሰልጣኞች ወጌሻዎችና አመራር አባላት ላይ ለፌዴሬሽኑ እያሣወቀ ደረጃውን የጠበቀ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ፤

1.3 አቤቱታዎችን ለፌዴሬሽኑ የማቅረብ ወቅታዊ ምላሽና ወሳኔዎችን በዲስፕሊን መመሪያው በተጠቀሰው የጊዜ ገደቦች የማግኘት ፤

1.4 ለከተማው አሰተዳደር ቡድን አቅምና ችሎታ ያላቸውን አትሌቶችን ማሰመረጥ/መመረጥ/

1.5 በፌዴሬሽኑ በሚዘጋጁ የውድድር ደንብና መመሪያዎች ላይ የማሻሻያ ሀሳብ የማቅረብ

1.6 የውጡ የውድድር ደንብና መመሪያዎች በወቅቱ የማግኘት፤

## 2. <u>የክለቦች ግዴታ</u>

2.1 የአትሌቶች፣ የአሰልጣኞችና የወጌሻዎች መብት በውላቸው መሰረት መጠበቅ፤

2.2 በፌዴሬሽኑ የፀደቀ የአትሌቶች ውል ስምምነት አንድ ቅጂ ለአትሌቱ መስጠት፤

2.3 ለአትሌቶች የሚደረግ የዝውውር ክፍያ ለፌዴሬሽኑ በግልፅ የማሳወቅ፤

2.4 የውል ዘመናቸውን ያጠናቀቁ አትሌቶች የመልቀቂያ ወረቀት የመስጠት፤

2.5 በፌዴሬሽኑ የሚሰጡ ውሳኔዎች ተግባራዊ ማድረግ፤

2.6 ፊርማና ማህተም ያረፈበት የፌዴሬሽኑን ደብዳቤዎች የመቀበልና ምላሽ መስጠት፤

2.7 በፌዴሬሽኑ አካላት የክለቡን አደረጃጀት መረጃዎችና ኢንፎርሜሽን ትብብር ሲጠየቅ የመስጠት፤

2.8 የታገደ የክለብ አባል በየትኛውም የአትሌቲክስ ውድድርና ስልጠና እንዳይሳተፍ የመከልከልና የማገድ፤

2.9 የክለቡን መመዝገቢያና ሌሎች ክፍያዎችን በወቅቱ የማጠናቀቅ

2.10 ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው መደበኛና መደበኛ ባልሆኑ ውድድሮች ላይ የመሳተፍ፤

2.11 በፌዴሬሽኑ በሚዘጋጁ አመታዊ ውድድሮች ላይ ቢያንስ አራት ውድድሮች መወዳደር፤

2.12 በአንድ ውድድር ዘመን ከ25 አትሌቶች ያላነሰ መስመዝገብ ተሳታፊ መሆን፤

2.13 በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ውድድሮች ከተማ አስተዳደሩን ወክለው እንዲወዳደሩ የሚመረጡ የአትሌቶች ሲጠየቅ ቅድሚያ የመስጠት፣

2.14 ከክለቡ ውስጥ ደንብና ውል ውጪ በአትሌቶች የተለየ ጥቅም ለማግኘት ሲል በደል/ችግር/ ቢፈጥር ጉዳዩን በማጣራት በክለቡ ላይ እርምጃ መውሰድ ፡፡

2.15 ከአ/አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እውቅና ውጪ የውድድርና ስልጠና ቀጥታ ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድም፡፡

# አንቀጽ 7

# የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚዎች፤ የክለብ አመራሮች፤ አማተር አገልጋዮችና ልዩልዩ ኮሜቴ አባላት መብትና ግዴታ

## 1. መብት

1.1 በፌዴሬሽኑ ውስጥ የመመረጥ የመምረጥ መብት አላቸው፣

1.2 ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ፣

1.3 ከፌዴሬሽኑ የሚገኙ ጥቅማ ጥቅም የማግኘት፣

1.4 ባላቸው ሙያ፤እውቀትና ልምድ ሲመረጡ ማገልገል፡፡

## 2. ግዴታ

2.1 ከላይ የተጠቀሱ አባላት በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ በግልና በጋራ ተጠያቂ ይሆናሉ፤

2.2 በመደበኛ ስብሰባ መገኘት፣

2.3 የፌዴሬሽኑን ስምና ዝና የመጠበቅ፣

2.4 እርስ በእርስ የመከባበር የመደማመጥ ሀሳብን የሌላውን ባልደረባ ሰብዕና ሳይነካ በቀጥታ መግለፅ፣

2.5 ከፌዴሬሽኑ ሠራተኞች ጋር መልካም ግንኙነት የመፈጠርና አርአያ ሆኖ መገኘት፣

2.6 ለፌዴሬሽኑ ልዩልዩ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተገዢ መሆን፣

2.7 ለስፖርት ጨዋነት መርሆዎች መገዛትና አርአያ መሆን፣

2.8 ሙስናንና ብልሹ አሰራርን መዋጋት፣

2.9 የክ/ከተማ አትሌቲክስ ኮሜቴና ክለቦች በአጠቃላይ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር መልካም የሆነ የስራ ግንኙነት እንዲኖር መጣር፡፡

# አንቀጽ 8

# የዳኞች መብትና ግዴታ

## 1.መብት

1.1. በወሰዱት የዳኝነት ደረጃ በሚመደቡበት ጊዜ ጠብቀው የዳኝነት አገልግሎት መስጠትና መዳኘት፣

1.2. የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች መውሰድ፣

1.3. ሙያውን በተመለከተ ከፌዴሬሽኑ የደጋፊ ደብዳቤ በጠየቁ ጊዜ የማግኘት፣

1.4. የዳኝነት ሙያና አሰራር የበለጠ እድገት እንዲያገኝ ተገቢውን የሙያ ድጋፍ የመስጠት፣

## 2.ግዴታ

2.1. በሰለጠኑበት የዳኝነት ሙያ ውድድሮችን መምራት፣

2.2. በየውድድር ዘመን በፌዴሬሽኑ ጊዜ ሰሌዳ መሰረት በዳኝነት ለማገልገል መመዝገብ ፣

2.3. በዳኝነት በሚመደብበት ጊዜ የስፖርታዊ ጨዋነት መርህ በመከተል ፍትሀዊ ዳኝነት መስጠት፣

2.4. ፌዴሬሽኑ በሚጠራው የሙያ ማሻሻያ ሴሚናር ላይ እንዲገኙ ጥሪ ሲደረግ መገኘት፣

2.5. ለአ/አ ከተማ አስተዳደር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ተመዝገበው በሌላ ከተማ አስተዳደር /ወይም/ክልል ፌዴሬሽን ተመዝግበው አትሌቲክስ ዳኝነት ስራ አለመስራት፣

2.6. በዳኝነት ሲመደቡ በቅድመ ስብሰባና ውድድር ሰዓትና ቀን አክብሮ መገኘት፣

2.7. በዳኝነት ተመድበው ውድድሩ ሳያልቅ የውድድሩ መሪ ሳያሰናብቱ ጥሎ አለመሄድ፣

2.8. በውድድር ወቅት ለዳኝነት ሲመጡ በተሟላ ስፖርታዊ አለባበስ መቅረብ፣

# አንቀፅ 9

# አትሌቶችን ለቅጣት የሚያበቁ ጥፋቶች

## 1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶች

1.1. በልምምድና በውድድር ቦታ አስፈላጊ የስፖርት ትጥቅ አሟልቶ አለመገኘት፣

1.2. የልምምድና የውድድር ትጥቆችንና የፌዴሬሽን ንብረቶች በንፅህናና በጥንቃቄ አለመያዝ፣

1.3. በሐኪም ወይም በወጌሻ እንዲተገበሩ የሚነገሩና የትምህርታዊ ስልጠናዎች ላይ አለመገኘት፣

1.4. ፌዴሬሽኑ በማያውቀው ሁኔታ ህጋዊ ዕውቅናና ፈቃድ ሳያገኝ ከተመዘገቡበት ፌዴሬሽን ውጪ ውድድሮች ላይ መሳተፍ፤

1.5. አትሌቱ ለመገልገያ ከፌዴሬሽኑ የተረከባቸውን ንብረቶች በጊዜው መልሶ አለማስረከብ፤

1.6. ለቡድኑ ውጤታመነት ሲባል የሚፈለገውን በቂ ዕረፍት አለማድረግ፤

1.7. በአሰልጣኝና በቡድን መሪ የሚሰጡ ስነ-ሰርዓት እና ተጓዳኝ መመሪያዎችና ትዕዛዞች አለማክበር፤

1.8. ውድድሩን የሚመሩ ዳኞች እና ሌሎች አመራር አካላት ጋር ግጭት መፍጠር፤

1.9. በአሰልጣኙ የሚሰጡ የስልጠና ጫናዎችን ተቋቁሞ ተግባራዊ አለማድርግ፤

1.10. የቡድኑ አባል ያልሆነና ያልተፈቀደለትን ሰው ወደ ምግብ ቤትና ማረፊያ ቤት ይዞ መግባት ፤

1.11. አትሌቱ በውድድር ወቅት ሆነ ብሎ የቢጫና ቀይ ካርድ ሰለባ መሆን፤

1.12. ያለ በቂ ምክንያት ፈቃድ ሳይሰጥ ከልምምድ መቅረት፤

1.13. አትሌቶች ማረፊያ ስፍራ እንዲገባ ሲጠሩ ጥሪውን አክብሮ አለመገኘት፤

1.14. ፌዴሬሽኑ ሳያውቀውና ሳይፈቅድ በግሉ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከፌዴሬሽኑ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሆኔታ ጋር በፅሁፍና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ተጠቅሞ መረጃ መስጠት፤

1.15. ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ተግባራት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያላቸው ሌሎች የዲሲፕሊን ጉድለቶች መፈፀም፤

## 2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶች

2.1. የብድን መሪ፤የአሰልጣኞችናና የኃላፊዎችን ትዕዛዝ አለማክበር፤በቸልተኝነት ፤በመለገም ወይም ሆን ብሎ የአሰራር ሰነ-ስርዓትን ባለመከተል በስራ ላይ በደል ማድረስ፤

2.2. በመኖሪያ፤በመመገቢያ፤በልምምድ፤በውድድርና በማንኛውም ስፍራዎች ለስፖርተኞች የተከለከሉ መጠጦች፤ሲጋራ፤ጫት፤አደዛዥ ዕፆች፤ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገሮችና ያልታዘዙ መድሐኒቶችን መጠቀምና ይዞ መገኘት፤

2.3. በልምምድ፤በውድድር፤በመመገቢያ ስፍራ እና በማደሪያ ስፍራ ማንኛውም ዓይነት ድምፅ ያለው ወይም ድምፅ አልባ መሳሪያ ይዞ መገኘት፤

2.4. በማረፊያ/ሆቴል በአካባቢውና በመመገቢያ ቦታ ያታዊ ትንኮሳ ማድረግ፤

2.5. የጋራ መጠቀሚያ በሆነው ማረፊያ ስፍራ ውስጥ የለሌላ ሰው ንብረት ጥንቃቄ አለማድረግ አስነዋሪ በሆነ የእምነት ማጉደል፤የማታለል የማጭበርበርና የስርቆት ተግባር ውስጥ በማናቸውም ቦታ ፈፅሞ መገኘት፤

2.6. በፌዴሬሽኑ ንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፣

2.7. ያለ ፈቃድ ከተያዘው ማረፊያ ውጭ ማደር፤

2.8. ለስፖርት ተመልካቹ፤ለተወዳዳሪው ቡድን አትሌቶች ተገቢውን ክብር አለመስጠት፤

2.9. በማንኛውም ቦታ በጠብ አጫሪነት፤በድብድብ፤በስድብናዘለፋ፤እንዲሁም አትሌቲክስ ስፖርትን ከሚጎዳ የጥፋት ተግባር ላይ መገኘት፤

2.10. የፌዴሬሽኑንና ክለብን በሚጎዳ ተግባርና የአድማ እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ፤

2.11. በግድየለሽነትና በተንኮል የቡድኑን ውጤት እንዲቀየር ማድረግ፤

2.12. በማንኛውም ስፍራ የከተማ አስተዳደሩን መልካም ገፅታ የሚያጠፋ ተግባራት ላይ መሳተፍ፤

2.13. ፌዴሬሽኑ ሊያውቀው የሚገባውን መረጃ መደበቅ ወይም የተሳሳተ መረጃ መስጠት፤

2.14. የሐሰት መረጃ አቅርቦ መገኘት፣

2.15. አንድ ተወዳዳሪ ለሁለት ክለብ ለመወዳደር ፈርሞ የተገኘ፣

2.16. ውድድሩን የሚመሩ ዳኞችና የውድድር አመራር አካላትን መሳደብ፤ለመደባደብ መሞከርና መማታት፤

2.17. አትሌቶች ማረፊያ ሰፍራ እንዲገብ ሲጠሩ ጥሪውን አክብሮ አለመገኘት፤

2.18. ፌዴሬሽኑ ሳያውቀውና ሳይፈቅድ በግሉ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ከፌዴሬሽኑ ጋር በተያያዘ ማንኛውም ሆኔታ ጋር በጹሁፍና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ተጠቅሞ መረጃ መስጠት፤

2.19. ከዚሁ በላይ ከተዘረዘሩ ተግባራት ጋር ተመሳሳይ ክብደት ያላቸውሌሎች የዲሲፕሊን ጉድለቶች መፈፀም፤

2.20. ከአሰልጣኞች ከቡድን መሪዎች ከአትሌቶች እና ከፌዴሬሽኑ ሰራተኞች ጋር ስፖርታዊ ጨዋነት ማጉደል፤

# አንቀጽ 10

## <u>አሰልጣኞችን ለቅጣት የሚያበቁ ጥፋቶች</u>

### 1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶች

1.1. በስልጠና ውድድር ወቅት በዕቅድ ያለመስራት፣

1.1 የስፖርተኞችን የስልጠናና የውድድር ግምገማ ወቅታዊ አቋምናየሚያስመዘግቡት ውጤት አለመያዝ፣

1.2. አትሌቶች በሚያሣዩት የዲስፕሊን ጉድለት በአቋም መቀነስና በሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶች በኃላፊነት እርምጃ አለመውሰድ፤

1.3. ወቅታዊ የስልጠናና የውድድር ክንውኖችን በፅሑፍ ሪፖርት አለማድረግ፤

1.4. አትሌቶች የስነ ስርዓት ጉድለት ሲፈጽሙ በወቅቱ ለፌዴሬሽኑ አለማሳወቅ፣ ለተፎካካሪና ለተወዳዳሪ አትሌቶች ክብር አለመስጠት፤

1.5. የአትሌቶችን ቢጫና ቀይ ካርድ በውድድር መዝግቦ አለመያዝና ውሳኔዎችን ተግባራዊ አለማድረግ፤

1.6. ተግባብቶ አለመስራትና የሚጠበቀውን ውጤት አለማስመዝገብ፤

1.7. የፌዴሬሽን ስልጠና ስራዎችን ጨዋነት በተሞላበት ሁኔታ በመተጋገዝ፤በመተባበርና የጋራ ስራ እድርጎ አለመሰራት፣

1.8. በተለያዩ ማሊያዎች ቡድን አሰልፎ መገኘት፡፡

## 2. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት አይነቶች

2.1. የፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያ የስራ አስፈፃሚና የጽ/ቤቱን ውሳኔዎች አለማክበር፤

2.2. የፌዴሬሽኑን ደንብና መመሪያ እንዲሁም የስራ አስፈፃሚ የሚሰጠውንና በየጊዜው የሚያስተላልፉቸውን ውሳኔዎች አለማክበር፤

2.3. አሰልጣኙ በፈፀመው ስነ-ስርዓት ጉድለት ምክንያት በፌዴሬሽኑ በክለቡ፣ በፕሮጀክት፣በክ/ከተማ ላይ ቅጣት እንዲጣል ሲያደርግ፤

2.4. የተጭበረበረና የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ተጠቃሚ ለመሆን መሞከር፣

2.5. ከአትሌቶች ሆነ ከክልል በእርሱና በፌዴሬሽኑ ስም የሙስና ተግባር መፈፀም፤

2.6. የፌዴሬሽኑን ጥቅም አሳልፎ ለሌላ አካል መሰጠት፤

2.7. ውስጥ ለውስጥ አትሌቶችን በመከፋፈልና በማሳደም ቡድኑ ውጤት እንዳያመጣ ማድረግ፤

2.8. የሙስና ተግባር መፈፀም፤

2.9. ጾታዊ ትንኮሳ ማድረግ፡፡

# <u>አንቀፅ 11</u>

# <u>ወጌሻን ለቅጣት የሚያበቁ የዲሲፕሊን ጥፋቶች</u>

### 1. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶች

1.1. የስራ ዕቅድና አፈፃፀም በወቅቱ ሪፖርት አለማድረግ፤

1.2. በልምምድና በውድድር ወቅት በሰዓቱ አለመገኘት፤

1.3. የታመሙ ስፖርተኞችን በወቅቱ ህክምና እንዲያገኙ አለማድረግ፤

1.4. በአትሌቶች ፍላጎት እየተመራ ያለ አግባብ ፍቃድ መስጠት፤

**2.ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ የጥፋት ዓይነቶች**

2.1. የተሳሳተ መረጃ በማቅረብ ተጠቃሚ ለመሆን ለማድረግ መሞከር፤

2.2. የፌዴሬሽኑን ጥቅም አሳልፎ ለሌላ አካል መስጠት፤

2.3. ውስጥ ለውስጥ አትሌቶችን በመከፋፈልና በማሳደም ቡድኑ ውጤት እንዳያመጣ ማድረግ፤

2.4. የተሳሳተ መረጃ በማቅረብና በመስተት የሙስና ተግባርን መፈፀም፤

2.5. የአትሌቶችን የህክምና ሚስጥር አሳልፎ መስጠት፡፡

## አንቀጽ 12

## የስነ-ስርዓት እርምጃዎች

የተፈጥሮና ህጋዊ ሰውነት ባላቸው አትሌቶች፤አሰልጣኞች ፤ወጌሻዎች የክለብ አመራሮች፤አማተር አገልጋዮችና ልዩ ልዩ ኮሚቴ አባላት ላይ የጋራ ተፈፃሚ የሚሆኑ የቅጣት ዓይነቶች ወይም እርምጃዎች ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ናቸው፡፡

## ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት

- **የቃል ማስጠንቀቂያ**
- **የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ/ተገስጾ / ወቀሳ/**

### ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት

- የገንዘብ ቅጣት
- ማገድ /ማሰናበት/

### የቅጣት ማብራሪያዎች

- ቀላል ጥፋት ዓይነቶች ህግ መጣስ ወይም በገቡት ግዴታ ሳይወጡ ሲቀረ የሚሰጥ የዲሲፕሊን ቅጣት ነው፡፡

❖ ከባድ ጥፍት ዓይነትቶች የሚባሉትን በተደጋጋሚ ጊዜ ህግ በመጣስ የገቡትን ግዴታ ሳይወጡ ሲቀር ብሎም የውድድርና የስልጠና ሂደት ላይ ከፍተኛ ስነ-ስርዓት ጉድለት የሚያስከትል ሲሆን ነው፡፡

## ቀላል ጥፋት

የቃል ማስጠንቀቂያ፣ የጹሁፍ ማስጠንቀቂያን/ተግሳፅ/ወቀሳ/ያካትታል ቀላል ጥፋቶች ከተደጋገሙ ወደ ከባድ ቅጣት ሊሻገር ይችላል፡፡

## ከባድ ጥፋት

የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ /ወቀሳ/ ተግሳፅ/ አጥፊው ለፈጸመው የዲሲፕሊን ግድፈት ለአጥፊው አካል በጽሁፍ የሚሰጠው ወይም በገንዘብ እስከ 10,000.00 /አስር ሺህ ብር/ ሊያስቀጣው የሚችል ጥፋት የሚወስድ ጥፋት ነው፡ ጥፋቶችን በተደጋጋሚ የሚፈፅመው ከሆነ ወደ ማገድ ማሰናበት ሊሻገር ይችላል፡፡

ማሰናበት ወይንም ማገድ፣በውሉ መሰረት ሳይፈፀም ሲቀር ጥፋቱ ከባድ የሆነና በተደጋጋሚ ሲፈፀም ፌዴሬሽኑን የሚጎዳና ስርዓት የሚያጓድል ሆኖ ሲገኝ የሚፈፀም ቅጣት ነው፡፡እንደጥፋቱ ከባድነት እስከ 15,000.00 /አስራአምስት ሺህ ብር/ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ሊወሰድ ይችላል፡፡

## የገንዘብ ቅጣት

ሀ. የሚወሰደው የገንዘብ ቅጣት ከብር-1000.00-/አንድ ሺህ ብር/ በታች መሆን የለበትም፡

ለ. የግለሰብ የገንዘብ ቅጣት የወር፣አበል ወይም የወር ደመወዝ ከሚያገኘው በላይ መሆን የለበትም፣

ሐ. የገንዘብ ቅጣቱን የሚያሳውቀው የዲሲፕሊን ኮሜቴ ጊዜውንና የጊዜ ገደቡን አብሮ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ13

## የአትሌቶች የስነ ምግባር ጉድለት ለማስተካከል በቅደም ተከተል የሚወሰዱ እርምጃዎችና ደረጃቸው

1. **አትሌቶች የስነ ምግባር ጉድለቶች ሲያሳዩ እንደጥፋቱ ዓይነትና መደጋገም ቀጥሎ የተዘረዘሩት የሰነ ምግባር ማስተካከያ እርምጃዎች ይወሳዳል፤**

ሀ. በአሰልጣኞችና በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በኩል ምክር መስጠት፤

ለ. በአሰልጣኞችና በቴክኒክ ኮሚቴ ሰብሳቢ በኩል የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ሐ. በቴክኒክ ኮሜቴ የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

መ. አትሌቱ የፈፀመው የስነ ምግባር ጉድለት ከፍተኛ ሆኖ ሲገኝና ይህም በቴክኒክ ኮሚቴ ታይቶና ተረጋግጦ የመጨረሻ ውሳኔ ይስጥ ዘንድ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳብ ይቀርባ፤

2. **ከፍተኛ የዲሲፕሊን ጉድለት በፈፀመ አትሌት ላይ የሚወሰዱ የዲሲፕሊን እርምጃዎች የሚከተሉ ይሆናሉ፤**

ሀ. ለሶስት ወር ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፤

ለ. ለስድስት ወር ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፤

ሐ. ለአንድ ዓመት ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፤

መ. ለሁለት ዓመት ከማንኛውም ስልጠናና ውድድር መታገድ፤

3. **ቀላል የዲሲፕሊን ጉድለት በቃል ማስጠንቀቂያ /በምክር/ የሚታለፉ የስነምግባር ጉድለቶች**

ሀ. ወደ ስልጠና ውድድር ስፍራ አርፍዶ መምጣት

ለ. የግል ንፅህናን የልምምድ የውድድር ትጥቅና የመጠቀሚያ መሳሪያዎች በጥንቃቄ አለመያዝ

ሐ. በክልል ከተሞች /ክልል/ በሚያርፉባቸው ስፍራ ተገቢውን ጥንቃቂ አለማድረግ

መ. አብረውት ከሚሰሩ አትሌቶች ጋር ተግባብቶ አለመስራት

ሠ. ከአሰልጣኝ ጋር ተግባብቶና ተከባብሮ አለመስራት

ረ. ያለ ፈቃድ ከስልጠና እና ከውድደር መቅረት

ሸ. ከተመደበለት አሰልጣኝ ወይም ከተመደበበት ፕሮግራም ውጪ ከሌሎች ጋር ተቀላቅሎ መስራት

በ. በውድድር ስፍራዎች ዳኝነት ማወክ

ቀ. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ በአንቀጽ 11 በተ.ቁ1-16 ያሉትን ጥፋቶችን ሲፈፅም ይሆናል

4. **ከባድ የዲሲፕሊን ጉድለት የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡ የስነ ምግባር ጉድለቶች**

ሀ. ከላይ ቁጥር 3-ከሀ-ረ ስር አንዱን የስነምግባር ጉድለት ፈፅሞ በቃል ማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የስነ ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ

ለ. በተመደበበት ውድድር አጥጋቢ ባልሆነ ምክኒያት አለመሳተፍ

ሐ. ከተማ አስተዳደሩን ወክለው የመወዳደር የውድድሩ ሽልማት ላይ ለመገኘት ፈቃደኛ አለመሆን

መ. በፌዴሬሽኑ ተመድበው ሙያዊ ግልጋሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ አካላት ጋር ተግባብቶ አለመስራት

ሠ. የፌዴሬሽኑ የሚያወጣቸውን ደንቦች እና መመሪያዎች አለማክበር

ረ. ውል/ግዴታ/የገባውን ሳይፈፅም ሲቀር

## 5. ለሶስት ወር ከውድድር የሚያሳግዱ የስነ ምግባር ጉድለቶች

ሀ. ከላይ በቁጥር 4 ከሀ-ሠ ከተጠቀሱት የስነ ምግባር አንደኛውን ፈፅሞ በጹሁፍ ማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የስነ ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፤

ለ. የተፈለገበትን ክፍያ ማዘግየት ወይም ለመክፈል ፈቃደኛ አለመሆን፤

ሐ. ከተማ አስተዳደሩን ለሚወክሉ የውድድር ጥሪዎች ውድድሮች ላይ ቅድሚያ አለመስጠት፤

መ. በስልጠና ሆነ በውድድር ስፍራዎች ሁከት መፍጠርና ፀጥታ ማደፍረስ፤

ሠ. የአትሌቲክስ ስፖርትን ከሚጎዳ ተግባር ላይ መሰማራት የስም ማጥፊያ ዘመቻ ማካሄድ፤

ረ. ከባድ ዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ በተቁ1-17ያሉትን ሲፈፅም ይሆናል፣

## 6. ለስድስት ወር ከውድድር የሚያሳግድ የስነ- ስርዓት ጉድለቶች

ሀ. ከላይ በቁጥር 5 ከሀ-ረ ከተጠቀሱት የስነ- ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈጽሞ ከሶስት ወር ቅጣት የታለፈ እና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ ጉድለት ፈጽሞ የተገኘ፤

ለ. የተሳሳተ ፊርማ መፈረም ወይም ሰነድ በመደለዝና በመሰረዝ ለማጭበርበር መሞከር፤

ሐ. የፌዴሬሽኑ አባላት ኮሚቴን መዝለፍ ዛቻና ማስፈራራት

መ. ያለ በቂ ምክኒያት ለአ/አ ምርጥ ሲመረጡ ምርጫ አለመቀበል፤

ሠ. ያለ በቂ ምክኒያት ከአ/አ ምርጥ ራስን ማሰናበት፤

ረ. ለኢትዮጵያ ሻምፒዮና ለመላው ኢትዮጵያ ጨዋታና ከተማውን በሚወክል ቡድን ላይ ተመርጦ ያልተሳተፈ፤

## 7. ለአንድ ዓመት ከውድደር የሚያሳግዱ የስነ-ስርዓት ጉድለቶች

ሀ. ከላይ በቁጥር 6 ከሀ-ረ ከተጠቀሱት የስነ-ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈጽሞ ከስድስት ወር ቅጣት የታለፈና ያንኑወይም ተመሳሳይ የስነ-ምግባር ጉድለቶች ፈጽሞ ሲገኝ፤

ለ. ከተማ አስተዳደሩን ወክሎ ለውድድር ክልል/ከተማ/ሄዶ በእንቢተኝነት ሳይወዳደር ተመልሶ ወደ አ/አ የተመለሰ፤

**8. ከሁለት ዓመት ከስልጠናና ከውድድር የሚያሳግድ የስነ-ስርዓት ጉድለት**

ሀ. ከላይ በቁጥር ሰባት ከሀ-ለ ከተጠቀሱት የስነ- ምግባር ጉድለቶች አንደኛውን ፈጽሞ የተገኙ በአንድ ዓመት የታለፈና ያንኑ ወይም ተመሳሳይ የስነ-ምግባር ጉድለት ፈጽሞሲገኝ ፤

ለ. አበረታች እፅ ወስዶ በምርመራ የተረጋገጠ ሲሆን፤

**9. የአ/አ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ የእግድ ቅጣቱን ወደ ገንዘብ ማዛወር /መቀየር/ ይችላል፤**

## አንቀፅ 14

## የአሰልጣኞች የስነ-ምግባር ጉድለት ማስተካከያና እርምጃዎችና ደረጃቸው

### 1. የቀላል ጥፋቶች ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የስነ- ምግባር ጉድለቶች

ሀ. ስራን በእቅድና በጋራ ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን፤

ለ. በስልጠና ስራ ውስጥ ሚስጥር መያዝ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች አለመጠበቅ

ሐ. ከስፖርታዊ ጨዋነት ውጪ ሆኖ መገኘት መጠጥ ጠጥቶ በስልጠናና በውድድር ቦታ መገኘት፤

### 2. የቀላል ጥፋቶች የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የስነ- ምግባር ጉድለቶች

ሀ. ከላይ ከተገለጹት አንቀጾች ከተጠቀሱ የስነ-ምግባር ጉድለቶች አንዱን ፈፅሞ በማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ ተመሳሳይ የስነ- ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ ፤

ለ. ፌዴሬሽኑ የሚያወጣቸው ደንቦችና መመሪያዎች አለማክበር፤

### 3. ከአ/አ ከተማ ምርጥ ቡድን አሠልጣኝነት የሚያሳግዱ የስነ-ምግባር ጉድለቶች፤

ሀ. ከላይ በንዑስ አንቀፅ ከሀ-ለ ስርከተጠቀሱት አንዱን ሰነ-ምግባር ፈፅሞ በፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የታለፈና ያንኑ የስነ-ምግባር ጉድለት ፈፅሞ ሲገኝ፤

ለ. በሙስና ተግባር ላይ መሰማራቱ ሲረጋገጥ ፤

ሐ. ያታዊ ትንኮሳ መፈፀሙ ሲረጋገጥ፤

መ. በስልጠና ስፍራዎች ሁከት መፍጠር ፀጥታን ማደፍረስ፤

ሠ. አበረታች መድሀኒቶችን ለአትሌቶች የሰጠ፤

ረ. በተጭበረበረ ማስረጃ ማሠልጠን በህግ እንዲጠየቅ ያደርጋል፣

ሸ. አሠልጣኙ የገባበትን ግዴታ ሳይፈፀም ሲቀር፤

## አንቀፅ 15

## የክለብ አመራሮች፤ የቡድን መሪ ፤ወጌሻና የቡድን አባላት የሰነ-ምግባር ጉድለት ማስተካከያ እርምጃዎችና ደረጃቸው

1. አንድ የክለብ አመራር የቡድን መሪ፤ ወጌሻ ወይም የቡድን አባላት በውድድር ስፍራ ያል ተገባ ፀባይ ካሳዩ የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡
2. አንድ የቡድን መሪ ወይም አባል ወይም ወጌሻ ወይም አመራር በውድድር ስፋራ ወይም በስልጠና ስፍራ ፌዴሬሽኑ የመደባቸውን ዳኞች ወይም አመራሮችን ያንጓጠጠ ወይም የውድድሩን መንፈስ ለመለወጥ ማንኛውንም ሙከራ ያደረገ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፡፡
3. የክለብ አመራሮች በሚደረገው የስብሰባ ጥሪና ውይይት መድረክ ላይ መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የማይገኙ ከሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ 2ኛ ጊዜ ከሆነ ብር 300.00 /ሦስት ሺ/ ያስቀጣል ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ ብር/ ይቀጣሉ
4. ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው ውድድሮች ወይም በሚሳተፉባቸው ውድድሮች ላይ በውድድር ስፍራ የተደባደበ ወይም ሁከት የፈጠረ አካል ከብር 3000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ ሊደርስ የሚችል የገንዘብ ቅጣት በክለቡ ወይም በሚመለከተው አካል ላይ ይወሰናል፡፡
5. በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄዱ ውድድሮች ከተማ አስተዳደሩን ወክለው እንዲወዳደሩ የሚመረጡ አትሌቶችን ሲጠየቅ ማንኛውም ክለብ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውጤት ቅድሚያ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ይህም በትይዩ በውድድር ከ1ኛ-5ኛ ደረጃ የወጡ አትሌቶችን ክለቡ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ይህ ባይሆን ግን በክለቡ ላይ እንደውድድሩ ክብደት፡-
    1. የመጀመሪያ ጥፋት ከሆነ ብር 10,000.00 ይቀጣል፡፡
    2. ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከሆነ ብር 15,000.00 ይቀጣል፡፡

3. ጥፋቱ ለሦስተኛ ጊዜ ከሆነ የክለቡ ፍቃድ ይሰረዛል፡፡

6. የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ደንብና መመሪያ ሳያከብር የቀረ ክለብ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል ድርጊቱን ደግሞ ሲፈጽም የገንዘብ ቅጣት ብር 8,000.00/ሰምንት ሺህ ብር/ይቀጣል፡፡

7. በከተማ አቀፍ ደረጃ አዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጀው ውድድሮች ላይ ያለበቂ ምክኒያት ሳይሳተፍ የቀረ ክለቡ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ ለ2ኛ ጊዜ ከፈፀመ የብር ቅጣት ብር 8,000.00 /አምስት ሺህ ብር/፣ ለ3ኛ ከሆነ ከአባልነት ይሰረዛል፡፡

## አንቀፅ 16

## ከአማተር አገልጋዮች ፣ከኮሚቴ አባላት፣ከዳኞች እና ከሌሎች አካላት የሚጠበቅ ስነ-ምግባር፤

1. ማንኛውም አማተር አገልጋዮች ኮሚቴ አባላት ዳኞች እና ሌሎችም አባላት በተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት ዙሪያ በግልና በጋራ ተጠያቂ ናቸው፡፡
2. ማንኛውም አማተር አገልጋዮች ወይም የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ
   - ሀ. መደበኛ በሆኑና ባልሆኑ ጥሪ ሲደረግባቸው ስብሰባዎች ላይ መገኘት፤
   - ለ. የፌዴሬሽኑ ስምና ዝና የመጠበቅ፤
   - ሐ. የእርስ በርስ የመከባበር የመደማመጥ ሀሳብን የሌላውን ስብዕና ሳይነካ በቀጥታ መግለፅ፤
   - መ. ከፌዴሬሽኑ አባላት ጋር መልካም ግንኙነት የመፍጠርና አርአያ ሆኖ መገኘት፤
   - ሠ. የፌዴሬሽኑ ልዩ ልዩ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተገዢ መሆን፤
   - ረ. ለስፖርታዊ ጨዋነት መርሆች መገዛትና አርአያ መሆን፤
   - ሸ. አሉባልታ፤ሙስናንና ብልሹ አሰራር መዋጋት፤
   - ቀ. ከክ/ከተማ አትሌቲክስ ኮሚቴ፤ከክለቦች በአጠቃላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር መልካም የሆነ የስራ ግንኙነት እንዲኖር መጣር፤
   - በ. በፌዴሬሽኑ በሚሰጡ ሙያ ማሻሻያ ሲሚናርና ስብሰባዎች ላይ መገኘት፤
   - ተ. በሚመደቡበት ሙያዊ ወይም ስራ በተሰጡት ቀናትና ሰዓት አገልግሎት መስጠት፤
   - ቸ. በቅንነትና ከአድሎ ነፃ በሆነ መልኩ በሚመደቡበት ስራ ማገልገል፤
   - ነ. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ክስ በተመለከተ ውሳኔ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይወሰናል፣
3. ከላይ ከተገለፁትንና ሌሎች የህግ ጥሰቶች ሲያጋጥሙ ፌዴሬሽኑ የሚከተለውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የቃል ማስጠንቀቂያ፤

ለ .ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፤

ሐ. ጥፋቱ ከባድ ከሆነ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም አግባብነት ያለው ኮሚቴ ተገምግሞ እስከ ሁለት ዓመት በማገድ ውሳኔ ይሰጣል፤

መ. ገንዘብ ቅጣት ሊያስቀጣ የሚችል ጥፋት ከሆነ በገንዘብ ቅጣት እስከ 15,000.00/አስራ አምስት ሺህ ብር/ድረስ ሊቀጡ ይችላሉ፡

## አንቀጽ 17

## የክስ አቤቱታ አቀራረብና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት፤

ማንኛውም በዚህ ደንብ ላይ በተካተቱ ጉዳዮች መሠረት የሚነሳ ክስ አቤቱታ በሚከተለው መንገድ ይከናወናል፤

ሀ. አትሌቱ አሰልጣኙ ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል የክስ አቤቱታውን በፅሁፍ ለፌዴሬሽኑ ጽ/ቤት ያቀርባል፤

ለ. ጽ/ቤቱ የቀረበለትን ክስ ከስነ- ምግባር ደንብና ከፌዴሬሽኑ መመሪያዎች ጋር በማገናዘብ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሁለቱን ወገኖች አቅርቦ በጉዳዩ ላይ አሰተያየታቸውን እንዲሰጡ ያደረጋል፡፡

ሐ. ሁለቱም ወገኞች አሉኝ የሚሏቸውን መረጃዎች ማቅረብ ፤የማዳመጥና የማየት ኃላፊነት አለበት፤

## አንቀፅ 18

## ስለ ይግባኝ አቀራረብና የይግባኝ መብቶች

1. የክስ ሠሚ ኮሚቴ አባላት ከ3-5 ያልበለጡ ይሰየማሉ ፤ይግባኙም በዚሁ ይታያል፤
2. ይህን የፌዴሬሽኑ ዲሲፕሊን መተዳደሪያ ደንብ የተላለፉ ውሳኔዎች የመጨረሻ ናቸው የሚል ካልሆነ በቀር ማንኛውም የይግባኝ አቤቱታዎችለክስ ወይም ለይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ሊቀርቡ ይችላሉ፤
3. አትሌቶች፤ አሰልጣኞችና ሌሎች አባላት በጊዜ ገደብ የተቀጡ የቅጣቱን ግማሽ እንደፈፀሙ እገዳው እንዲነሳላቸው ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ፤
4. የገንዘብ ቅጣት የተጣለባቸው ይግባኝ የሚጠይቁት የቅጣቱን ግማሽ ከፍለው ማስረጃ ሲያቀርቡና ጥያቄቸውን በጽሁፍ ሲያቀርቡ ነው፤
5. በይግባኝ የማይታዩ የሚከተሉት ጉዳዮች ይሆናሉ

   ሀ. የተሰጡ የቃል ማስጠንቀቂያ፤

ለ. ተግሳጽ ወይም ወቀሳ፤

ሐ. እስከ ሁለት ወር የሚደርስ እገዳ ቅጣት፤

መ. እሰከ 1000.00/አንድ ሺ.ህ ብር/ የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት፤

6. ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ውሳኔ ከተሰጠበት ሶስት ቀን ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት ለይግባኝ መጠየቂያ 1000.00/አንድ ሺ.ህ ብር/ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## አንቀፅ 19

## ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ህጎች፤

ከዚህ ዲሲፕሊን መመሪያ ጋር የሚጋጩ የዲሲፕሊን መመሪያዎች ወይም የውድድርና ስነ - ስርዓት ኮሚቴ ወይም የክለቡ ደንቦች ወይም ልምዶችና አሰራሮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

## አንቀጽ 20

## የዲስፒሊን መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀፅ 21

## መተዳደሪያ ደንቡን ስለማሻሻል

21.1. ይህ መመሪያ እንዲሻሻል ክለቦች/ቡድኖች በተወካዮቻቸው ወይም በክ/ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሲጠየቅ እና ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ከ50% በላይ መሻሻሉ ከታመነበት ሊሻሻል ይችላል፡፡

21.2. በዚህ መመሪያ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ አሻሚ ትርጉም የሚያሰጡ ሁኔታዎች ቢያጋጥሙ የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 22

## የመመሪያው ተፈፃሚነት

22.1. ይህ መመሪያ በክ/ከተማ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች፣ በክለቦች፣ በፕሮጀክቶችና ልዩ ልዩ ቡድኖች እንዲሁም በአትሌቶችና በአሠልጣኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 23

## ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ደንቦች

ቀደም ሲል በ2004 ዓ.ም ጸድቆ በስራ ላይ የዋለው መተዳደሪያ ደንብ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ተሽሯል፡፡

## አንቀፅ 24

## መመሪያውን ስለመተርጎም

በዚህ መመሪያ ላይ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ሲያጋጥሙን የአዲስ አበባ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የመተርጎም ስልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 25

## መተዳደሪያ ደንቡን ስለማጽደቅ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ከጸደቀበት ከታህሳስ ወር 2012 ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

የአ/አ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን
ታህሳስ 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ